# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሰኞ 83ኛ ዓመት ቁጥር 014 መስከረም 14 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!


# «የዓለም የጸጥታ ዘርፍ ቅኝት የሀገራትን ሉዓላዊነት ያከበረ፣ የባለብዙ ወገን ትብብር እና አካታችነትን የተከተለ ሊሆን ይገባል»

- አቶ ደመቀ መኮንን ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር እና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



አዲስ አበባ፡- የዓለም የጸጥታ ዘርፍ ቅኝት የሀገራትን ሉዓላዊነት ያከበረ፣ የባለብዙ ወገን ትብብር እና አካታችነትን የተከተለ እንዲሆን ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር እና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን ጥሪ አቀረቡ።

አቶ ደመቀ ይህን ያሉት «ሰላም፣ ብልፅግና፣ ለውጥና ዘላቂነት» በሚል መሪ ሃሳብ በአሜሪካ ኒውዮርክ እየተካሄደ ባለው 78ኛው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጉባዔ ላይ ባደረጉት ንግግር ነው።

ኢትዮጵያ ለመንግሥታቱ ድርጅት መመስረት ታሪካዊ ሚና እንደተጫወተች ሀገር የጋርዮሽ ዓለም እንዲኖር ትሻለች ብለዋል። የነበረው አካታች ያልሆነ መዋቅር የጋራ ፍላጎትን ለማስፈጸም የማያስችል በመሆኑ ሁላችንም በተባበረ መንገድ የባለብዙ ወገን ሥርዓት ለመዘርጋት አቋም ሊኖረን ይገባል ብለዋል።

ዓለምአቀፋዊ ሰላምና ጸጥታ እንዲሰፍን ከተፈለገ አዲሱ የዓለም የጸጥታ ሥርዓት የአባል ሀገራትን ሉዓላዊነት ያከበረ መሆን እንዳለበት ኢትዮጵያ በጽኑ እንደምታምን ነው አቋሟን የገለጹት። ኢትዮጵያ በመንግሥታቱ ድርጅት ሰላም ማስከር ተልዕኮ ስር ለዓለም ሰላም ቁልፍ ሚና እንደተጫወተ ሀገር የጸጥታው ምክር ቤት ሪፎርም

«የዓለም የጸጥታ ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል

# በ80 ቢሊዮን ብር የሚገነባው የማዕድን ፋብሪካ ማሽኖችን ማስገባት ጀመረ

- ፋብሪካው በተያዘው ዓመት የሙከራ ምርት ይጀምራል

**ፍሬሕይወት አወቀ**



ሀዋሳ፡- በ80 ቢሊዮን ብር የሚገነባው የቀንጢቻ ማዕድን ፋብሪካ ማሽኖችን ማስገባት መጀመሩ ተገለፀ።

የቀንጢቻ ማይኒንግ ኩባንያ ጀነራል ማናጀርና ዋና ዳይሬክተር ሚስተር ብሩስ ቲኒ እንደገለጹት፤ ለማዕድን ፋብሪካው ማሽኖችን ማስገባት ተጀምሯል፡፡

በማዕድኑ ዘርፍ ኢትዮጵያ በማዕድን ሀብት ትልቅ አቅም ያላት መሆኑን ጠቅሰው፣ ሀገሪቱ በማዕድን ዘርፍ ብዙ መሥራትና መጠቀም ይኖርባታል ያሉት ኃላፊው፤ በተለይም ሊትየም በዓለም ላይ በጣም ተፈላጊነቱ እየጨመረ መሆኑን ጠቁመው በቀጣይ ከፍተኛ ገቢ የምታገኝበትና የውጭ ባለሀብቶችንም ትኩረት የሚስብ መሆኑን አስገንዝበዋል።

ኩባንያው አሁን ላይ ካስገባቸው ማሽኖች በተጨማሪ በቀጣይም ቀሪ ማሽኖችን በማስገባት ላይ መሆኑን የተናገሩት ሚስተር ብሩስ፤ በዚሁ ዓመት የሙከራ ምርት ማምረት እንደሚጀምር ተናግረዋል። ኩባንያው የማዕድን ሀብቱን ከማልማት ጎን ለጎን ለአካባቢው ማኅበረሰብ ትምህርት ቤት፣ መንገድ፣ የጤና ተቋማትና የተለያዩ መሠረተ ልማቶችን እያሟላ እንደሆነም ሚስተር ብሩስ ተናግረዋል።

በአፍሪካ የመጀመሪያው የሆነውን ማሽን ወደ ኢትዮጵያ ያስገባው የቀንጢቻ ማይኒንግ ከፍተኛ ሼር ሼህ ዓሊ ሁሴን በበኩላቸው፤ ኩባንያው የሊቲየም ምርትን በማልማት ቀዳሚ መሆኑን ነው፡፡ በአሁኑ ወቅትም በአፍሪካ የመጀመሪያ የሆነውን

በ80 ቢሊዮን ብር ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል

# ክልሉ በመስቀል በዓል ከአንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን በላይ ጎብኚዎችን ለማስተናገድ ተዘጋጅቷል

ገጽ 6



# «የመውሊድ በዓልን ኢስላማዊ ሥርዓት በጠበቀና አብሮነትን በሚያጠናክር መንገድ ማክበር ይገባል»

- ዶክተር ሼህ አቡበክር ሱሌይማን

ገጽ 6


















አቶ ዮዳሄ አርዓያሥላሴ

## ለ25 ሚሊዮን ዜጎች ብሔራዊ መታወቂያ ሊሰጥ ነው

- **እስከ አሁን ለሦስት ሚሊዮን ዜጎች ተሰጥቷል**

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- በ2016 ዓመተ ምህረት ማብቂያ ለ25 ሚሊዮን ዜጎች ብሔራዊ መታወቂያ ለመስጠት እየተሠራ መሆኑን የብሔራዊ መታወቂያ መርሐ ግብር አስታወቀ። እስከ አሁን ለሦስት ሚሊዮን ዜጎች ብሔራዊ መታወቂያ እንደተሰጠም ተገልጿል።

የብሔራዊ መታወቂያ መርሐ ግብር ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ዮዳሄ አርዓያሥላሴ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ መርሐ ግብሩ በ2014 ዓመተ ምህረት ምዝገባ የጀመረ ሲሆን በተለያዩ አካባቢዎች ከ125 ሺህ በላይ ለሚሆኑ ሰዎች የብሔራዊ ዲጂታል መታወቂያ መሰጠት ተችሏል። በ2015 ማብቂያ ከትምህርት ሚኒስቴርና ከሌሎች ድርጅቶች ጋር በጥምረት በተሠሩ ሥራዎች ወደ 3 ሚሊዮን የሚጠጉ ዜጎችን የብሔራዊ ዲጂታል መታወቂያ ባለቤት ማድረግ ተችሏል።

በቀጣይም የዲጂታል መታወቂያውን ኅብረተሰቡ በተለያዩ አካባቢዎች እንዲያገኝ የማመቻቸት ሥራ ይሠራል ያሉት አቶ ዮዳሄ፤ በ2018 ዓመተ ምህረት ማብቂያ ከ90 ሚሊዮን በላይ ዜጎች የብሔራዊ ዲጂታል መታወቂያ እንዲኖራቸው ይደረጋል ብለዋል።

በ2016 ዓመተ ምህረት ለ25 ሚሊዮን ዜጎች ዲጂታል መታወቂያ ለመስጠት ተማሪዎችንና የባንክ ደንበኞች ላይ ትኩረት ተደርጎ ይሠራል። ለዚህም ከትምህርት ሚኒስቴር፣ ከፋይናንስ ዘርፉ፣ ከገቢዎች ሚኒስቴርና ከሌሎች ተቋማት ጋር በመተባበር እንሠራለን ብለዋል።

ትግበራው የአሠራር ሥርዓትን ለማዘመን ያለመ ነው። የብሔራዊ ዲጂታል መታወቂያው ኅብረተሰቡ በአገልግሎት ሰጪ ተቋማት ተገቢውን አገልግሎት እንዲያገኝ ጉልህ እገዛ ያደርጋል። እንደ ባንክ፣ ጤና፣ ኢንሹራንስ እና የመሳሰሉ ሌሎች አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ለኅብረተሰቡ የተፋጠነ እና ዘመናዊ ሥራ እንዲሰጡ ምቹ ሁኔታን እንደሚፈጥርም ገልጸዋል።

እንደ ዋና ሥራ አስኪያጁ ገለፃ፤ በአዋጁ መሠረት የመታወቂያው ትክክለኛ መጠሪያ የኢትዮጵያ ዲጂታል መታወቂያ ነው። ይህንን መታወቂያ እውን ለማድረግ እስከ አሁን ሦስት አሠራሮች ተዘርግተዋል። አንደኛው በኪስ የሚያዝ የፕላስቲክ መታወቂያ (እንደ ዲጂታል የቀበሌ መታወቂያ ዓይነት) የሚሰጥ ሲሆን ሁለተኛው በፒዲፍ የተዘጋጀ ነው። ሦስተኛው በስልክ ላይ መታወቂያውን በማስቀመጥ መገልገል የሚቻልበት ሥርዓት ነው።

ሦስቱ አማራጮች በሕግ ፊት እኩል ተቀባይነት አላቸው። ይህንን በሚመለከት ለፖሊስ፣ ለክልሎች እና ለተለያዩ አካላት የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች እየተሠሩ ነው ያሉት አቶ ዮዳሄ፤ ብሔራዊ ዲጂታል መታወቂያ በኪስ የሚያዝ ወረቀት ብቻ ሳይሆን የራሱ መለያ /ፋይዳ/ የሚባል ቁጥር ይዞ በማንኛውም ቦታ በቁጥሩ ምክንያት አገልግሎት ማግኘት የሚችሉበት ዘመናዊ አሠራር መሆኑንም አስረድተዋል።

ዲጂታል መታወቂያ በኢትዮጵያ የሚኖር ማንኛውም ዜጋ የራሱን ማንነት የሚገልጽበት መለያ ነው ያሉት ያሉት አቶ ዮዳሄ፤ አንድ ሰው ከቤቱ ሆኖ የባንክ አካውንት መክፈት፣ የኢንሹራንስ አገልግሎት ማግኘትና በአገልግሎት ሰጪውና ተቀባዩ ዘንድ መተማመን መፍጠር ያስችላልም ብለዋል፡፡

# በቱሪዝም ዘርፍ ሀገራዊ ዕድገትን ለማረጋገጥ የተደረጉ ማሻሻያዎች ውጤት እያስገኙ ነው

**ማርቆስ በላይ**



አዲስ አበባ፡- ሀገራዊ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ዕድገትን ለማረጋገጥ የተደረጉ ማሻሻያዎች ውጤት እያስገኙ ነው ሲሉ በኦሮሚያ ክልል በምክትል ርዕሰ መስተዳድር ማዕረግ የማኅበራዊ ዘርፍ አስተባባሪ አቶ አብዱላኪም ሙሉ ገለጹ፡፡

የኢሬቻ በዓልን ምክንያት በማድረግ የተዘጋጀው የኦሮሚያ ቱሪዝም ሳምንት ትናንት በይፋ ተከፍቷል፡፡

አቶ አብዱላኪም በመርሐግብሩ መክፈቻ ላይ እንደገለጹት፤ ሀገራዊ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ እድገትን ለማረጋገጥ ዘርፈ ብዙ ማሻሻያዎች እየተደረገ በመሆኑ የቱሪዝም ሀብቶችን ለማስተዋወቅና የዜጎችን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚ ለማድረግ በተደረገው ጥረት አበረታች ውጤት ተገኝቷል።

የቱሪዝሙ ዘርፍ ላይ በመሥራት እንደ ሀገር ያለው ተፈጥሯዊ ሀብት እንዳይባክን ማድረግ ያስፈልጋል ያሉት አቶ አብዱላኪም፤ የክልሉ መንግሥት ለቱሪዝም ዘርፍ ትልቅ ትኩረት በመስጠት እየሠራ ይገኛል ብለዋል፡፡

በክልሉ የሚገኙትን የቱሪዝም ሀብት ለዓለም ለማስተዋወቅ ሰፊ ሥራዎች መሠራታቸውን ጠቅሰው፤ ቱሪዝም የኢኮኖሚ ምንጭ በመሆኑ አበረታች ውጤት እየተገኘ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ የቱሪዝም ዘርፍ የዜጎችን የኑሮ ሁኔታ ለማሻሻል የሚያስችል ነው ያሉት ኃላፊው፤ የክልሉ መንግሥት የቱሪዝም መዳረሻዎችን በማስፋፋትና በማስተዋወቅ ከፍተኛ ሥራ እየተሠራ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

እንደ ክልሉ በቱሪዝም ዘርፍ በተሠሩ ሥራዎች አበረታች ውጤት መገኘቱን በመግለፅ የባሌ ብሔራዊ ፓርክ በዩኔስኮ ማስመዝገብ መቻሉን ለአብነት አንስተዋል፡፡ ከቱሪዝም ዘርፉ ዜጎች ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ተጠቃሚ በማድረግ ተሳታፊና የቱሪዝም ሀብቶችን እንዲንከባከቡ የማድረግ ሥራ እየተሠራ ነው ብለዋል፡፡

የኦሮሚያ ቱሪዝም ኮሚሽን ኮሚሽነር ለሊሴ ዱጋ በበኩላቸው፤ የሦስተኛው ዙር በተዘጋጀው የቱሪዝም ሳምንት የሩዋንዳ፣ ዑጋንዳና ኬንያ የቱሪዝም ዘርፍ አባላት መገኘታቸውን ተናግረዋል፡፡

በቱሪዝም ሳምንቱ በቱሪዝም ዘርፍ አስተዋጽኦ ያበረከቱ አካላት ለ3ኛ ጊዜ ይሸለማሉ ያሉት ኮሚሽነር ለሊሴ፤ በቪዚት ኦሮሚያ የቁንጅና ውድድር የኦሮሚያ ቱሪዝም አምባሳደር ትመረጣለች ብለዋል፡፡

እንደ ኮሚሽነር ለሊሴ ገለጻ፤ በቱሪዝም ኤግዚቢሽኑ የተለያዩ የሆቴል፣ የቱሪዝም፣ የጉዞና አስጎብኚ ድርጅቶች ምርትና አገልግሎታቸውን ያስተዋውቃሉ፡፡ በቱሪዝም ሳምንቱ ቴክኖሎጂና ቱሪዝም ለማስተሳሰር የቱሪዝም ሃካቶን ውድድር ለ3ኛ ጊዜ ለአዳዲስ የቱሪዝም ቴክኖሎጂ ፈጠራዎች እውቅና እንደሚሰጥ ገልፀዋል።

የቱሪዝም ሳምንትና ኤግዚቢሽኑ ከመስከረም 13 እስከ 15 የሚካሄድ መሆኑ ተገልጿል፡፡



# የመስቀል ደመራ፣ የመውሊድና የኢሬቻ በዓላት ላይ በጎ ፍቃደኞች ከፀጥታ አካላት ጋር በቅንጅት ይሠራሉ

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ፡- የመስቀል ደመራ፣ የመውሊድና የኢሬቻ በዓላት ላይ በጎፍቃደኞች ከፀጥታ አካላት ጋር በቅንጅት እንደሚሠሩ ተጠቆመ።

ከሁለት ሺህ በላይ በጎፍቃደኞችና የከተማዋ ጸጥታ አካላት የተሳተፉበት የፓናል ውይይት ትናንት ተካሂዷል።

በፓናል ውይይቱ ላይ ንግግር ያደረጉት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኅብረተሰብ ተሳትፎና በጎ ፍቃድ ማስተባበሪያ ኮሚሽን የበጎፍቃድ ዘርፍ ምክትል ኮሚሽነር ወይዘሮ ነፃነት ዳባ እንደገለፁት፤ ሦስቱም በዓላት በሀገራችን ዜጎች ትልቅ ቦታ የሚሰጣቸው ናቸው። የፓናል ውይይቱም እነዚህን ትላልቅ በዓላት በሰላም እና በደመቀ ሁኔታ ለማክበር የሚያስችል ነው።

በጎፍቃደኞች የሁልጊዜ ተግባራቸውን ተፈጻሚ በማድረግ በዓላቱ የአንድነት፣ የአብሮነት፣ የህትማማችነትና ወንድማማችነት የምናጎለብትበት የምናጠናክርበት በዓል መሆን አለበት ሲሉ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፖሊስ ኮሚሽን፣ ከሰላምና ፀጥታ አስተዳደር ቢሮ ተወክለው ንግግር ያደረጉት ኢንስፔክተር ካሊድ የማታ በበኩላቸው፤ የመስቀል ደመራ፣ የመውሊድና የኢሬቻ በዓላት የአደባባይ በዓላት ከመሆናቸው ጋር ተያይዞ ሰፊ ሥራ ይጠይቃል። ስለዚህም ማኅበረሰቡ በተለይ ደግሞ የከተማዋ በጎፍቃደኛ ወጣቶች ከጸጥታ አካላት ጋር በቅንጅት በመሥራት በዓላቱ በሰላም እንዲጠናቀቁ የበኩላቸውን ሊወጡ ይገባል።

ቢሮው ሰላምን ለማረጋገጥ ከዚህ ቀደም ከሚሠራቸው መደበኛ ተግባራት ለበዓላቱ የተለየ እንቅስቃሴ እያደረገ ይገኛል ያሉት ኢንስፔክተር ካሊድ፤ ኅብረተሰቡም ሰላምን ያውካሉ ብሎ የታዘባቸው ድርጊቶች ካሉ በወቅቱ ሊጠቁም ይገባል ብለዋል።

ዜና

# ትውልድን የተመረኮዘው የሀገር ግንባታ

ልጅዓለም ፍቅሬ

ነገርን ከስሩ ውሃን ከጥሩ ሲሉ አበው ይተርታሉ፡፡ እንዲህ ያለው ቃል ለዚህ ጉዳይ ተገቢ አማርኛ ነው፡፡ ሀገርን ለመገንባት ትውልድን ማብቃት አቻ የሌለው ተግባር ነው፡፡ ትውልድን ብቁ ማድረግ ቀላል ሥራ አይደለም፡፡ አሁን ላይ ትናንት አብነት ይደረጋል፡፡ ዛሬንም እንደ መልካም ዕድል መጠቀም ያስፈልጋል፡፡ ትውልድ እንደ ሻማ ነው፡፡ ከተንከባከቡት ቀልጦ ይበራል፤ ካልሆነ ጥቅም ሳይሰጥ ይቀልጣል፡፡ ትውልድን መገንባት ለእከሌ ተብሎ የተጣለ ግዴታ አይደለም። የሁሉም ኃላፊነት ነው፡፡

ትውልድ ብቁ፣ ጠንካራ የሥነ ልቦና ውቅር ያለው መሆን አለበት፡፡ በሥነ-ምግባር ሊታነጽም ይገባዋል፡፡ ማኅበራዊ እሴቶችን ያዳበረ አርቆ አሳቢ ትውልድ ለማፍራት የቤት ሥራዎች አይታጡም። ግለሰቦች፣ ግብረ-ሰናይ ድርጅቶች፣ የመንግሥት ተቋማት፣ ቤተ-እምነቶች ኃላፊነት በመውሰድ ረገድ ግንባር ቀደም ናቸው፡፡

በሀገራት መለያያ መንገድ አያጡም፡፡ ሀብት፣ ቴክኖሎጂ፣ እውቀት እንዲሁም ባህልና እሴት አንዱን ከሌላው ይለያሉ፡፡ እነዚሁ ሀገራት ልዩነቶችን ለማጥበብ ጎንበስ ቀና ሲሉ መመልከት የተለመደ ነገር ነው፡፡ ይህም መልካም ዕድሎችን ለመጠቀም ያስችላል፡፡ እዚህ ላይ የዳያስፖራው ያለው ሚና ቀላል የሚባል አይደለም፡፡

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጉዳዩን በሚመለከት ጠይቋል፡፡ መላሹ አቶ ደመቀ ነጋሳ ይባላሉ፡፡ በአውሮፓ ኔዘርላንድ ለብዙ ዓመት ኖረዋል፡፡የኢትዮጵያ ዳያስፖራ ማኅበር ምክትል ፕሬዚዳንት ናቸው፡፡ ስለትውልድ ግንባታ የልባቸውን አውግተዋል፡፡ ኢትዮጵያውያኑ የውጭ ነዋሪዎች ትውልድን በመገንባት ሂደት ውስጥ የማይተካ ሚና አላቸው፡፡

በሀገሪቱ ዘላቂ ልማት ማምጣት ላይ ዳያስፖራው ስላለው አስተዋፅኦ በአቶ ደመቀ ተጠቅሷል፡፡ እውቀትን፣ ልምድን፣ ቴክኖሎጂን ለማሸጋገር ኢኮኖሚን ከመደገፍና የሀገሪቱን ዲፕሎማሲ ማሳደግ ላይም ሚናቸው ከቁጥር በላይ ነው ባይ ናቸው፡፡ ዳያስፖራው የሀገሪቱን ባህል፣ እሴት ለተቀረው የዓለም ክፍል ያስተዋውቃል፡፡ ይህን ለማድረግ ጠቃሚ የሆኑ አዲስ አሠራሮችን ወደ ሀገራቸው ማስተላለፍ ተገቢ ነው፡፡

ሀገርን በዘላቂነት ለመገንባት ትውልድ ላይ መሥራት የማይዘነጋ ቀዳሚ ተግባር ነው። ዳያስፖራው በቴክኖሎጂ ሊያለማ ይገባዋል፡፡ በመሠረተልማት ልማት ላይም መሳተፍ አለበት። አቶ ደመቀ በኢንቨስትመንትና ሥራ ዕድል ፈጠራ ላይ ቢሳተፉ መልካምነቱን ገልጸዋል፡፡ ለኢትዮጵያውያ ኑ ትውልድን መገንባት ጎን ለጎን ሌሎችም ሥራ አሏችሁ ብለዋል፡፡ ለልጆቻቸው ባህል፣ ታሪክ፣ እሴትና ቋንቋቸውን ማሳወቅ አለባቸው፡፡

ብርሃኑ ገረመ (ዶ/ር) ቀጣይ አስተያየት ሰጪ ናቸው፡፡ አውሮፓ ነዋሪ ናቸው፡፡ የበለጸገች ኢትዮጵያን ለመፍጠር ምን ይጠበቅብናል ለሚለው ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ትውልዱ ላይ ስለሚከወኑ ተግባራት አስፈላጊነት ገልጸዋል፡፡ የዳያስፖራው ተሳትፎ መጠነከር መቻል አለበት ብለዋል፡፡

ዳያስፖራዎች በተለያዩ የሥራ መስኮች ላይ ተሳታፊ ናቸው፡፡ የትምህርትና የምርምር ተቋማት ላይ ይገኛሉ፡፡ ይህም በትምህርት ላይ ሰፊ ተግባር ለማከናወን አቅም ይፈጥራል፡፡ በዚህ ብቻ መቆም አያስፈልግም፡፡ ቀጣይ ሥራዎች መሥራት ያስፈልጋል፡፡ ያለውን ተሞክሮ ማካፈል ይገባል፡ ፡ ዴሞክራሲ ማጎልበት ሂደት ላይ ሚናው ጉልህ ነው፡፡ በቴክኖሎጂ ሽግግርና መልካም አስተዳደር ግንባታም ላይ ሥራው ቀላል አይባልም። በተለያዩ ዘርፎች ያለ ድጋፉን አጠናክሮ መቀጠል እንዳለበትም ይመክራሉ፡፡

# ለሀገራዊ ምክክሩ ኅብረተሰቡ አምኖ የሚመርጣቸው ተወካዮች የተጣለባቸውን ኃላፊነት በብቃት መወጣት አለባቸው

- **በአዲስ አበባ በአጀንዳ ልየታ የሚሳተፉ ተወካዮች ልየታ ተጠናቋል**

መአዛ ማሞ

አዲስ አበባ፡- ለሀገራዊ ምክክሩ ኅብረተሰቡ አምኖ የሚመርጣቸው ተወካዮች የተጣለባቸውን ኃላፊነት በብቃት መወጣት እንዳለባቸው የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ገለጸ። በአዲስ አበባ በአጀንዳ ልየታ የሚሳተፉ ተወካዮች ልየታ ተጠናቋል።

የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ ምክትል ዋና ኮሚሽነር ሂሩት ገብረሥላሴ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የአመራረጥ ሂደቱ ከተለያዩ የማኅበረሰብ ክፍሎች በተባባሪ አካላት የተለዩት ተሳታፊዎች ከየማኅበረሰብ ክፍሉ ሁለት ተወካዮችን መርጠዋል። ተሳታፊዎቹ የሚያምኑባቸውን ተወካዮች በራሳቸው መምረጣቸውን ጠቁመው፣ የተመረጡት ተወካዮች ሀገራዊ ምክክሩ ስኬታማ እንዲሆን ያላቸውን ሁሉ ሳይሰስቱ እንዲሠጡና የተጣለባቸውን ኃላፊነት በብቃት መወጣት እንዳለባቸው ተናግረዋል።

በሁሉም ክፍለ ከተሞች በሁለት ዙር የተደረገው በአጀንዳ ልየታ የሚሳተፉ ተወካዮች ልየታ መስከረም 12 መጠናቀቁንም ገልጸዋል።

ተወካዮችን የማስመረጡ ሂደት ረዘም ያለ ሂደት እንደነበረ ያስታወሱት ኮሚሽነር ሂሩት ግብዓት ከማሰባሰብ ጀምሮ ተባባሪ አካላትን በማቋቋም ወደ ሥራው መገባቱን አስታውሰዋል። ተባባሪ አካላቱ ከፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ከሲቪክ ማኅበራት፣ ከዕድር መሪዎች፣ መምህራን እና ዳኞች የተካተቱበት ሲሆን ለእነዚህ አካላት ሥልጠና በመስጠት ኮሚሽኑ የሚሠራውን ሥራ እንዲያግዙ እንዲሁም እንዲታዘቡ መደረጉን ተናግረዋል።

ምክክር ምን እንደሆነና የሚደረገውን ዝግጅት እንዲረዱ በማድረግ በየአካባቢያቸው ተሳታፊዎችን እንዲለዩ የተደረገ መሆኑን አስታውሰው፤ ከየወረዳው ከተለያዩ ማኅበረሰብ ክፍሎች የተለዩት ተሳታፊዎች ለአጀንዳ ልየታ ተወካዮቻቸውን እንዲመርጡ መደረጉን ገልጸዋል። አመራረጡም ተሳታፊዎቹ ይወክሉናል የሚሏቸውን ተወካዮች ያለኮሚሽኑ ጣልቃ ገብነት በራሳቸው መምረጣቸውን ኮሚሽነሯ አስረድተዋል።

በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ሪፖርተር ምልከታ የተደረገበት የየካ ክፍለ ከተማ የልየታ ማዕከል ከስድስት ወረዳዎች ከተለያዩ የማኅበረሰብ ክፍሎች የተውጣጡ ተሳታፊዎች ተወካዮቻቸውን በራሳቸው መርጠዋል።

ከወረዳ ዘጠኝ የንግዱን ማኅበረሰብ ወክለው የተገኙት አቶ ጆቴ ቶሎሳ ሀገራዊ ምክክሩ ያለውን አለመግባባት ቀርፎ ዘላቂ ሰላም እንደሚያመጣ እምነታቸው መሆኑን ገልጸው፤ እሳቸውም የበኩላቸውን ለማበርከት መዘጋጀታቸውን ጠቁመዋል። የወረዳ ዘጠኝ የሴቶች ተወካይ የሆኑት ወይዘሮ ክብነሽ ኡርጌ በበኩላቸው ምክክሩ ነፃና ስኬታማ እንዲሆን ኮሚሽኑ እያደረገ ያለውን ጥረት አድንቀው ምክክሩ ሰላምን ይዞ የሚመጣ በመሆኑ ሁሉም የሚጠበቅበትን በማድረግ የድርሻውን እንዲወጣ ጠይቀዋል።

# ከቱሪስቶች ከ86 ቢሊዮን ብር በላይ ወደ መዲናዋ ኢኮኖሚ እንዲገባ ይደረጋል

ዳግማዊት አበበ

አዲስ አበባ፡- በተያዘው በጀት ዓመት ከሀገር ውስጥ እና ከውጭ ቱሪስቶች 86 ነጥብ 99 ቢሊዮን ብር ወደ መዲናዋ ኢኮኖሚ ፈሰስ ይደረጋል ተብሎ ይጠበቃል ሲል የአዲስ አበባ ባህል ኪነጥበብና ቱሪዝም ቢሮ አስታወቀ፡፡ ከ35 ሚሊዮን 498 ሺህ በላይ ብር ከቱሪዝም ዘርፍ ቀጥተኛ ገቢ ለማግኘት ታቅዷል፡፡

በአዲስ አበባ ባህል፣ ኪነጥበብና ቱሪዝም ቢሮ የዕቅድና በጀት ዝግጅት፣ ክትትልና ግምገማ ዳይሬክተር አቶ ደረጀ መኮንን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በ2016 በጀት ዓመት ከውጭ ቱሪስቶች 42 ነጥብ 59 ቢሊዮን ብር እንዲሁም ከሀገር ውስጥ ቱሪስቶች 44 ነጥብ አራት ቢሊዮን ብር በአጠቃላይ 86 ነጥብ 99 ቢሊዮን ብር ወደ መዲናዋ ኢኮኖሚ እንዲገባ ይደረጋል ተብሎ ይጠበቃል፡፡

በ2015 ዓ.ም 39 ነጥብ 15 ቢሊዮን ብር ወደ መዲናዋ ኢኮኖሚ እንዲገባ መደረጉን ያነሱት አቶ ደረጀ ይህም ከውጭ ቱሪስቶች ብቻ ነው ብለዋል።

እንደ ዳይሬክተሩ ገለጻ፤ የከተማዋ ኢኮኖሚ ላይ የገባ የገንዘብ መጠን የሚሰላው አንድ ቱሪስት ከተማዋ ላይ ሲቆይ በቀን ምን ያህል ያወጣል ምን ያህል ቀንስ ይቆያል የሚለው ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው፡፡ በዚህ ዓመት 650 ሺህ የውጭ እንዲሁም ሰባት ሚሊዮን 500 ሺህ የሀገር ውስጥ ቱሪስቶች ከተማዋን ይጎበኛሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡

በሌላ በኩል ከዘርፉ በየደረጃው ከሚሰጡ አገልግሎቶች 26 ሚሊዮን 500 ሺህ የሚጠጋ ብር እንዲሁም ልዩ ልዩ ፕሮጀክቶችን በመቅረፅ ከዘጠኝ ሚሊዮን ብር በላይ ገቢ ለማግኘት ታቅዷል ያሉት አቶ ደረጀ፤ በአጠቃላይ እንደቢሮ ከአገልግሎቶች እና ተባባሪ አካላት 35 ሚሊዮን 500 ሺህ የሚጠጋ ብር ገቢ ለማግኘት ይሠራል ሲሉ ገልጸዋል፡፡

ዳይሬክተሩ እንዳሉት፤ ከቱሪዝም ከኪነጥበብ እንዲሁም ከባህል ዘርፍ ከ15 ሺህ በላይ ወጣቶች የሥራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዷል፤ የሥራ ዕድሉ ከሚፈጠርላቸው ወጣቶች ውስጥም ከ12 ሺህ በላይ የሚሆኑት በቋሚነት ነው ብለዋል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## ሕዝባዊ በዓላት የአብሮነታችን መገለጫዎች ናቸው!

ሕዝባዊ እና ሃይማኖታዊ የአደባባይ ባህሎቻችን የእኛነታችን መገለጫ በዓለም ማኅበረሰብ ዘንድም የምንታወቀባቸው መለያችን ናቸው፡፡ ከቀናት በኋላ የምናከብራቸው የመስቀል ደመራና የኢሬቻ በዓላትም በሀገራችን በድምቀት ከሚከበሩ ሃይማኖታዊና ባህላዊ ክብረ በዓላት መካከል ዋነኞቹ ናቸው፡፡

የመስቀል በዓል ትውፊታዊም መንፈሳዊም ነው። በመስቀል በዓል የርስ በርስ የመተሳሰብ፣ የአብሮነት፣ የፍቅር፣ የሰላም መገለጫ ሲሆን፤ በሥራም ሆነ በሌላ አጋጣሚ ተራርቆ የቆየ ሁሉ የሚገናኝበት፣ ዘመድ ከዘመዱ የሚጠያየቅበት፣ የሚረዳዳበት እንዲሁም አዲስ ጎጆ የሚቀለስበት ጊዜ መሆኑ ልዩ ቦታ ይሰጠዋል።

በተመሳሳይ የኢሬቻም በዓል ስለአብሮነት የሚሰበክበት፤ አብሮነት ከንግግር ባለፈ በተግባር የሚኖርበት እርቅና ሰላም የሚሰበክበት የአብሮነታችን ማጠናከሪያ ገመድ ነው፡፡

ኢትዮጵያውያን ደስታና ችግሮችን በአብሮነት ያሳለፍንና የምናሳልፍ ሕዝቦች ነን። በታሪክ ከመቆራኘት ባለፈ የጋራ እሴቶች፣ ባህል እና አኗኗር ያለን ሕዝቦች መሆናችንንም የምንገልጸው በነዚህ በዓላት ነው፡፡

እነዚህ እሴቶች የመላው ኢትዮጵያውያን እሴቶች ናቸው፡፡ የኢትዮጵያውያን መገለጫ የሆነውን የአብሮነት እሴት በማጠናከር የሕዝብን አንድነት ማጽናት የቻሉ ናቸው፡፡ከእኛም አልፎ ለዓለም ሕዝብ ያስተዋወቁን ናቸው፡፡ ሁለቱ በዓላት ከጠንካራ ክረምት ወደ አዲስ ተስፋ በምንሸጋገርበት መስከረም ወር መከበራቸው ሁሌም የተለዩና በአዲስ መንፈስ አብሮነታችንን አጠንክረን ለመዝለቅ ዕድል ይሰጡናል፡፡

ሁለቱም በዓላት የአደባባይ በዓላት ከመሆናቸው ባሻገር በዩኔስኮ በማይዳሰሱ ቅርሶች የተመዘገቡ በመሆናቸው በተለይ ወደ መዲናችን አዲስ አበባ ከሁሉም የዓለማችን ክፍሎች የሚመጡ ቱሪስቶች እና ከአጎራባች ክልሎች በዓላቱን ለማክበር የሚመጡ ሰዎችን በፍቅር ተቀብለን በፍቅር መሸኘት ይጠበቅብናል፡፡

ኢትዮጵያ የበርካታ ባህላዊና ታሪካዊ ሀብት ባለቤት ብትሆንም እምቅ አቅሟን በተገቢው መንገድ ማልማትና ማስተዋወቅ ባለመቻላችን ከዘርፉ የምናገኘው ገቢ እንዳላደገ ይታወቃል፡፡ አንድነታችንን አጠናክረን እነዚህን ሀብቶቻችን ማልማት፣ መጠበቅና መንከባከብ አለብን። ይህ ደግሞ የቱሪዝም ዘርፍ እንዲነቃቃ ያደርገዋል። በተጨማሪም ለበርካታ ዜጎች የሥራ እድል መፍጠር ይቻላል።

እነዚህ ተዝቀው የማያልቁ ቱባ ባህሎቻችን የኢኮኖሚ ምንጭ ሆነው ለቀጣዩ ትውልድ እንዲሸጋገሩ ባህላዊ እሴቶቻችንን በደንብ አልምተን እንደ አንድ የቱሪዝም ገቢ ምንጭ በማድረግ ለሀገራዊ ብልጽግናችን መሠረት የምንጥልበት መሆን ይኖርባቸዋል።

ለዚህም እንደ መስቀል ደመራና ኢሬቻ ያሉ ቱባ ባህሎቻችን አከባበራቸው ሳይሸራረፍ ለትውልድ በማስተላለፍ ዘረኝነት፣ ጥላቻና ቂም በቀልን በማስወገድ የሀገራችንን ብልፅግና ለማረጋገጥ ሁሉም ዜጋ የድርሻውን ሊወጣ ይገባል።

ሁለቱም በዓላት የአደባባይ በዓላት እንደመሆናቸው እና በርካታ የማኅበረሰብ ክፍሎች የሚሳተፉባቸው ከመሆናቸው ባሻገር የሀገርን ገፅታ የሚገነቡ በመሆናቸው ለሰላምና ለፀጥታ ሁሉም ኃላፊነት አለበት፡፡ የመስቀል ደመራ እና የኢሬቻ በዓላትን ሃይማኖታዊ እና ባህላዊ እሴቶቻቸውን ሳይለቁ ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲተላለፉና በሰላም እንዲከበሩ በተለይም ወጣቶች ያለባቸው ኃላፊነት ትልቅ ነው፡፡

ስለሆነም መላው ኢትዮጵያዊ የመስቀል ደመራ እና የኢሬቻ በዓላት በድመቀት ሲከበሩ ሃይማኖታዊ እና ባህላዊ እሴቶቻቸውን ጠብቀው ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲተላለፉ እና በሰላም ተጀምረው እንዲጠናቀቁ ኃላፊነቱን ሊወጣ ይገባል፡፡ ለሰላም ቅድሚያ በመስጠት በዓላቱ በድምቀት እንዲከበሩ ወጣቶች በየአካባቢያችን ለሰላምና ፀጥታ አስፈላጊውን ትብብር ማድረግ ይኖርባቸዋል። ለዚህም ከፀጥታ አካላት እና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ሊሠሩ ይገባል፡፡ እነዚህ በዓላት በሕዝቦች መካከል ለዘመናት የዳበረውን የአብሮነት እሴት ለማስቀጠልና ትውልድ ለማስተላለፍ ጠቀሜታቸው የጎላ ነው።

በአዲሱ ዓመት ማግስት እነዚህን በዓላት ስናከብር ለአብሮነት ትኩረት በመስጠት እርስ በርስ ለመተባበር፣ ለመረዳዳት እና አንድነትን በማጠናከር መንፈስ ሊሆን ይገባል፡፡ ይህም በሠላምና በፍቅር የተሳሰረ ጠንካራ ማኅበረሰብ ለመፍጠር ጠቀሜታው የጎላ መሆኑም አብሮነትን ማጠናከርና እሴቱንም በትውልዱ ውስጥ በማስረጽ የተጀመረውን ሀገራዊና ሁለንተናዊ የብልጽግና ጉዞ ማፋጠን ይገባል!


## አዲስ ዘመን

ኢፕድ ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፦ epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፦ 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፦ ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የጥፋት ምንቸት ውጣ፤የልማት ምቸት ግባ

ይቤ ከደጃች.ውቤ

ያለንበት ወቅት አዲስ ዘመን የባተበት አዲስ ተስፋ የፈነጠቀበትና ይህንኑ ብሩህ ተስፋ የምንሰንቅበት ነው። ምንጊዜም አዲስ ዓመት ሲመጣ ሰዎች በጎ በጎውን ያልማሉ ተስፋም ያጭራሉ። ክረምት ወጥቶ፣ አሮጌው ዓመት አልፎ መስከረም የጠባበት ምድር በልምላሜ መስኩን የሚያለብስበት፣ በአደይ አበባው የምትዋብበት፣ ገበሬው በክረምቱ የዘራው ዘር ፍያሬያማ መሆኑን አውቆ አረሙን እየነቀለ ዘሩ አጨዳ እንዲደርስ ተስፋ የሚያደርግበት ነው።

መስከረም ክረምቱ አልፎ መስኩ በልምላሜ፣ በአሸንዳ፣ በእንግጫ (በኦሮሚፋ ቡቂሳ ይባላል) በአደይ አበባ ተውባ የምትታይበት ነው። በርዕሳችን የጥፋት ምንቸት ውጣ ፤ የልማት ምቾት ግባ ያልነውም ይህንኑ ተስፋን ሰንቀን ነው። በአዲሱ ዓመት መናቆርና መቃቃር እንዲቀር መፋቀርና መጣመር እንዲሰምር በመመኘት መሆኑ ይሰመርበት።

አዲስ ዓመት ሲመጣ ችቦ ሲለኮስ ሴቶች የጎመን ምንቸት ይውጣ የገንፎ ምንቸት ይምጣ (ይግባ) እንደሚሉ የደስታ ተክለወልድ ሐዲስ የአማርኛ መዝገብ ቃላት ይገልፃል። ምንቸት እንስራ ፣ማሰሮ መሳይ አነስ ያለ ሁለት ጆሮ ያለው ምግብ ማብሰያ ነው። በገጠር ክረምት ሲገባ ጎመን፣ ድንች የመሳሰሉ ምግቦች በብዛት የሚበስሉበት ነው። በተለይ በክረምቱ እንደጎመን ዓይነት ቅጠላ ቅጠሎች ሁነኛ ምግብ ማባያ ሆነው በገበታ ይቀርባሉ። ይህም ብርዱን ለመከላከል ያግዛል።

በተለይ በክረምት ጎመን በብዛት በገጠር በየጓሮው ስለሚበቅል ወጣወጥ ለመሥራት የተቸገሩ ሁሉ ከጓሮ በክረምቱ ዝናብ የበቀለውን ጎመናቸውን ቀንጥሰው ምግባቸውን ያዘጋጃሉ። ከዚሁ በተጨማሪ ገበሬው ከክረምቱ እርሻ መልስ እቤቱ የስንዴ ፣የበቆሎ፣ የባቄላ ንፍሮ በብዛት እየበላ ብርዱን የሚረሳበት የእርሻውን ድካም የሚያስታግስበት ነው።

> 2016 ዓ.ም የህዳሴ ግድብ አራተኛ የውሃ ሙሌት በስኬት የተጠናቀቀበት፤ አብዛኛው የዓባይ ግድብ ሥራ ፍሬ አፍርቶ ዜጋው ሁሉ ተስፋ የሰነቀበት ነው። ዜጋው ከጨለማው ክረምት እየወጣ እንዳለው ሁሉ የዓባይ ግድብም ከኢትዮጵያም አልፎ ለጎረቤቶች ጭምር የኤሌክትሪክ ብርሃን የሚሆንበት፤ የሀገራቱ የምጣኔ ሀብት ትስስሩ የበለጠ የሚጠናከርበት እንደሚሆን ይታመናል ፤ ሀገሪቱም የውጭ ምንዛሪ የምታፈራበት በዚህም ድህነትን ለመዋጋት ለጀመረችው ጥረት አቅም የምትገዛበት ነው

2016 ዓ.ም የህዳሴ ግድብ አራተኛ የውሃ ሙሌት በስኬት የተጠናቀቀበት፤ አብዛኛው የዓባይ ግድብ ሥራ ፍሬ አፍርቶ ዜጋው ሁሉ ተስፋ የሰነቀበት ነው። ዜጋው ከጨለማው ክረምት እየወጣ እንዳለው ሁሉ የዓባይ ግድብም ከኢትዮጵያም አልፎ ለጎረቤቶች ጭምር የኤሌክትሪክ ብርሃን የሚሆንበት፤ የሀገራቱን የምጣኔ ሀብት ትስስሩ የበለጠ የሚጠናከርበት እንደሚሆን ይታመናል ፤ ሀገሪቱም የውጭ ምንዛሪ የምታፈራበት በዚህም ድህነትን ለመዋጋት ለጀመረችው ጥረት አቅም የምትገዛበት ነው።

ስለ ዓባይ ግድብ ስናነሳ ወደ ኋላ ወደ ንጉሱ ዘመን ማቅናታችን አይቀርም። ንጉሡ / በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ /ዓባይን በመገደብ ለአንግሎ ኤጅብት፤ ማለትም በወቅቱ በእንግሊዝ ቅኝ ለነበረችው ግብፅና ሱዳን እናከራየዋለን የሚል ሃሳብ እንደነበራቸው። ይህንኑ እውን ለማድረግ የተለያዩ የውጭ ሀገር የጥናት ባለሙያዎችን በመጋበዝ በግድቡ ዙሪያ ጥናት ማስጠናታቸውን ሰነዶች ያስረዳሉ።

ንጉሡ ጥናቱን ቢያስጠኑም፤ለግንባታው የሚሆን ሀብት ብድርና እርዳታ ፈልገው ሊያገኙ አልቻሉም። ከዚህ የተነሳም « እኛ ዓባይን እንገድብ ብንል አቅም የለንም። የውጭ ሀገራት ደግሞ ዓባይን ለመገደብ እርዱን ብንል ግብጽን ላላማስቀየም ፈቃደኛ አይሆኑም ። ቀጣዩ ትውልድ ግን በራሱ ንዋይ(ገንዘብ) ይገነባዋል» በሚል ትንቢት መሰል ንግግር አድርገው ሥራው በይደር መቆየቱን መረጃዎች ያመላክታሉ።

ከ12 ዓመት በፊት ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ የዓባይን ግድብ ሰነዱ አቧራ አራግፈው ኢትዮጵያውያን በራሳቸው አቅም ግድቡን እንዲሰሩ መሠረት ጥለዋል፤ መሪዎች ሲለዋወጡ ግንባታው እንደ ዱላ ቅብብል ቀጥሎ ዛሬ በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ዘመን ግንባታው ወደ ፍጻሜ እያመራ ነው። አራተኛው የግድቡ የውሃ ሙሌት በስኬት ተከናውኗል።

ይህም ለሕዝቡ ትልቅ የአዲስ ዓመት ስጦታም ተደርጎ ተወስዷል።አዲሱን ዓመትም አድምቆታል።

በትምህርታችን ውሃ ሕይወት ነው ተብሎ ተደጋጋሚ ሲነገር እሰማ እንደነበር አስታውሳለሁ። በርግጥም ሰውን ጨምሮ እንስሳቱ አራዊቱ አዕዋፋቱ እፅዋቱ ውሃን ይሹታል፣ይጠጡታል ይጎነጩታል፣ ይተጣጠቡበታል፣ ይዋቡበታል ይዝናኑበታል፣ ይጽናኑበታል ይዋኙበታል፣ ይኖሩበታል (አዞንና ዓሣን ያስቧል)፤ይህን ስናስብ በርግጥም ውሃ ለሁሉም መሠረታዊ እንደሆነ እንረዳለን።

በኢትዮጵያ ካሉት 122 ቢሊዮን ሜትር ኩዩብ የገፀ ምድር ውሃ 70 በመቶ ዓባይ ወንዝ ተፋሰስ ላይ እንደሚገኝ መረጃዎች ያመለክታሉ። ከነባሩቹ ዘጠኝ ክልሎች ስድስቱ ለዓባይ የሚገብሩ ወንዞች አላቸው። ሀገሪቱ ካሉዋት በመስኖ ሊለሙ ከሚችሉ መሬቶች 2/3ኛው በዚሁ ተፋሰስ ውስጥ የሚገኝ ነው። ተፋሰሹ 40 ሚሊዮን ሕዝብ በዓባይ የሚኖር ፣ በሀገሪቱ የቆዳ ስፋት 37 በመቶ የሚሆነውን የሚሸፍን ጭምር ነው።

የግድቡ ግንባታ ኢትዮጵያ በምሥራቅ አፍሪካም ሆነ በአፍሪካ ደረጃ ያላት ተፅዕኖ ፈጣሪነት እንዲጎለብት አዎንታዊ ሚና እንደሚኖረውም ይታመናል ። ለሀገሪቱም ብሎም ለጎረቤት ሀገሮች ብርሃን ፈንጣቂ የዘመኑ ትልቅ ስጦታ ነው። በበጎ ህሊና ማየት ከተቻለ ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በዙሪያዋ ላሉት ለጎረቤት ሀገሮች የግድቡ የመጨረሻ የውሃ ሙሌት የምሥራች የሚሆን ነው።

በርግጥም «ድር ቢያብር አንበሳ ያስር» እንደሚባለው ሀገርኛ ብሂል ኢትዮጵያውያን የዓባይን ግድብ በመገንባት ከድህነት የሚወጡበትን ፣የጠላት ምንጭ የሚያደርቅበትን፣ የውጭ ምንዛሪ የሚፈጥሩበትን፣ ድህነት የሚዋጉበትን ጥልቅ ሥራ ሠርተዋል። ይህም መጪው ጊዜ የጥፋት ምንቸት ውጣ የልማት ምቾት ግባ የምንልበት ለመሆኑ አንድ ማሳያ ነው።

ዜና



## «የመውሊድ በዓልን ኢስላማዊ ሥርዓት በጠበቀና አብሮነትን በሚያጠናክር መንገድ ማክበር ይገባል»

- ዶክተር ሼህ አቡበከር ሱሌይማን

**አማን ረሺድ**

አዲስ አበባ፡- አንድ ሺህ 498ኛውን የነብዩ ሙሐመድ (ሠ.ዐ.ወ) መውሊድ በዓልን ስናከብር ኢስላማዊ ሥርዓትን በጠበቀና አብሮነትን በማጠናከር ሊሆን እንደሚገባ የእስልምና ሃይማኖት መምህሩ ዶክተር ሼህ አቡበከር ሱሌይማን ተናገሩ።

ዶክተር ሼህ አቡበከር ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር በነበራቸው ቆይታ እንደገለጹት፤ በዓሉ የሙስሊሙን ብሎም የሕዝቦችን አንድነት ለማጠናከር፣ ፍቅር እንዲጎለብትና መልካም ሥራዎች እንዲጠናከሩ በማድረግ ጉልህ ሚና አለው፡፡

የመውሊድ በዓል ከነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ጋር ያለንን ቅርበት የምናስታውስበትና ታሪካቸውን ለትውልድ የምናስተላልፍበት ነው ሲሉ መምህሩ አስገንዝበዋል።

መሰል በዓላቶችንና መድረኮች በተራ ነገሮች ማሳለፍ አይገባም ያሉት ዶክተር ሼህ አቡበከር፤ ሕዝበ ሙስሊሙ ከዚህ በተለየ መንገድ ለሀገር ጥቅም በሚያስገኝ መልኩ ሊያከብረው ይገባል ብለዋል፡፡

ዶክተር ሼህ አቡበከር እንዳመላከቱት፤ በዓሉን ስናከብር የነብዩ ሙሐመድን (ሠ.ዐ.ወ)መልካም ስብዕና፣ ቸርነት፣ ደግነት፣ ለሰው አሳቢነትና ሩህሩህነት በመላበስና በመተግበር ሊሆን ይገባል።

ከመጥፎ አስተሳሰብ ወደ መልካም መንገድ በመጋበዝ የተሻለ ሀገር እንዲኖረንና የተሻለ ዕድገት ደረጃ ላይ እንድንደርስ አንዳችን ለሌላችን ድጋፍ መሆን ይኖርብናል ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል።

መውሊድ የነብይ መወለድ ክብረ በዓል ብቻ ሳይሆን ቀድሞ የነበሩት የእስልምና ዕውነታዎች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ ያደረገና ከኢትዮጵያ ጋር ከፍተኛ ቁርኝት ያለው በዓል መሆኑን አንስተዋል።

ኢትዮጵያ የነብዩ መሐመድ ተከታዮች ችግር ባጋጠማቸው ጊዜ መልዕክታቸውን ይዘው ሲመጡ ተቀብላ ያስተናገደች ሀገር በመሆኗ ለውለታዋ በቅዱስ ቁራን ላይ ከ30 በላይ ቃላት ተጽፎ ይገኛል፤ ይህን እንግዳ ተቀባይነትና መረዳዳት ማጠናከር ይገባል ብለዋል፡፡

የነብዩ ሙሐመድ (ሠ.ዐ.ወ) ለተቸገሩ ሰዎች ይረዱና ያዝኑ እንደነበር አውስተው፤ የተቸገሩትን በመርዳት፣ በማገዝ፣ በመተዛዘንና የእርሳቸውን ፈልግ በመከተል በዓሉን በደስታ ማክበር እንደሚገባ ገልጸዋል።

ሕዝበ ሙስሊሙ በዓሉን ሲያከብር ብቻውን ሳይሆን ከተቸገሩት ሰዎች ጋር ጠጋ ብሎ ችግራቸውንና ጭንቀታቸውን በመጋራትና ሸክማቸውን በማቅለል መሆን እንዳለበት ጠቁመው፤ በጎ ማድረጉ የሃይማኖቱ አስተምሮና ግዴታ መሆኑን ማወቅ ይገባል ሲሉ ተናግረዋል።

የነብዩ ሙሐመድ (ሠ.ዐ.ወ) መወለድ ለሰዎች የሐቅ፣ የመልካም ሥነ-ምግባርና ስብዕና፣ የመረዳዳት፣ የፍቅር፣ የእውነተኛ መንገድ ፣ መተዛዘን፣ መደጋገፍ፣ አብሮነትና አንድ የመሆን ምልክት ነው ያሉት ዶክተር ሼህ አቡበከር፣ ቀናነትንና ፍቅርን በማሳየት በዓሉን ማክበር እንደሚገባ ተናግረዋል።

ከጎረቤት ጋር ጥሩ ጸባይንና መልካም ሥነ-ምግባርን በመለዋወጥ፣ ለእስልምናና ሌሎች ሃይማኖቶች ተከታይ ለሆኑ ሰዎች ሁሉ መልካም በመሆን በዓሉ ሊከበር እንደሚገባ ጠቁመዋል።

በዓሉን ስናከብርም አሁን ያለንበትን ሀገራዊ ሁኔታም ሳንዘነጋ ከችግሩ እንድንወጣ ጸሎት ማድረስና የተፈናቀሉትን መጠየቅ ይጠበቅብናል ብለዋል።

ሙስሊሙ ማኅበረሰቡ ከነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) አስተምሮ ባለመራቅ የእርሳቸውን በጎ ተግባራት አዘውትሮ መተግበርና ለሀገሪቱና ለዓለም ችግሮች የመፍትሔ አካል መሆን ይገባል ሲሉ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

# ክልሉ በመስቀል በዓል ከአንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን በላይ ጎብኚዎች ለማስተናገድ ተዘጋጅቷል


**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- በመስቀል በዓል ከአንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን በላይ የሀገር ውስጥ ጎብኚዎችን ለማስተናገድ ዝግጅት ማድረጉን የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ባህልና ቱሪዝም ቢሮ አስታወቀ፡፡

የባህልና ቱሪዝም ቢሮው ምክትል ኃላፊ አቶ ኑሪ ከድር ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ ለመስቀል በዓል ከአንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን በላይ የሀገር ውስጥ ጎብኚዎች ክልሉን ይጎበኛሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡

እንደ አቶ ኑሪ ገለጻ፤ በዓሉ ባህላዊና ሃይማኖታዊ እሴቱን ጠብቆ እንዲከበር ከሰላምና ጸጥታ፣ በመንገድና ትራንስፖርት፣ በመሠረተ ልማት ዘርፍ እንዲሁም በሌሎች ዘርፎች የተለያዩ ግብረ ኃይሎችን በማዋቀር ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር እየተሠራ ይገኛል፡፡

በመስቀል በዓል በክልሉ የሚገኙ ዓለም አቀፍ ቅርሶችና የቱሪስት መስህቦችን ለማስተዋወቅ ሰፊ ጥረት ይደረጋል ያሉት አቶ ኑሪ፤ በዓሉ የክልሉን የቱሪዝም እንቅስቃሴ ለማነቃቃት



**አቶ ኑሪ ከድር**

እንደሚያግዝም ተናግረዋል፡፡

በርካታ ጎብኚዎች ወደክልሉ መምጣታቸው ኢኮኖሚውን ከመደገፍና ማኅበራዊ መስተጋብር ከማጠናከር አኳያ ጉልህ ሚና እንደሚኖረው አቶ ኑሪ አስረድተዋል።

አቶ ኑሪ እንዳመለከቱት፤ የመስቀል በዓል በክልሉ በሚገኙ ብሔር ብሔረሰቦች ዘንድ የዘመን መለወጫ በዓል ጋር ተያይዞ ከአሁኑ ጀምሮ በድምቀት እየተከበረ ይገኛል።

በዓሉ ሰፊ ባህላዊና ሃይማኖታዊ እሴት ያለው በመሆኑ በዓለም አቀፍ ደረጃ ለማስተዋወቅ የሚረዱ ጥረቶች እየተከናወኑ ይገኛል።

በዓሉ በሰላም እንዲከበር በቂ ዝግጅት ሲደረግ ቆይቷል ያሉት ምክትል ቢሮ ኃላፊው፤ ሰፊ ቁጥር ያላቸው የአካባቢው ተወላጆች በበዓሉ ለመታደም ወደ ክልሉ የሚመጡ በመሆኑ በትራንስፖርት ዘርፍ የታሪፍ ጭማሪ እንዳይደረግ ከሚመለከተው ባለ ድርሻ አካል ጋር እየተሠራ ነው ብለዋል፡፡

የመስቀል በዓል የመረዳዳትና የአብሮነት እሴት ጎልቶ የሚታይበት ትልቅ ባህላዊና ሃይማኖታዊ በዓል በመሆኑ ለሰላምና ለአንድነት ያለው ፋይዳ የጎላ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

የመስቀል በዓል የመተሳሰብና የፍቅር በዓል ሆኖ በደስታ ይከበራል ያሉት አቶ ኑሪ ወደክልሉ የሚመጡ ጎብኚዎችን በተሻለ የእንግዳ ተቀባይነት ለማስተናገድ አስፈላጊው ጥረት እንደሚደረግ አስታውቀዋል።

# ወጣቶች በሀገራዊ ምክክሩ በንቃት እንዲሳተፉ አስፈላጊው ጥረት ይደረጋል

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- ወጣቶች በሀገራዊ ምክክሩ በንቃት እንዲሳተፉና ውጤታማ ምክክር እንዲደረግ አስፈላጊውን ጥረት እንደሚያደርግ የኢትዮጵያ ወጣቶች ምክር ቤት አስታወቀ፡፡

የምክር ቤቱ ፕሬዚዳንት ወጣት ፉአድ ገና ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በሀገሪቱ ዘላቂ ሰላም እንዲሰፍን የወጣቶች ድርሻ ከፍተኛ በመሆኑ በሀገራዊ ምክክሩ በንቃት ሊሳተፉ ይገባል፡፡

እንደ ወጣት ፉአድ ገለጻ፤ ወጣቶች በዘላቂ ሀገራዊ ሰላም ግንባታ ላይ ያላቸው ሚና ጉልህ በመሆኑ ለሀገራዊ ምክክሩ ውጤታማነት አስፈላጊ ናቸው።

ወጣቶች ያልተካተቱበት ሰላም ሆነ የልማት ሥራ ውጤታማ ሊሆን አይችልም ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ በኢትዮጵያ ያለውን 41 ሚሊዮን ወጣት በሰላም ግንባታ ሂደት በአግባቡ መጠቀም ያስፈልጋል ብለዋል፡፡

ወጣቶች ለዘላቂ ሰላም በሚካሄዱ መድረኮች ላይ በንቃት መሳተፍ እንዳለባቸው በመግለጽ በሀገራዊ ምክክሩ አጀንዳዎችን በመስጠት በንቃት ሊሳተፉ ይገባል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

በሀገራዊ ምክክሩ ትውልዱን በሚመለከቱ የመወያያ አጀንዳዎች ላይ ወጣቶች በንቃት ተሳትፎ ማድረግ እንዳለባቸው የገለጹት ፕሬዚዳንቱ፤ ምክር ቤቱ ከሚመለከታቸው አካላትና ከብሔራዊ ምክክር ኮሚሽኑ ጋር በመሆን የወጣቶች ተሳትፎን ለማጎልበት እየተሠራ እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡


ወጣቱን በተሻለ መንገድ የሚሳተፍባቸው የምክክር መድረኮች፣ የሽግግር ፍትህና የሰላምና ልማት ሥራዎች ውጤታማ የመሆን ዕድላቸው ሰፊ ነው ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤



**ወጣት ፉአድ ገና**



**ወጣት ቤተልሔም በኃይሉ**



**ወጣት ሱራፌል ደበበ**

ሁሉም ወጣቶች በሀገራዊ ምክክር መድረኮች ሊቀርቡ የሚገባቸውን አጀንዳዎች በመጠቆምና ተሳታፊዎች በመምረጥ ሂደት በንቃት እንዲሳተፉ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

ወጣት ቤተልሔም በኃይሉ በበኩሏ፤ የሰላም ጉዳይ ከትንሽ እስከ ትልቁ የሚመለከተው በመሆኑ ወጣቱ በሀገራዊ የምክክር መድረኮች ላይ ጠንካራ ሃሳቦችን ይዞ ሊሳተፍ ይገባል፡፡

ወጣቱ ለሰላምና ለሀገራዊ ምክክር ያለውን ሚና መረዳትና መጠቀም ይኖርበታል ያለችው ወጣት ቤተልሔም፤ ከራስ ጀምሮ የአካባቢንና የሀገር ሰላምን ለመጠበቅ በሚያስችሉ ሀገራዊ የውይይት መድረኮች ላይ መሳተፍ ይኖርብናል ብላለች።

የሰላም እጦት ወጣቱን ጨምሮ የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ላይ ዘርፈ ብዙ ችግሮችን እያስከተለ መሆኑን በመጠቆም፤ በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የሚታየውን የሰላም እጦት በመቅረፍ ወደ ነበረበት መረጋጋት ለመመለስ የወጣቱ ድርሻ ከፍተኛ መሆኑን አመላክታለች።

ወጣቱ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽኑን ጨምሮ ስለ ሰላም ከሚሰብኩና ከሚሠሩ አካላት ጎን በመቆም ለሀገር ዕድገት የበኩሉን ድርሻ ሊወጣ እንደሚገባ ገልጻለች፡፡

ወጣት ሱራፌል ደበበ በበኩሉ እንደተናገረው፤ ሰላም ለተወሰኑ አካላት ብቻ የሚተው ሳይሆን የሁሉንም ኅብረተሰብ ርብርብ የሚጠይቅ በመሆኑ ወጣቶች የድርሻቸውን መወጣት አለባቸው፡፡

ወጣቱ እንደ ሀገር የጋራ በሆኑ ጉዳዮች ላይ መወያየትና መግባባት ይኖርበታል ያለው ወጣት ሱራፌል፤ በተለይም በጋራ ተቀምጦ መወያየትን ባህል ማድረግ ያስፈልጋል ሲል ተናግሯል።

እንደ ሀገር የሀገራዊ ምክክሩ አንድነትን ለማምጣት የሚያስችል በመሆኑን ወጣቱ በሀገሪቱ ወሳኝ ጉዳዮች ላይ በመግባባት ለዘላቂ ሰላም የድርሻውን መወጣት እንደሚኖርበት ወጣት ሱራፌል አስገንዝቧል።

## «የዓለም የጸጥታ ዘርፍ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

የምርጫ ሳይሆን ፍጹም አስፈላጊ ጉዳይ እንደሆነ እንደምታምን ተናግረዋል።

የጸጥታው ምክር ቤት አሳታፊ እና አካታች ሆኖ መዋቀር ያሻዋል ያሉት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ በተለይም በምክር ቤቱ ለአፍሪካ ቋሚ መቀመጫ የመስጠት ጉዳይ ፖለቲካዊ፣ ሞራላዊና ፍትሐዊ ውሳኔ የመስጠት ጉዳይ መሆኑን አንስተዋል።

የመንግሥታቱ ድርጅት ለአፍሪካ የሰላም ተልዕኮ በቂ የፋይናንስ ድጋፍ መስጠት እና ለሀገራት የሕግ ማስከበር ሥራዎች ስኬታማነት አስፈላጊውን የአቅም ግንባታ ድጋፍ ሊያደርግ እንደሚገባ ተናግረዋል።

በተጨማሪም የተናጠላዊ ማዕቀብ እና ተገቢ ያልሆኑ ኢኮኖሚያዊ እርምጃዎች የመንግሥታቱን ድርጅት መርህና አሠራር የሚጣረሱ በመሆኑ ኢትዮጵያ በታዳጊ ሀገራት ላይ የሚጣሉ መሰል እርምጃዎች ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ሊነሱ ይገባል ብላ እንደምታምን አንስተዋል።

በሉዓላዊ ሀገራት መካከል የሚፈጠሩ ፖለቲካዊ ልዩነቶችን በተናጠላዊ ማዕቀብ ሳይሆን በሰላማዊና በዴሞክራሲያዊ መንገድ በውይይት መፍታት አማራጭ መሆን እንዳለበትም ነው ያነሱት። ኢትዮጵያና መሰል ታዳጊ ሀገራት የመንግሥታቱ ድርጅት አጠቃላይ ቅርጽ መስተካከል እንዳለበት ጥሪ ሲያቀርቡ መቆየታቸውን አስታውሰዋል።

አሁንም ይበልጥ አካታች፣ ውጤታማና ለብዝሀነት የተመቸ እንዲሁም ታዳጊ ሀገራትን ታሳቢ ያደረገ አሠራር መዘርጋት እንዳለበት ገልጸው፤ ኢትዮጵያ የተቀላቀለችበት 'ብሪክስ' በዚህ ረገድ ትልቅ ምሳሌ መሆኑን አንስተዋል።

በሌላ በኩል በዓለም አቀፍ ደረጃ ለልማት ግቦች ስኬት የፋይናንስ አቅርቦት ቢኖርም በታዳጊ ሀገራት ግን ፍትሐዊነት የጎደለው በመሆኑ ይህንን ለማስተካከል አዲስ ፖለቲካዊ ቁርጠኝነት እና ዓለም አቀፍ ትብብር ይፈልጋል ብለዋል።

ኢትዮጵያ ሰላማዊና የበለጸገ ማኅበረሰብ ለመገንባት የልማት ግቦችን ቀርጻ እየሠራች መሆኗን ጠቅሰው፤ ለዚህ ግን አዲስ የሆነ አካታች ዓለም አቀፍ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ሥርዓት እንደሚያስፈልግ ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ መንግሥት ለሰላምና ዴሞክራሲ መስፈን ቁርጠኛ መሆኑን ገልጸው፤ በሰሜን ኢትዮጵያ ተከስቶ የነበረውን ችግር የአፍሪካን ችግር በአፍሪካ የመፍታት መርህ በፕሪቶሪያ በተደረሰው የሰላም ስምምነት መፍታት መቻሉን ለአብነት አንስተዋል።

ስምምነቱ በመልካም አፈጻጸም ላይ መሆኑን ጠቀሰው፣ ከሰላም ስምምነቱ ባሻገርም በሀገሪቱ ዘላቂ ሰላም ለማስፈን፣ ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ፣ የሽግግር ፍትህ ለማስፈን እየሠራ መሆኑን ተናግረዋል። ከዚህም ባሻገር የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን በማቋቋም ለኢትዮጵያዊውን የተሻለ እና ብሩህ ነገ ለመገንባት በትኩረት እየተሠራ መሆኑን ተናግረዋል ሲል ኢዜአ ዘግቧል።

## በ80 ቢሊዮን ብር...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ዘመናዊ ማሽን ወደ ሀገር ውስጥ አስገብቷል ሲሉ ገልጸዋል።

ማሽኑ የሊትየም ምርትን ፕሮሰስ በማድረግ እሴት ጨምሮ ለውጭ ገበያ ያቀርባል ያሉት ሼህ ዓሊ፤ ኩባንያው በሊትየም ምርት ሀገሪቱ ወደ ላቀ ደረጃ እንድትደርስ ያደርጋል ብለዋል። በቀጣይ ምዕራፍም ግዙፍ ማሽኖች ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት በሂደት ላይ መሆኑን አብራርተዋል።

ቀንጢቻ ማይኒንግ በውጭ ሀገር እና በኢትዮጵያ ባለሀብቶች የተቋቋመ እና በማዕድን ማውጣት ሥራ ላይ ያተኮረ ኩባንያ መሆኑን ጠቅሰው፤ ግንባታው ሙሉ ለሙሉ ሲጠናቀቅ ከ1000 በላይ ለሚሆኑ ዜጎች የሥራ ዕድል ይፈጥራል ያሉት ሼህ ዓሊ፤ ዘርፉ በተለይም በውጭ ምንዛሪ ግኝት ለሀገሪቱ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንደሚኖረው ተናግረዋል።

በርካታ ሀገራት ያደጉት ማዕድንን ተጠቅመው መሆኑን የጠቀሱት ሼህ ዓሊ፤ ኢትዮጵያም ዕምቅ የሆነውን የማዕድን ሀብት በመጠቀም ማደግ እንደምትችል ገልፀዋል። ለዚህም መንግሥትን ጨምሮ እያንዳንዱ ዜጋ ትልቅ ኃላፊነት አለበት ብለዋል።

እንደ ሼህ ዓሊ ሁሴን ገለፃ፤ ሀገሪቱ ከማዕድን በተጨማሪ የነዳጅ ሀብት ያላት መሆኑንና በቀጣይም በነዳጅ ሀብት ልማት ለመሰማራት ዕቅድ ያላቸው መሆኑንም አመላክተዋል።

# ተስፋ ሰጪዎቹ የክልሉ እምቅ ሀብቶች- ቡና፣ ሻይና ቅመማ ቅመም

**ፍሬሕይወት አወቀ**

የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል በተፈጥሮ ሀብት የታደለ ክልል ስለመሆኑ በስፋት ይነገራል። ክልሉ በተፈጥሮ ሃብት የታደለ እንደመሆኑ በርካታ የሰብል ምርቶችን ጨምሮ፤ አትክልትና ፍራፍሬ፣ የቅባት እህሎች እንዲሁም ቡና ሻይና ቅመማ ቅመም በስፋት ይመረታል።

አቶ በላይ አጁአብ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል ቡና፣ ሻይና ቅመማ ቅመም ዘርፍ ዋና ዳይሬክተርና የልማትና ጥበቃ ዘርፍ ኃላፊ ናቸው። እሳቸው እንደሚገልጹት፣ ክልሉ በተፈጥሮ የታደለና ስነምህዳሩም ለበርካታ የሰብል፣ የአዝዕርትና የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች የተመቸ ነው። በተለይም በቡና፣ በሻይና በቅመማ ቅመም ምርት ክልሉ ዕምቅ አቅም ያለው ሲሆን ለውጭ ምንዛሪ ግኘት ከፍተኛ አስተዋፅኦ የሚያበረክተው ቡና በክልሉ በስፋት ይመረታል። 560 ሺ ሄክታር መሬት በቡና የተሸፈነ ሲሆን፤ ከ88 ሺ 300 ሄክታር በላይ መሬት ደግሞ በቅመማ ቅመም እንዲሁም ሁለት ሺ 776 ሄክታር መሬት በሻይ ልማት ተሸፍኗል።

ክልሉ ለቡና፣ ለቅመማ ቅመምና ለሻይ ምርቶች ካለው የስነ ምህዳር ምቹነት አንጻር በክልሉ ከሚገኙ ስድስት ዞኖች መካከል አራቱ ቡናን በተለየ መንገድ ስፔሻላይዝ የሚያደርጉና ዋና ሰብላቸው አድርገው የሚያለሙ እንደሆኑ የሚናገሩት አቶ በላይ፤ በዘርፉ ሰፊ ሥራ እየተሠራ እንደሚገኝ ያስረዳሉ። እሳቸው እንደሚሉት፤ በክልሉ ከሚገኘው ሶስት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ህዝብ ውስጥ ከግማሽ በመቶ የሚበልጠው በቡና፣ በቅመማ ቅመምና በሻይ ምርቶች ልማት ላይ የሚሳተፍ ነው።

በክልሉ የቡና፣ የቅመማ ቅመምና የሻይ ምርት በሰፊው መመረት ብቻ ሳይሆን የሚመረተውን ምርት በጥራት በማምረትና ምርትና ምርታማነትን የማሳደግ ሥራ በመሥራት ወደ ማዕከላዊ ገበያ እንዲሁም ወደ ውጭ ገበያ ይላካል። ይህም ለአገሪቱ የውጭ ምንዛሪ ግኘት አይነተኛ አስተዋጽኦ እያበረከተ ሲሆን፤ በተለይም የቡናን ምርትና ምርታማነት በማሳደግ እንዲሁም በጥራት በማምረት አገራዊ የውጭ ምንዛሪ ግኘትን ለማሳደግና ዘርፉን እንዲደግፍ ታቅዶ እየተሠራ ስለመሆኑ አስረድተዋል።

እሳቸው እንዳሉት ፤ በ2015 በጀት ዓመት ክልሉ 64 ነጥብ አምስት ሺ ቶን የቡና ምርት ለመሰብሰብና ለማዕከላዊ ገበያ ለማቅረብ ባቀደው መሰረት ዕቅዱን ለማሳካት ሰፋፊ ሥራዎችን ሲሰራ ቆይቷል። ለአብነትም ለባለሙያዎች ስልጠና የመስጠት እና ከአቅራቢዎች ጋር ምክክር በማድረግ የኢንዱስትሪ ባለቤቶች ወደ ሥራ እንዲገቡ የማድረግ ሥራ ተሰርቷል። በዚህም 42 ሺ ቶን ቡና ለገበያ በማቅረብ የዕቅዱን 65 በመቶ ማሳካት ተችሏል።

ክልሉ በበጀት ዓመቱ 47 ሺ ቶን የቅመማ ቅመም ምርት በማምረት ወደ ማዕከላዊ ገበያ ለማቅረብ አቅዶ፣ 43 ሺ ቶን ምርት ሰብስቦ ለማዕከላዊ ገበያ ማቅረብ ችሏል። በዚህም የዕቅዱን 90 ነጥብ ዘጠኝ በመቶ በማሳካት በዘርፉ ከተያዘው ግብ አንጻር ከቡናና ሻይ የተሻለ አፈጻጸም ማስመዝገብ እንደቻለ ተናግረዋል። በሻይ ልማት ዘርፍ ካለፈው ጊዜ የተሻለ እንቅስቃሴ ስለመኖሩ ያነሱት አቶ በላይ፤ በበጀት ዓመቱ ሰባት ሺ ቶን የሻይ ምርት ለማቅረብ ታቅዶ፤ ከስደስት ሺ ቶን በላይ በማቅረብ የዕቅዱን 89 በመቶ ማሳካት ስለመቻሉ ነው የገለጹት።

በበጀት ዓመቱ በክልሉ የተመዘገበው የቡና ምርት መጠን ዝቅተኛ እንደሆነ ያነሱት አቶ በላይ፤ በተለይም በ2014 ዓ.ም ከነበረው የምርት መጠን (64 ሺ ቶን) ጋር ሲነጻጸር በ35 በመቶ ቀንሷል። ይህም በተለያዩ ችግሮች ምክንያት የተከሰተ እንደሆነ ያስረዳሉ።

አቶ በላይ እንደሚሉት፤ በክልሉ የቡና ምርት መቀነስ ተስተውሏል። ‹‹አንድ የቡና ዛፍ በተከታታይ ዓመት ጥሩ ምርት ከሰጠ በቀጣይ ዓመት በተወሰነ መጠን የምርት መቀነስ ያጋጥማል። ይህም ተፈጥሯዊ ነው። ነገር ግን



አቶ በላይ አጁአብ

> ክልሉ በበጀት ዓመቱ 47 ሺ ቶን የቅመማ ቅመም ምርት በማምረት ወደ ማዕከላዊ ገበያ ለማቅረብ አቅዶ፣ 43 ሺ ቶን ምርት ሰብስቦ ለማዕከላዊ ገበያ ማቅረብ ችሏል። በዚህም የዕቅዱን 90 ነጥብ ዘጠኝ በመቶ በማሳካት በዘርፉ ከተያዘው ግብ አንጻር ከቡናና ሻይ የተሻለ አፈጻጸም አስመዝግቧል

ከዚህ ባለፈ የክልሉ የቡና እንክብካቤ ሥራ ጠንካራ ባለመሆኑ የተፈጠረ ነው። ምክንያቱም መንታ የወለደች እናት ጥሩ ቀለብ እንደሚያስፈልጋት ሁሉ፣ በተለይም ጥሩ ምርት ለሚሰጠው ቡና የተሻለ እንክብካቤ በማድረግ ምርትና ምርማነትን ሊያሳድጉ የሚችሉ እንደ ኮምፖስትና ብስባሽ ያሉትን በመስጠት፣ በአረምና ኩትኳቶ ሥራው ላይ ተከታታይነት ያለው ስራ በመስራት በኩል ደካማ አፈጻጸም ነበር›› በማለት ለቡና ምርት መቀነስ አንዱ ምክንያት እንደሆነ በግምገማ መለየት መቻላቸውን ተናግረዋል።

ሌላው ከፍተኛ መጠን ያለው ቡና ወደ ገበያ መውጣት ያልቻለበት ምክንያት ዓለም አቀፍ የቡና ዋጋ ከመውረድ ጋር ተያይዞ እንደሆነ ያነሱት አቶ በላይ፤ ይህም እንደ ሀገር ካሳደረው ተጽዕኖ ባለፈ በክልሉም ከፍተኛ ተጽዕኖ ማሳደሩን ገልጸዋል። በመሆኑም በክልሉ የሚገኙ ቡና አቅራቢ ነጋዴዎችና አርሶ አደሩም ጭምር ዓለም አቀፍ የቡና ዋጋ መውረዱን ተከትሎ ዋጋው ሲሻሻል ይዞ ለመውጣት በሚል ወቅቱ የሰጠውን ቡና እንኳን ወደ ገበያ ለማውጣት ፈቃደኛ ባለመሆን በቤቱ እንዳስቀመጠ ነው የተናገሩት። በዚህም በርካታ መጠን ያለው ቡና በክምችት ደረጃ መኖሩን ተዘዋውረው መመልከት እንደቻሉ ነው የታዘቡት። በሌሎች ተጨማሪ ምክንያቶች ጭምር ባለፈው በጀት ዓመት ክልሉ በመጠን ያነሰና የቡና ምርት በሚፈለገው ልክ ለገበያ ማቅረብ አለመቻሉን አስረድተዋል።

የቅመማ ቅመም ምርትን አስመልክቶ አቶ በላይ ሲገልጹ፤ ክልሉ ከቅመማ ቅመም ምርት የተሻለ ምርት ማግኘት እንደተቻለ አንስተው፤ ዘርፉ የህግ ማዕቀፍ የሌለው በመሆኑ የተለያዩ ችግሮች ገጥመዋል። ይህም ምርቱን ከባዕድ ነገር ጋር የመቀላቀልና ገበያ ላይ ማቅረብ አንዱ ሲሆን፤ ይህን ለመቆጣጠር የሚያስችል የህግ ማዕቀፍ አለመኖሩ ችግር ባለበት ሁኔታ ከምርት አቅርቦት አንጻር የተሻለ ምርት የተመረተበትና ወደ ማዕከላዊ ገበያ የቀረበበት አግባብ ስለመኖሩ አስረድተዋል።

በክልሉ በዋናነት ከሚመረቱና ውድ ከሆኑ የቅመማ ቅመም ምርቶች መካከል ኮረሪማ፣ ሄል፣ ቁንዶ በርበሬ፣ ጥምዝ፣ ጠረፍ፣ ሮዝመሪ፣ ሎሚናት፣ ዝንጅብልና ሌሎችም ይገኙበታል ያሉት አቶ በላይ፤ ክልሉ ለቅመማ ቅመም ምርቶች በተለይም ኮረሪማን ጨምሮ የተለያዩ ውድ የሆኑ የደጋ ቅመሞችን ለማምረት እጅግ በጣም ምቹና ሰፊ አቅም ያለው በመሆኑ በዘርፉ መሳተፍ የሚፈልጉ ባለሃብቶች ልማቱን በማስፋፋትም ሆነ በምርቱ ላይ እሴት በመጨመርና በማቀነባበር በማስፋትም ለመሳተፍ የሚፈልግ ማንኛውም አካል ወደ ክልሉ ቢመጣ የሚቀበሉ መሆኑን ገልጸው፤ ባለሃብቱም ውጤታማ መሆን የሚችል እንደሆነ አመላክተዋል።

‹‹ክልሉ በቅመማ ቅመም ዘርፍ የዕቅዱን መቶ በመቶ ማሳካት ያልቻለው፤ በዘርፉ ከፍተኛ የሆነ የህገወጥ ንግድ ዝውውር በመኖሩ ነው›› ያሉት አቶ በላይ፤ ውድ ዋጋ ያላቸው የቅመማ ቅመም ምርቶች ለአብነትም ኮረሪማ፣ ሄልና ቁንዶ በርበሬ እንደሆኑ ጠቅሰው፤ በእነዚህ የቅመማ ቅመም የሰብል ምርቶች ላይ ከፍተኛ የሆነ የህገወጥ የንግድ ዝውውር አለ ብለዋል። ከምርት ጥራቱ ጋር ተያይዞም በአፈርና በአመድ በማሸት ጥራቱን የመቀነስ ተግባራት ስለመኖሩ አመላክተው፤ ለዚህም በቀጣይ ተግባራዊ በሚሆነው የህግ ማዕቀፍ ችግሩን ለመከላከል ጥረት የሚያደርግ ይሆናል። በዚህም ህገወጥ ንግድ ላይ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግና ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ በቀጣይ በቡና፣ በቅመማ ቅመምና በሻይ ዘርፍ የተሻለ የምርት መጠን ለማቅረብ በትኩረት የሚሠራ ይሆናል ብለዋል።

የሻይ ምርትን በተመለከተ በተለይም በከፋና በሸካ ዞን በሁለት የልማት ድርጅቶች በስፋት እየለማ መሆኑን የጠቀሱት አቶ በላይ፤ የሻይ ምርቱ ውሽውሽ እና ኢስት አፍሪካ በተባሉ የልማት ድርጅቶች እየለማ ያለ መሆኑን ጠቅሰዋል። በእነዚህ የልማት ድርጅቶች ዙሪያ የሚገኙ አርሶ አደሮች እያለሙ ለልማት ድርጅቶቹ የሚያቀርቡበት ሂደት መኖሩን ገልጸው፤ ነገር ግን የሽፋኑን መጠን ለማስፋት ማነቆ የሆኑ ችግሮች ስለመኖራቸው አንስተው ባለፈው ዓመት የሻይ የምርት ሽፋንን ወደ 27 ሄክታር ተጨማሪ የሻይ ልማት ለማሳደግ ታቅዶ አምስት ሄክታር ሽፋን ብቻ ማሳደግ መቻሉን ነው የገለጹት።


እሳቸው እንዳሉት፤ ለዚህም በርካታ ማነቆዎች ስለመኖራቸው ነው ያነሱት። በዋናነት ምርቱ በአርሶ አደሩ ጭምር እንዳይሰፋ ያደረገው በክልሉ በቂ የኢንዱስትሪዎች ያለመኖር ነው። የልማት ድርጅቶች ብቸኛ በመሆናቸውና ተወዳዳሪና ተፎካካሪ ድርጅቶች የሌላቸው በመሆናቸው የሻይ ምርቱን ከአርሶ አደሩ የሚገዙት በዝቅተኛ ዋጋ ነው። ይህም አርሶ አደሩ ላይ ተስፋ የመቁረጥና ተነሳሽነትን የሚቀንስ መሆኑን ጠቅሰው፤ ለአብነትም የአንድ ኪሎ ግራም ሻይ ምርት እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ አምስት ብር እንደሆነ ነው የገለጹት። ይሁንና አርሶ አደሩ የምርት ዋጋን የሚሸፍን አለመሆኑን በመወያየትና በማስረዳት፤ ወደ 25 ብር አካባቢ ያደገበት አግባብ ስለመኖሩና አሁንም በቂ እንዳልሆነ ነው የተናገሩት። ከምርት ወጪ አንጻር ድርጅቶቹ እየገዙበት ያው ዋጋ ዝቅተኛና አርሶ አደሩ ምርቱን ወደ ማሳ የሚወስድበትን ተነሳሽነት የሚቀንስ ነው ብለዋል።

ክልሉ በሻይ ምርት ዕምቅ አቅም ያለው በመሆኑ ችግሮቹን በመቅረፍ ምርቱ በክልሉ አቅም ልክ መመረት እንዲችል መሥራት የሚጠይቅ ነው ያሉት አቶ በላይ፤ ለዚህም በክልሉ የተለያዩና ተወዳዳሪ መሆን የሚችሉ የጎጆ ኢንዱስትሪዎችን መትከል ተገቢ ነው። በማለት የኬንያን ተሞክሮ ይጠቅሳሉ። ‹‹ኬንያ ላይ አርሶ አደሩ በራሱ ማሳ ላይ የሻይ ምርቱን ካሰፋ በኋላ የጎጆ ኢንዱስትሪዎች እየተስፋፉ ምርን የሚያነሱ ሲሆን፤ በዚህም በአሁኑ ወቅት ኬንያዎች ሻይ ላይ ያላቸው ልምድ እያደገና ምርቱም እየሰፋ የሄደበት ሁኔታ ስለመኖሩ ጠቅሰዋል። ኢትዮጵያም ከዚህ ተሞክሮ በመውሰድ አገሪቷ ያላትን ዕምቅ አቅም አሟጦ በመጠቀም ከዘርፉ አገር ማግኘት የሚገባትን ጥቅም ማግኘት እንድትችል የጎጆ ኢንዱስትሪዎችን በማስፋፋት ሻይን ማቀነባበር ያስፈልጋል። ይህ ካልሆነ በስተቀር አርሶ አደሩ ምርቱን ቢያሰፋ እንኳን ምርቱን አውጥቶ የሚሸጥበት ዕድል የለውም። ከዚህ በተጨማሪም የሻይ ምርት ከሌሎቹ ሰብሎች በበለጠ መቀነባበርን የሚፈልግና ሳይቀነባበር እንዲሁ ተመርቶ ብቻ ለገበያ የሚቀርብ ሰብል አይነት ባለመሆኑ አርሶ አደሩን እየፈተነ ያለና ምርቱ በሚፈለገው መጠን ማደግ አልቻለም›› በማለት አስረድተዋል።

ማህበራዊ

# አስኳላ

## "ትምህርት ለትውልድ"




ግርማ መንግሥቴ

በሌላው ዓለም፣ በተለይም በአደጉት ሀገራት የትውልድ ጉዳይ የእለት ተእለት አጀንዳ ነው። ስለ ትውልድ ይመከራል፣ ስለ ትውልድ ይጠናል፣ ስለ ትውልድ ፖሊሲ ይቀረፃል፣ ይሻሻላል፤ አዳዲሶችም ይወጣሉ።

በሰለጠነው ዓለም የአንድ ሕገመንግሥት አይነኬ እድሜ 19 ሲሆን፣ ከዛ በኋላ ይፈተሻል፣ ይከለሳል፤ ይበረዛልም። "ምክንያት?" ከተባለም፣ ሌላ አዲስ ትውልድ አዳዲስ ጥያቄዎችንና ፍላጎቶችን ይዞ መጥቷልና "ባለውና በነበረው ተገዛ" ይሉ ፈሊጥ የማይሰራ በመሆኑ ነው።

በሰለጠነው ዓለም ስለ ትውልድ የሚመክሩ መድረኮች ተቆጥረው አያልቁም፤ በነዚህ አገራት ስለ ትውልድ የሚጠበቡ አረጋዊያን እልፍ አእላፍ ናቸው። በዲሞክራት አገራት ስለ ትውልድና የተሻለ ነገ የሚጨነቁ የፖለቲካ ድርጅቶች ብዙ ናቸው። "ስለ ትውልድ ያገባናል፣ ኃላፊነትም አለብን" የሚሉ ተቋማት ቁጥራቸው ዳር ድንበር የለውም። ባጭሩ፣ በትውልድ ስም የተቋቋሙ፣ ትውልድ ላይ ለመስራት ወገባቸውን አስረው የተነሱ ተቋማት በዓለማችን አራቱም መአዘን ሞልተዋል።

መጪዋ ዓለማችንን ያለ መጪው ትውልድ ማሰብ እራሱ አለማሰብ ነው በማለት ትውልድ ላይ መስራት እንዳለባቸው ወስነው እየሰሩ ያሉ አካላት ሞልተዋል። ችግሩ "ውጤቱስ?" ካልሆነ በስተቀር ትውልድ ላይ የሚፈሰው መዋእለ ነዋይ፣ ስለ ትውልድ ሲባል የሚወጣው ጉልበትና እውቀት ከግምት በላይ ነው። ይሁን እንጂ፣ ከዚህ ሁሉ ወጪ አንዳንዶቹ አገራት ሲያተርፉ ቀሪዎቹ ደግሞ ሲከስሩ ነው የሚታዩት።

እዚህ ላይ ለተሻለ ትውልድ መምጣት፣ መፈጠር፣ ለተሻለ ነገ ...ስለሚሰሩት አነሳን እንጂ፣ ሆን ብለው፣ በጀት፣ የሰው ኃይል፣ ጊዜ ... መድበው የተኮላሸ ትውልድ እንዲፈጠር የሚሰሩ የሉም እያልን አይደለም። በዓለማችን የትኛውም ክፍል እንደ እነዚህ አይነት መርገምቶች ሞልተው ተትረፍርፈዋል። እነዚህ ወገኖች የልፋታቸውን አላገኙም ማለት በማይቻል ደረጃም ዓላማቸውን እያሳኩ ሲሆን፣ ማህበረ-ባህላዊ እሴቶችን መናድ ላይ የተሰማራው ወጣትና መሰል የህብረተሰብ ክፍል (በተለይ በፖለቲካው አለም ያሉ) የእነዚህ ተቋማትና ቡድኖች፣ እንዲሁም ግለሰቦች የ"ልፋት"ና ምኞቶቻቸው ውጤቶች ናቸው።

ይህንን አገላለፃችንን መሬት ለማሳረፍ ደግሞ የትምህርት ሚኒስቴር ሚኒስትሩ ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ፣ የካቲት 24 ቀን 2014 ዓ.ም ጂንካ ላይ ባደረጉት ንግግር «በቅርብ በተደረጉ ጥናቶች እንደተረጋገጠው 3ኛ ክፍል ከደረሱ ተማሪዎች መካከል 65 በመቶዎቹ ማንበብ አይችሉም። ለዚህ ምክንያቱ ባለፉት 27 አመታት በትምህርቱ ላይ የተሠራው አሻጥር ነው።» ያሉትን ብቻ መጥቀሱ ከበቂ በላይ ይሆናልና የነበረው የትምህርታችን ይዞታ ይህንን ይመስል ነበር። ከዚህ አኳያ ነው እንግዲህ የትምህርት ሚኒስቴርን "ትምህርት ለትውልድ" መርህን በማድነቅ፣ በመደገፍና ወደዚህ ገጽ በመምጣት "እሰየው" ለማለት የተፈለገው።

ምናልባት ከ70 በመቶ በላይ ወጣት ያላት አፍሪካ ተዘናግታ ካልሆነ በስተቀር፣ በተቀረው ዓለም በራሱ፣ በወጣቱ ሳይቀር ለወጣቱ እየተሰሩ ያሉ ተግባራት አያሌ ናቸው። ከእነዚህ ተቋማት መካከል ደግሞ የትምህርት ተቋማት ቀዳሚዎቹና ልዩ ትኩረት የተሰጣቸው ናቸው።

ኢትዮጵያ ወጣ ገባ እያለችም ቢሆን ስለ ትውልድ ጉዳይ መጨነቋ አልቀረም። ከ"ወጣት የነብር ጣት" ጀምሮ "ያለ ወጣቱ ታስትፎ አብዮቱ ግቡን አይመታም" ድረስ ሄዳለች። ከ"የወጣቶች ማህበር" እስከ "የወጣቶች ሊግ" ብቻ ሳይሆን ወጣቶችና ስፖርትንም እስከ ማቋቋም ድረስ ገፍታበታለች። "ውጤቱስ?" ከተባለ ዝቅ ብለን የምናየው ይሆናል። (እዚህ ጋ "ያ ትውልድ" (ትውልዱን ለማስታወስ በሰሜን አሜሪካ «ያ ትውልድ ተቋም» በኢትዮጵያዊያን መቋቋሙን ልብ ይሏል)፣ "ይሄ ትውልድ"፣ "የዛሬ ልጅ"፣ "የድሮ ልጅ" ... የሚሉ አተካሮዎች ውስጥ መግባቱ አያስፈልግም በሚል እንጂ፣ ኢትዮጵያ ውስጥ የትውልድ ጉዳይ ሥርዓት ባለው መንገድ እየተመራ ነው ለማለት ጊዜው ገና ይመስላል።)

እዚህ ላይ "እቅድህ የ10 አመት ከሆነ ዛፍ ትከል፤ እቅድህ የ100 አመት ከሆነ ትውልድን (ልጅህን) አስተምር" የሚለውን የቻይናዊያን (ኮንፊሺየስ) አስተምህሮ ማንሳት አስፈላጊ ነው። በአገራችንም ወጣቱንና ትውልድን ማእከል አድርገው በመስራት የሕይወት ዘመናቸውን ያሳለፉ ግለሰቦች የነበሩ ሲሆን፣ ይህ ጸሐፊ እስከሚያውቀው ድረስ፣ እንደ ኢትዮጵያዊው ምሑር፣ የሙብት ተሟጋች፣ ፖለቲከኛና ሐያሲ ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማሪያም (1922 – 2013 ዓ.ም)፣ በስማቸው "መስፍን ወልደማርያም ፋውንዴሽን" የሚል ተቋም ተመስርቷል (ፋውንዴሽኑ በፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም ስም የተሰየሙ ቤተ መጻሕፍት እና ማዕከላት በሁለተኛ ደረጃ እና በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት እንዲከፈቱ የማድረግ እቅድ እንዳለው በምስረታው እለት ተገልጿል)፣ ወጣት ተኮር ስራዎችን የሠራ አለ ለማለት ሞራሉ አይኖርም። ሰውየው ለወጣቱ ጥብቅና እንደ ቆሙ፣ ወጣቱን እንደ ገሰፁ፣ ወጣቱን እንዳስተማሩ፤ ያላቸውን ሁሉ ለወጣቱና መጪው ትውልድ እንደ ወረወሩ፤ ወጣቱን እንዳወያዩ፣ ከወጣቱ ጋር እንደ ተወያዩ ነው ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩት ። በመሆኑም ነው፣ ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ሀውልታቸው ላይ አዘወትረው የሚናገሯትና "ነገ የወጣቱ ነው" የምትለው አገላለፃቸው እሳቸውን ለትውልድ ትገልፅ ዘንዳ ስፍራ የተቸራት።

"የከፍተኛ ትምህርት ዘይቤ" መጽሐፍ አዘጋጅ፣ ዶ/ር እጓለ ዮሀንስንም እዚሁ ጋ ጠቅሶ ማለፍ የግድ ይሆናል። ሌሎችም ብዙ ብዙ አሉ፤ ችግሩ አንዱ የገነባውን ሌላው (በተለይም መጪው) ማፍረሱ ሆነ እንጂ።

"ትውልድ" ከዚህም ባለፈ በተለያዩ የፖለቲካው አለም ሰዎችም ሲጠቀስ፣ ሲወደስ ... ይሰማል። ከተወዳጆቹና ተወዳሾቹም አንዱ የአሁኑ (ወይም፣ መጪው? ትውልድ) ሲሆን፣ በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ብያኔ ይህ ትውልድ የአባቶቹ ልጅ፣ "የመደመር ትውልድ" እንጂ በየ "ጓጥ ስርጓጉጡ" ተወሻሽቆ በአገሩ ላይ ብሽሽቆሽ የሚጫወት ትውልድ አይሆንም።

ወደ ፈጠራው አለም ስንመጣ የማይታለፉ ሰዎችን የምናገኝ ሲሆን፣ ቀዳሚውም የ"ተማር ልጄ" ባለቤት ድምፀ ሸጋው አለማየሁ እሸቴ ነው። "ተማር ልጄ / ወገን ዘመድ የለኝ / ሀብት የለኝም ከጄ" . . . የተሻለ ትውልድን ከመፍጠር፤ የተሻለ ነገን እውን ከማድረግ አኳያ የአባቶችን ሚና ብቻ ሳይሆን የአሁኑ ትውልድ ለነገው ዛሬ ምን ማድረግ እንዳለበት ሁሉ የሚመክር "ዜማ!!!"።

እንደሚታወቀውና ከላይ እንደ ተመለከትነው፣ ከታችም እንደምንመለከተው ትምህርት ሚኒስቴር እና የትውልድ ጉዳይ ተነጣጥለው የሚታዩ አይደሉም። "ትምህርት" የሚለው እስካላምታታን ድረስ ሁለቱ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገፅታዎች ናቸው።

ትምህርት ሚኒስቴር ወደ ሪፎርም ከገባ ወዲህ ለውጥ ካመጣባቸውና እያመጣባቸው ካሉ አሰራሮች፣ አካሄዶችና አስተሳሰቦች አንዱ ይኸው "ትምህርት ለትውልድ" ሲሆን፣ የማህበራዊ ድረገጽ መግቢያ ገፁን መከፈቻ ያደረገውም ይህንኑ ሞቶና ሎጎ (አርማ) ነው።

ሳይገድሉ ጎፈሬ፣ ሳያጣሩ ወሬ እንዳይሆንብን፣ ከፈረሱ አፍ እንዲሉ የትምህርት ሚኒስትሩ ፕሮፌሰር ብርሀኑ ነጋ የሚሉትንም እንስማ።

ጳጉሜ 02/2015 ዓ.ም የትምህርት ሚኒስቴርና ተጠሪ ተቋማት ሠራተኞች የ2015 ዓ.ም ስራ አፈጻጸምና የ2016 ዓ.ም እቅድ ላይ ውይይት ባካሄዱበት እለት "የቀጣዩ ትውልድ ዕጣ ፋንታ በእጃችን በመሆኑ በላቀ የኃላፊነትና ተጠያቂነት ስሜት እንስራለን" ለሚለው ከፍተኛ አፅንኦት የሰጡት ሚኒስትሩ ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ የቀጣዩን ትውልድ ዕጣ ፋንታ በመወሰን በኩል የትምህርት ዘርፉ ሠራተኞች ሚና ከፍተኛ መሆኑን ጠቅሰው ሁሉም ሠራተኛ በየተሠማራበት የሥራ መስክ በላቀ የኃላፊነትና ተጠያቂነት ስሜት ሊሠራ እንደሚገባም አስገንዝበዋል፡፡

በውይይቱም፣ በአጠቃላይ ትምህርት ልማት ዘርፍ "ትምህርት ለትውልድ"ን መሰረቱ ያደረገው የአዲሱ ሥርዓተ ትምህርት ትግበራ፤ የ12ኛ ክፍል ሀገር አቀፍ ፈተና፣ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ማሻሻያ፣ በአዲሱ የትምህርት ቤቶች ዲዛይን መሠረት አዳዲስ ትምህርት ቤቶችን የመገንባት ሥራዎችና ሌሎችም ሥራዎች ስኬታማ በሆነ መልኩ የተተገበሩና የተጀመሩ መሆናቸው በውይይቱ ወቅት የተነሱ ሲሆን፣ ያለፈውን አመት ጥንካሬዎች ይበልጥ ተጠናክረው እንደሚቀጥሉና ያጋጠሙ ክፍተቶችን በማረም በመጪው 2016 ዓ.ም በለውጥ ሥራዎችም ሆነ በመደበኛ ሥራዎች ከፍተኛ ስኬት ለማስመዝገብ እንደሚሠራም የጋራ ግንዛቤ ስለመያዙ ተነግሯል።

ሌላዋ፣ ጳጉሜን 5 "የትውልድ ቀን" መሆኑን ተከትሎ መልእክት ያስተላለፉት የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ ሲሆኑ፤ "አዲሱ ትውልድ ሀገሩን የሚወድ፣ የሚያነብ፣ የሚመራመርና ችግር ፈቺ ሊሆን ይገባል" የሚለው የመልእክታቸው ኃይለ-ቃል ነበር።

የትምህርት ሚኒስቴር የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር ባዘጋጁትና ሚኒስትሮች፣ ሚኒስትር ዴኤታዎች፣ የዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንቶችና ሌሎችም ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች በተገኙበት በዚሁ መድረክ ላይ "ትውልዱ በትምህርት የታነጸ፣ ታሪክና ባህሉን የሚያውቅና ስለሀገሩ የሚቆጭ፤ የማንበብ ባህልን በማዳበር ችግር ፈቺ ሆኖ ሀገሩን የሚያሻግር ሊሆን ይገባል።" ሲሉም ነው ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ያሳሰቡት።

ኢትዮጵያ በተፈጥሮ ሀብት የታደለች መሆኗን የጠቆሙት ፕሬዚዳንቷ ትውልዱ ተስፋ ሰጪ የፈጠራ ችሎታውን በማዳበር ሀገሩን መለወጥ እንዳለበት መክረዋል። የትምህርት ሚኒስትሩ ፕሮፌሰር ብርሀኑ ነጋ በበኩላቸው አዲሱ ትውልድ በማንበብ፣ በማሰላሰልና ምክንያታዊ በመሆን ሀገሩን ሊያሻግር እንደሚገባ አስገንዝበዋል።

በተመሳሳይ፣ ወጣቱም ሆነ መጪው ትውልድ አገርን መውደድና መጠበቅ፣ ስልጣኔን ማስቀጠል፤ እንዲሁም፣ የዓለምን ፈተና መሻገር የሚችል መሆን እንደሚጠበቅበት፤ በእሳቸው ዘመን የነበረው ትውልድ ለስልጣኔ የሚቆጭ ግብረገብ፣ በማንበብና በማሰላሰል የሚያምን እንደነበረም ፕሮፌሰር ብርሀኑ ወደ ኋላ አስታውሰዋል።

በጉዳዩ ላይ ገፋ አድርገው የሄዱት በደርግ ዘመን የተወሰደውን አስከፊ ርምጃና ታሪካዊ ስህተት ሲገልፁት "አንድ ትውልድ የመመተር እርምጃ" በማለት ሲሆን፣ ይህም በቀይ እና ነጭ ሽብር ስያሜ የተወሰደውን መተላለቅ እና የስልጣን ሽኩቻ፤ እንዲሁም ያለቀውን ወጣት ለማመልከት መሆኑን ይገልፃሉ።

በኢህአዴግ ዘመን ያለውን የመረመሩ ደግሞ ወጣቱ በተለያዩ ሱሶች የደነዘዘበትና ለባለ ዲግሪ ሥራ አጥነት የተዳረገበት መሆኑ ላይ ይስማማሉ።

ከለውጡ በኋላ ያለውን በተመለከተ ይህንን ያህል ለውጥ መጥቷል ለማለት መረጃው ባይገኝም፣ በትምህርቱ ዘርፍ ግን በርካታ መታየት የጀመሩ እንቅስቃሴዎች መኖራቸው ላይ የብዙዎቻችን ግንዛቤ አለ።

የ"ትምህርት ለትውልድ"ን እንደ መርህ መጠቀም አንድምታውም ሆነ ፋይዳው ምንድን ነው? የሚለውን መቃኘት ካስፈለገ በወርድና ስፋቱ ጥልቀትና ርዝመቱ ምክንያት መመለሻ ልናጣበት የምንችል ከመሆኑ በስተቀር ተግባሩ ያስኬዳል። ሆኖም ግን ለዚህ ጽሑፍ ሲባል ብቻ ቀንበበን መመልከቱ ጠቃሚ ይሆናል።

ከላይ ለመጠቋቆም እንደ ሞከርነው ትምህርትና ትውልድ የሚነጣጠሉ ጉዳዮች አይደሉም። የመጀመሪያው ሁለተኛውን መቅረጫ ሲሆን፣ ሁለተኛው የተዋጣለት ይሆን ዘንድ የመጀመሪያው እጅግ አስፈላጊ መሆኑ ከሁሉም በላይ ሊሰመርበት ይገባል። በተለይ በዚህም ይሁን በመጪዎቹ ዘመናት የሁለቱ መስተጋብር የምርጫ ጉዳይ ሳይሆን የግዴታና ተፈጥሯዊ ነውና በጉዳዩ ላይ ደግሞ ማሰብ፣ ደጋግሞ ሀሳብ መለዋወጥ፤ ሳይታክቱም መስራትን ይጠይቃል።

ሁለቱን ነጥለን ማየት አይቻልም ስንል፣ እድሜያቸውን ትውልድ ቀረፃ ላይ ያሳለፉት አርቲስት፣ ደራሲና የመድረክ ባለሟሉ አባባ ተስፋዬ (ተስፋዬ ሳህሉ) በጥኡመ ልሳናቸው "ልጆች፣ የዛሬ አበባዎች / የነገ ፍሬዎች" በማለት ሲያስተምሩ እንደ ኖሩት በትምህርት ዓለም ውስጥ ያሉ ልጆች የዛሬ አበባዎች፤ የነገ ፍሬዎች ናቸውና ትምህርትም ሆነ አጠቃላይ የትምህርት ሥርዓቱ ከተበላሸ ልጆችም (በተራዛሚው ትውልዶች) ተበላሹ ማለት በመሆኑ "የነገ ፍሬዎች" ብሎ ነገር አይኖርም ማለት ነው። ይህ ማለት ደግሞ አገርም ሆነ ህዝብ አለ ማለት የማያስችልበት ደረጃ ያደርሳልና ድስት ጥዶ ከማልቀስ ከወዲሁ አንድ ነገር ማድረጉ የግድ ይሆናል።

የትምህርት ሚኒስትር ፕሮፌሰር ብርሃኑ ሰኔ 25 ቀን 2015 ዓ.ም እኩለ ቀን ላይ በጽሕፈት ቤታቸው በመገኘት ለሀገር ውስጥ መገናኛ ብዙኃን በወቅታዊ ጉዳይ ላይ መግለጫ በሰጡበት ወቅት እንደተናገሩት፤ አሁን በሀገራችን ያሉ ትምህርት ቤቶች አብዛኞቹ ከደረጃ በታች ከመሆናቸው የተነሳ ለመማር ማስተማር ሥራው ምቹ አይደሉም። በመሆኑም ይህንን ለመቅረፍ «ትምህርት ለትውልድ» የትምህርት ቤቶች መሠረተ ልማት ማሻሻል ሀገራዊ ንቅናቄን በሀገር አቀፍ ደረጃ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዐቢይ በተገኙበት የተጀመረው በሁሉም ክልሎች ተግባራዊ የተደረገ ሲሆን ሁሉም ገንዘቡ፣ እውቀቱና ጉልበቱ ያላቸው ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን መርሀ ግብሩን እንዲደግፉት የማድረግ ሥራ ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል።

ከዚህም ሆነ ከሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ "ሞቶ" (ትምህርት ለትውልድ) መረዳት የሚቻለው መንግሥትና የመንግስትን ፕሮግራም አስፈፃሚው መሥሪያ ቤት (ሚኒስቴሩ) ያለፈው ስህተት እንዳይደገም፤ መጪዎቹ ዘመናት መልካም ሥነ ምግባር ያለው፣ የእውቀት ባለቤት የሆነ፣ የእውነት አራማጅ፣ ለሀገርና ወገኑ ከፍተኛ አክብሮትና ፍቅር ያለው፣ ሰርቶ የማይጠግብ፣ ዘርቶ የሚቅም፣ ወልዶ የሚስም ... ትውልድ ማፍራት ላይ በሙሉ ኃይል እየሰሩ መሆኑን ነውና፣ ትምህርት ባለ ድርሻዎቹ በርካቶች እንደ መሆናቸው መጠን፣ የሚመለከተው ሁሉ ሊያብርና ሊተባበር፤ ከሚኒስቴሩ ጎንም ሊሰለፍ ይገባል እንላለን።

መልካም አዲስ አመት፤ መልካም የትምህርትና መማር-ማስተማር ዘመን!!!

# ‹‹ባለፉት አምስት ዓመታት ከ275 ሺህ ሜትር ኪዩቢክ በላይ ተጨማሪ ውሃ አዲስ አበባ አግኝታለች››



- የአዲስ አበባ ከተማ ውሃና ፍሳሽ ባለሥልጣን የውሃ አቅርቦትና ሥርጭት ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ፍቃዱ ዘለቀ

ስምስም መንግሥቱ

**ውሃ ለሰው ልጅ መሠረታዊ የሕይወቱ አካል መሆኑን ተከትሉ፤ መንግሥት በቻለው አቅም ተደራሽ የማድረግ ግዴታ እንዳለበት በህግ ተቀምጧል፡፡ በዚሁ መሠረት በአዲስ አበባ ከተማ ውሃ በተመጣጣኝ የአገልግሎት ክፍያ እንዲቀርብ እየተደረገ ቢሆንም፤ የአገልግሎት መቋራረጥን ምክንያት በማድረግ ከነዋሪዎች ተደጋጋሚ ቅሬታዎች ይሰማሉ፡፡**

**በተለይ በአንዳንድ የከተማዋ አካባቢዎች ውሃ በቧንቧ መጠቀም ብርቅ በመሆኑ፤ በመንግሥት ድጎማ በተመጣጣኝ የአገልግሎት ክፍያ እየቀረበ ያለው ውሃ በተለያየ መንገድ በመኪና እና በጋሪ ተጉዞ ነዋሪው ጋር ከተመን በላይ እየተሸጠ ገበያው ደርቷል የሚል ጥቆማ ደርሶናል፡፡**

**ጥቆማውን መሠረት በማድረግ በከተማዋ ውሃ የማስተዳደር፣ ተደራሽ የማድረግ፣ ለሚሰጠው አገልግሎትም ክፍያ የመሰብሰብ ሥልጣንና ኃላፊነት የተሰጠው የአዲስ አበባ ከተማ ውሃና ፍሳሽ ባለሥልጣን ጉዳዩን እንዴት ያየዋል? ስንል ከተገልጋይ የሰማነውንና የታዘብነውን በባለሥልጣኑ የውሃ አቅርቦትና ሥርጭት ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጅ ለአቶ ፍቃዱ ዘለቀ ጥያቄ አቅርበን፤ እርሳቸውም ምላሽ ሰጥተውናል፡፡ መልካም ንባብ፡-**

**አዲስ ዘመን፡- በቅድሚያ የአዲስ አበባ ከተማ የውሃ አቅርቦት ታሪክ ምን ይመስላል ከሚለው እንነሳ?**

**አቶ ፍቃዱ፡-** ከታሪክ እንደምንረዳው፤ የውሃ ስርጭቱ በቧንቧ ቤት ለቤት ውሃ ማቅረብ መነሻ ያደረገ አልነበረም። መጀመሪያ ውሃ መቅረብ የጀመረው ከምንጭ ነው። ምንጩም ከእንጦጦ የተገኘ ነበር። የውሃ አቅርቦት ተደራሽነቱም ውስን ነበር። የምንጭ ውሃ ተጠቃሚዎችም መሳፍንት ተብለው የሚጠሩ ከፍተኛ የሀገሪቱ ባለሥልጣናት ነበሩ።

በመቀጠል በነፃ ቦኖ በሚባለው የውሃ አገልግሎት መስጫ ቤተ መንግሥት፣ ስድስት ኪሎና አራት ኪሎ አካባቢዎች ብቻ ተደራሽ ሲደረግ ነበር። አብዛኛው ማህበረሰብ የሚጠቀመው ከምንጭና ከወንዝ ነው። ከተማዋም አሁን በምትገኝበት ደረጃ የሰፋች አልነበረች። በመሆኑም የተጠቃሚውን ቁጥርና የሚቀርበውን የውሃ መጠን በመረጃ አስደግፎ ለማቅረብ ያስቸግራል። በወቅቱ የውሃ አቅርቦት ጉዳይ አሳሳቢ ሆኖ የሚነሳም አልነበረም። በጊዜው ወንዞችም ሆኑ ምንጮች ጥሩ ነበሩ። ይህ ከአንድ መቶ አመት በፊት የነበረ ታሪክ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- አዲስ አበባ ከተማ የምንጭ ውሃ ከመጠቀም ከወጣች በኋላ እንዴት ወደ ዘመናዊ የውሃ ስርጭት ቻለች?**

**አቶ ፍቃዱ፡-** አዲስ አበባ ወደ ዘመናዊ የውሃ ስርጭት የገባችው በሁለት አይነት መልኩ ነው። ከመሬት አካል በላይ ከሚሰበሰብ ወይንም ገፀምድር፣ እንዲሁም ከመሬት ውስጥ በቁፋሮ ከሚገኝ ወይንም ከከርሰምድር ነው። ባለስልጣኑ ከእነዚህ ሁለት ምንጮች ውሃ አምርቶ ለተጠቃሚው እያሰራጨ የሚገኘው።

በግድብ ደረጃም በአዲስ አበባ ከተማ በስተምእራብ በኩል በ1948 ዓ.ም አካባቢ የተገነባው የገፈርሳ ግድብ ሲሆን፤ የዚህ ግድብ ውሃ ስርጭት የተጀመረው በቦኖ አገልግሎት ነው።አገልግሎቱንም ሲሰጥ የነበረው በማዘጋጃ ቤት ውስጥ በተቋቋመ ውሃ ቢሮ ወይንም ውሃ ክፍል አማካኝነት ነበር። በመቀጠል በ1963 አካባቢ መጀመሪያ ደግሞ የለገዳዲ ግድብ ሥራ ጀመረ።

በዚሁ መሠረት ከለገዳዲ ግድብ በቀን 50ሺ ሜትሪክ ኪዩብ፣ ከገፈርሳ ግድብ ደግሞ በቀን 23ሺ ሜትሪክ ኪዩብ ውሃ እየተመረተ ለከተማዋ ነዋሪ ሲቀርብ የነበር። ባለሥልጣን መሥሪያቤቱም በአዋጅ ተቋቁሞ የውሃ ታሪፍ እየሰበሰበ ሥልጣን ያለው ተቋም ሆኖ አገልግሎት መስጠት የጀመረው በዚህ ጊዜ ነው። በ1990ዎቹ መጀመሪያ ላይ ደግሞ ሶስተኛው የገርቢ ግድብ ለአገልግሎት በቃ። ከምንጭ ወደ ግድብ ተሸጋግሮ የውሃ አቅርቦት አገልግሎት እየሰፋ የመጣው በዚህ መልኩ ነው። አሁን ላይ ለአዲስ አበባ ከተማ የውሃ አገልግሎት እየተዳረሰ ያለው ከሶስቱ ግድቦች ነው።

የውሃ ልማቱን ሥራ በተመለከተም፤ የገፀምድር ውሃ የሚገኘው በክረምት ወቅት የሚዘንብ ዝናብ በግድብ ውስጥ በማጠራቀም ወይም በመሰብሰብ ነው፡ ፡የገፀምድር ውሃ ጭቃ የያዘ ስለሚሆን በግድቡ ማጣሪያ ጣቢያ ውስጥ ማለፍ ይኖርበታል። በዚሁ መሠረትም የተሰበሰበውን ወይም የተጠራቀመውን የዝናብ ውሃ ከአዲስ አበባ ከተማ በስተምእራብ በኩል በሚገኘው ገፈርሳና በለገዳዲ ግድቦች በሚገኙ የማጣሪያ ጣቢያዎች ውስጥ የማጣራት ሂደት ይከናወናል።

ድሬ ግድብ የራሱ የማጣሪያ ጣቢያ ስለሌለው ልክ እንደለገዳዲ ግድብ ጥሬ ውሃ ይይዝና በገፈርሳና በለገዳዲ ግድቦች በሚገኝ የውሃ ማጣሪያዎች ውስጥ እንዲጣራ ይደረጋል፡ ፡ከገፀምድር የተገኘው ውሃ በዚህ መልኩ ከተጣራ በኃላ ለህብረተሰቡ ይሰራጫል።

ሌላው የከርሰምደር ውሃ ልማት ሥራ ደግሞ ጉድጓድ በመቆፈር ውሃ ወደ ሥርጭት የሚገባበት አሰራር ነው። ከ2000 ዓ.ም በፊት በየአካባቢው አልፎ አልፎ ጉድጓድ በመቆፈር ውሃ የሚቀርብበት ሁኔታ ነበር። የከርሰ ምድር ውሃ አቅርቦት እየተጠናከረ የመጣው ከ2001 ዓ.ም በኋላ ነው። በዚሁ መሰረትም ለውሃ መገኛ ይሆናሉ የተባሉ መሬቶችን በጥናት በመለየት የሚከናወን ሲሆን፤ አሁን በደረስንበት ደረጃም እስከ አምስት መቶ ሜትር ጥልቀት ያለው ጉድጓድ በመቆፈር ውሃ ማግኘት ተችሏል። በዚህ ወቅት 238 ጉድጓዶች በሥራ ላይ ሲሆኑ፤ ከእነዚህ ጉድጓዶች ውስጥ የሚወጣው ውሃ ተሰብስቦ ወደ ስርጭት ማእከል (ኔትወርክ) ውስጥ እየገባ ለህብረተሰቡ እንዲቀርብ ይደረጋል።

በአጠቃላይ ከርሰ ምድር ማለት ለዘመናት በመሬት ውስጥ የተከማቸ ውሃን ለተጠቃሚው እንዲደርስ ማድረግ ነው። ከከረሰ ምድር ውስጥ የሚወጣ ውሃ ብዙ ማጣራት አይፈልግም። ንጹህ ውሃ ነው። ውሃው ወደ ስርጭት ከመወሰዱ በፊትም አይረን፣ ፍሎራይድ፣ ማንጋኒዝ የተባሉ ንጥረነገሮች በውስጡ መኖሩን እንዲሁም የሙቀቱና የቅዝቃዜው መጠን ይለካል። የዓለም ምግብና ጤና ድርጅት (ደብሊው ኤች ኦ) ካስቀመጠው መስፈርት በታች መሆንና አለመሆኑ ተረጋግጦ በክሎሪን ታክሞ ወደ ህብረተሰቡ እንዲሰራጭ ይደረጋል።

የገፀምድርና ከርሰምድር ውሃ አስፈላጊነታቸው ጥያቄ ውስጥ አይገባም። እንደውሃ መገኛ አይነቱ ሁለቱም ተቀናጅተው ጥቅም ላይ ይውላል። ጥቅም ላይ እየዋለ ያለው እንደየሀገሩ ሀብት ተጨባጭ ሁኔታ አንዱን አይነት ወይም ሁለቱንም በማጣጣም ነው።የዓለምአቀፍ ተሞክሮም የሚያሳየው ይሄንኑ ነው።

በሀገራችንም በአሁኑ ጊዜ አቃቂ ክፍል አንድ፣ ሁለት፣ ሶስት፣ ቱሉጉዶ እና ኮዬፈጩ በሚል በየደረጃው በሥፋት ሥራዎችን በማከናወን ላይ ነን። የከተማዋን የውሃ ፍላጎት ለማሟላትና በአቅርቦት መካከል ያለውንም ክፍተት ለመሙላት ጥረት ማድረግ የተቻለውም እነዚህን ሥራዎች በመሥራት ነው።

ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ በአሁኑ ጊዜ በድምሩ ከገፀምድርና ከከርሰምድር በቀን ወደ 792ሺ ሜትሪክ ኪዩቢክ ውሃ አምርቶ የማቅረብ አቅም ተፈጥሯል። ተቋሙ ይህን አቅም ቢፈጥርም፣ ከከተማዋ ነዋሪ የውሃ አቅርቦት ፍላጎት ጋር በንጽጽር ሲቀርብ ልዩነቱ የሰፋ ነው። በአሁኑ ጊዜም ለከተማው ነዋሪ ወደ አንድ ነጥብ ሶስት ሚሊዮን ሜትሪክ ኪዩቢክ የውሃ አቅርቦት እንደሚያስፈልግ ይገመታል።

**አዲስዘመን፡- አዲስ አበባ ከተማ ለነዋሪዎችዋ ልታቀርብ የምትችለውን የውሃ መጠን ለማወቅ በጥናት የመለየት ሥራ ተሰርቷል?**

**አቶ ፍቃዱ፡-** እንደሀገር ወይም አዲስ አበባ ከተማ ከከረሰምድርና ከገፀምድር ይሄን ያህል ሜትሪክ ኪዩብ የውሃ መጠን ይገኛል፤ ይህን ያህል ውሃ የመሰብሰብ አቅም አለ በሚል በዝርዝር የተከናወነ የጥናት ሥራ የለም። ነገር ግን በየጊዜው እየተጠና ፕሮጀክት ተቀርፆ እየለማ ነው። ወደ ምርት ተቀይሮ ውሃ ለተጠቃሚው እንዲደርስ እየተደረገ መሆኑ አያጠያይቅም። እኛ ጥናት እየሰራን ያለነውም ለምንፈልገው ወይም ለምናስበው ፕሮጀክት ብቻ ነው። ባጠናነው አካባቢም የምናገኘውን የውሃ መጠን እየወሰንን እንሔዳለን።

ለምሳሌ ለገዳዲ ግድብ ከመሰራቱ በፊት፣ ከግድቡ ሊገኝ የሚችለው የውሃ መጠን ይታወቃል። ውሃም የሚመረተው ግድቡ በተሰራበት ዲዛይን መጠን ልክ ነው።የከርሰምድር ውሃ መገኛዎችን በተመለከተም ወደ ትግበራ የሚገባው እንዲሁ ጥናት ተካሂዶ ነው። ለምሳሌ የአቃቂ ከርሰምድር የመጀመሪያ የጥናት ሥራ በቀን እስከ 223 ሺህ ሜትር ኪዩብ ማምረት የሚያስችል የከርሰ ምድር ውሃ መጠን መኖሩን ነበር።ለህብረተሰቡ ውሃ የምናሰራጨው በዚህ መልኩ በየፕሮጀክቱ እያረጋገጥን በማልማት ነው ።

**አዲስ ዘመን፡- አሁን በሥራ ላይ ካሉ የውሃ ማሰራጫ ግድቦች ተጨማሪ አዳዲስ ሥራዎች የሉም ማለት ነው? አያይዘው የሚገልጹልን ግድቦች በደለል የመሞላት ችግር ያጋጥማቸዋል። በዚህ ረገድ ያለበት ደረጃ እና ተጽእኖ ምን ይመስላል?**

**አቶ ፍቃዱ፡-** በደለል ከመሞላት ጋር የተያያዘው፤ በገፀምድር ውሃ መገኛ ላይ ከሚያጋጥም ችግር ወይም ተግዳሮት መካከል አንዱ ይህ ነው። የአካባቢ ጥበቃ ሥራ ካልተሰራ ገድቦች በደልል የመሞላት ሁኔታ ከፍተኛ ነው። ወደ ግድቡ የሚገቡ ወንዞች ወይንም ወደ ግድቡ የሚገባው ጎርፍ የሚሰበሰብበት ምድረ አካል ይታወቃል። እነዚህን አካባቢዎች በአረንጓዴ ልማት መንከባከብ ካልተቻለ በጎርፍ መልክ ወደየግድቦቹ የሚገባው ውሃ አፈር ብቻ ሳይሆን ደረቅ ቆሻሻን ጨምሮ የተለያዩ ባእድ የሆኑ ነገሮችን ሰብስቦ ወደ ግድቡ ይገባል። እነዚህ ለግድቦቹ ውሃ የመያዝ መጠን መቀነስ አንዱና ዋና ምክንያቶች ናቸው።

አሁን ካለው የከተማ መስፋፋት ጋር ተያይዞ ከፍተኛ ስጋት እየሆነ የመጣ ጉዳይ ነው።የገፈርሳ ግድብ ከዚህ ቀደም የአርሶአደሮች መኖሪያ፣ ከግብርና ሥራ ውጭ የከተማ አገልግሎት ያልነበረበት አካባቢ ነበር። አካባቢው ለግድብ ሥራም ሲመረጥ ይህንኑ ታሳቢ ያደረገ ነበር። ለገዳዲና ድሬ ግድቦችም አካባቢዎቹ ተመርጠው ግንባታው እንዲከናወን የተደረገው እንዲሁ በተመሳሳይ ሁኔታ ነው። አሁን ላይ ግን አካባቢዎቹ ወደ ከተማ መኖሪያነት በመለወጣቸውና አረንጓዴ ስፍራ መሆኑ በመቅረቱ ለግድቦቹ በደለል መሞላት ስጋት ሆነዋል።

በተለይም ወደ ገፈርሳ ግድብ ከሁለት አቅጣጫዎች የሚገቡ ወንዞች ወይም ተፋሰሶች አሉ። ከሁለቱ በአንደኛው ቡራዩ በሚባለው አካባቢ ተፋሰስ ላይ ሰፊ ቁጥር ያለው ህብረተሰብ በመስፈሩ ወደ ግድቡ የማያስፈልጉ ነገሮች የመግባታቸው እድል በመስፋቱ ስጋቱን ከፍ አድርጎታል።

ተቋሙ በተቻለ መጠን በግድቡ ዙሪያ የአካባቢ ጥበቃ ሥራ በመሥራት ስጋቱን ለመቀነስ ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል። የአካባቢው ወጣቶች በማህበር ተደራጅተው የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት እንዲያከናውኑ፣ ህብረተሰቡንም በማሳተፍ እንዲሁም ከአካባቢ አስተዳደሮች ጋር በመናበብ ሥራ እየተሰራ ነው። ድሬ ግድብ ላይም በተመሳሳይ ባለሥልጣኑ ፕሮጀክት ቀርፆ ከኔዘርላንድ መንግሥት ጋር በመተባበር የተፋሰስ ጥበቃ ሥራ እየሰራ ይገኛል። እንዲህ ያለውን የጥበቃ ሥራ በማስፈት የተጠናከረ ሥራ ለመሥራት እቅዱ ቢኖርም፤ የከተማ መስፋፋቱ እስካለ ድረስ ግን ፈተናውን መቋቋም አዳጋች ይሆናል።

ለግድቦቹ ተፋሰስ በሆኑ ስፍራዎች በስፋት የአካባቢ ጥበቃ ሥራ በመሥራት ወደ ግድቡ ደለል እንዳይገባ መከላከል፤ በተለይም ግድቡ ጠርዝ ድረስ የእርሻ ሥራ እንዳይከናወን፣ መኖሪያቤቶችና ኢንዱስትሪዎች እንዳይስፋፉ ማድረግ ያስፈልጋል። ይሄን ማድረግ የሚቻለው ደግሞ ህብረተሰቡን በማሳተፍ ነው።

አዳዲስ ግንባታዎችን በተመለከተ፤ ባለስልጣኑ በቀን 792ሺ ሜትሪክ ኪዩብ ውሃ የማምረት አቅም ፈጥሯል። ይህን ውጤት ማስመዝገብ የተቻለው በየአመቱ ሥራዎች እየተሰሩ በመምጣታቸው ነው ። ከከርሰ ምድሩም ሆነ ከገፀምድሩ ውሃ የማልማት አቅጣጫ ተቀምጦ እየተሰራ ነው። በተጨማሪም ሱሉልታ አካባቢ ገርቢ ግድብን ለመሥራትም የጥናት፣ ወሰን የማስከበር፣ ቴክኒካል ሥራዎች፣ ኮንትራክተር የመምረጥና ሌሎችም የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች ተጠናቅቋል። የግድቡ ግንባታ የሚከናወነው ከቻይና መንግሥት በሚገኝ የገንዘብ

ወደ ገጽ 10 ዞሯል

# ‹‹ባለፉት አምስት ዓመታት...

ከ ገጽ 9 የዞረ

ብድር ነው። ብድሩ እንደተለቀቀም ወደ ሥራ ይገባል።

ይህ ፕሮጀክት የቆየ ነው። በወቅቱ የተያዘው የሶስት አመት ፕሮጀክት ተብሎ ነበር።የግድብና የማጣሪያ ጣቢያ ግንባታ ሥራዎች እንዲሁም ከማጣሪያ ጣቢያው ወደ ሰሜን አዲስ አበባ ክፍል ኔት ውርክ (መስመር) ዝርጋታንም ያካተተ ነው። ሌሎችም ተጨማሪ ሥራዎች አሉት። በወቅቱም ለሥራው የተቀመጠው የገንዘብ መጠን ወደ 95 ሚሊየን ዶላር አካባቢ ነው። ከግድቡ ስፍራ ወደ አዲስ አበባ ከተማ የሚመጣው ውሃ በበላይ ዘለቀ አድርጎ ድል በር አካባቢ ላይ የመጀመሪያውን ማጠራቀሚያ በማለፍ ሽሮ ሜዳን ቀጨኔ፣ጉለሌ አካባቢን በከፊል ተጠቃሚ የሚያደርግ ነው። በዋናነት በስተሰሜን ያለውን በአዲስ አበባ ከተማ በከፍተኛ ደረጃ ያለውን የውሃ አገልግሎት አቅርቦት ችግር ለመፍታት የሚያስችል ነው።

ነገር ግን ገንዘቡ ባለመለቀቁ ወደ ሥራ አልተገባም። ገንዘቡ ከመንግሥት ጋር በሚደረግ ድርድር የሚፈታ ጉዳይ ነው። ገንዘቡ ቢለቀቅም ለውጦች እንደሚኖሩ ይጠበቃል። ገንዘቡ ከተገኘ ግን ከሁለት አመት ባልበለጠ ጊዜ ማጠናቀቅ ይቻላል። የፕሮጀክት ሥራውን ከዳር ለማድረስ ከሚደረጉ ጥረቶች ጎን ለጎን ባለሥልጣኑ መሥራት የሚጠበቅበትን ሥራዎች አጠናክሮ በመቀጠል የተለያዩ ተግባራትን አከናውኗል።

እየተደረገ ያለው እንቅስቃሴ ምን ያህል ነው? ከተባለ ውሃ አቅርቦት ላይ የተሰጠው ትኩረት አንዱ ማሳያ ነው። ከ2000 ዓ.ም ጀምሮ በተከታታይ ለ15 አመታት ሲሰራ የነበረው የከርሰምድር ውሃ አገልግሎት አቅርቦት ላይ ነበር።

ከዚህ አንጻር እንዴት እየተሰራ እንደሆነ ለማስረዳት ከ2011ዓ.ም ጀምሮ በተከታታይ አመታት ተጨማሪ ውሃ ወደ ከተማው እንዲገባ የማድረግ ሥራ ተሰርቷል።2011 ዓ.ም ኮዬፈጬ ከሚባል የከርሰምድር ውሃ መገኛ፣ 44ሺ ሜትሪክ ኪዩቢክ፣ በ2012 ዓ.ም ደግሞ በከተማዋ ከተለዩ ከፍተኛ የውሃ አገልግሎት አቅርቦት ችግር ባለባቸው ጉድጓድ በመቆፈር 10ሺ ሜትሪክ ኪዩቢክ ውሃ ወደከተማዋ እንዲገባ ተደርጓል። እንዲሁም በ2013ዓም ከቱሉ ጉዶ የከርሰምድር ውሃ መገኛ ፕሮጀክት 68ሺ ሜትሪክ ኪዩብ፣ በተጨማሪም በ2014ዓም ከለገዳዲ ክፍል ሁለት ፕሮጀክት እንዲሁ 86ሺ ሜትር ኪዩብ ከከርሰምድር ውሃ በማውጣት አቅም ተፈጥሯል።

በ2015 ዓ.ም ከፍተኛ የውሃ አገልግሎት አቅርቦት ችግር ያለባቸው በተለይም የጋራ መኖሪያቤቶች ባሉባቸው ፉሪ፣ ሃና፣ በረከት፣ ጀሞ ተብለው በሚጠሩና በሌሎችም ቦታዎች አካባቢውን ያማከለ ጉድጓድ በመቆፈር ወደ 68ሺ ሜትሪክ ኪዩቢክ ውሃ በማውጣት አቅም የመፍጠር ጥረት ተደርጓል። በድምሩ ከ2011 እስከ 2015ዓም ባሉት አመታት ከ275 ሺህ ሜትር ኪዩቢክ ተጨማሪ ውሃ ወደ ከተማዋ እንዲገባ ተደርጓል።

በዚህ መልኩ በየአመቱ ሥራ እየተሰራ ተጨማሪ ውሃ ወደ ከተማዋ እንዲገባ ቢደረግም የከተማው የውሃ ፍላጎት ሊጣጣም አልቻለም። ለመኖሪያም ሆነ ለተለያየ አገልግሎት እየተከናወነ ያለው ግንባታ ወደ ላይ ወይም ፎቅ መሆኑ በውሃ አቅርቦትና በፍላጎት መካከል ክፍተት እንዲፈጠር የራሱ አስተዋጽኦ አድርጓል። የመሬት አቀማመጡም በራሱ ተግዳሮት ፈጥሯል። ለውሃ መገኛ ቅርብ የሆኑና በአቀማመጣቸውም ምቹ የሆኑ አካባቢዎች ብቻ ውሃ የሚያገኙበት፣ ምቹ ባለመሆናቸው፣ ኢንዱስትሪዎች፣ ሆስፒታሎችና ትላልቅ የሚባሉ ፕሮጀክቶች በስፋት በአካባቢው በመኖራቸው ውሃ የማያገኙበት ሁኔታ እየተፈጠረ ነው።

እንዲህ ያለውን ችግር ለመፍታት እንደውሃ መገኛ ሁኔታ የፈረቃ ሥርዓት በመዘርጋት ሁሉም በተራ አገልግሎቱን እንዲያገኝ እየተደረገ ነው። ህብረተሰቡም በሥርዓቱ ውስጥ ገብቶ በአገልግሎቱ ተጠቃሚ የመሆን ዝግጁነቱን አሳይቷል። አሁን ላይ ከህበረተሰቡ እየተነሳ ያለው ከአካባቢ አካባቢ ልዩነት ለምን ተፈጠረ የሚል በፈረቃ አገልግሎት ፍትሐዊነት ላይ ያተኮረ ቅሬታ ነው።

እዚህ ላይ ግንዛቤ መያዝ ያለበት ለከተማው የሚሰራጨው ውሃ ሁሉም ከአንድ ቋት ውስጥ አይደለም። ውሃ ወደ ተለያየ አካባቢ ለማሰራጨት ጥረት ሲደረግ በተለያየ የአሰራር ዘዴ ወይም ሥርዓት ነው። ሌላው ፕሮጀክቶች ሲነደፉ ተልእኮ ወይም ዓላማ አላቸው። ለምሳሌ «የአቃቂ ክፍል ሶስት ለ» የሚባለው በቀን 70ሺ ሜትር ኪዩብ እንዲሰጥ ዲዛይን ተደርጎ የተሰራ ፕሮጀክት ዓላማውም ፕሮጀክቱ የተነደፈውም አቃቂ ገላን አካባቢ ከተቆፈሩ ጉዳጓዶች፣ በምእራብ በኩል ሄዶ፣ ዓለምባንክ



ቤተል አካባቢ ላለ ህብረተሰብ፣ ሰበታ በከፊል ይዞ እስከ ጦር ኃይሎች ድረስ ውሃ ለማቅረብ ነው።

የለገዳዲ ግድብ ደግሞ ማዕከል የተደረገው ምሥራቅ አዲስ አበባ ከተማን፣ሰሜን ደግሞ በከፊል ውሃ እንዲያሰራጭ ነው። ሁሉም የየራሳቸውን ተልእኮ ይዘው ስርጭቱን እንዲያከናውኑ በመደረጉ አይገናኙም። የውሃ ስርጭት ፈረቃው ውሃ የሚገኝበትን መሠረት ያደረገ ነው። በህብረተሰቡ ዘንድ ፍትሐዊ ያልሆነ ስርጭት ያለ እንዲመስል ያደረገው አሰራሩ ላይ ያለውን ሁኔታ ካለመረዳት ነው። አሁን ባለው አሰራር ፈረቃቸው ተጠብቆላቸው ውሃ እያገኙ ያሉ አካባቢዎች ለምሳሌ ከለገዳዲ ግድብ ውሃ የሚያገኙ ክፍለ ከተሞች የካ በከፊል፣ ቦሌ፣ አራዳ፣ ጉለሌ በከፊል፣ ቂርቆስ በከፊል ናቸው። ለገዳዲ ግድብ የኃይል አቅርቦት አጠቃቀሙ አነስተኛ በመሆኑ፤ በዚህ በኩል እንደክፍተት የሚነሳ ነገር አይኖርም። በቀን እስከ 180ሺ ኪዩቢክ የሚያመርተውን ውሃ 24 ሰዓት ያሰራጫል። በእነዚህ አካባቢ የመስመር መሰበርና የተለያየ ችግር ካላጋጠመ በስተቀር ፈረቃቸው እንደተጠበቀ ነው።

ሌላው ለገዳዲ ክፍል ሶስት ለ የሚባለው ሲሆን፤ ይሄም በዓለም ባንክ በኩል አድርጎ፣ጦርኃይሎች፣ ሳርቤት፣ ንፋስልክ ላፍቶ ክፍለከተማ በከፊል ኮልፌቀራኒዮ፣ ቂርቆስና ልደታ አካባቢዎችን ይሸፍናል። በእነዚህ አካባቢዎች ያለውን የውሃ ስርጭት ስምንመለከት ደግሞ አቃቂ ክፍል ሶስት ለ አካባቢ 24 ጉድጓዶች ተቆፍሮ፤ 24 የተለያየ ቦታ ማሰራጫ (ትራንስፎርመር) ተገጥሟል። ጤናማ የሆነ የውሃ ስርጭት እንዲኖር 24ቱም የከርሰምድር ውሃ መገኛዎች ላይ ኤሌክትሪክ መቋረጥ አይኖርበትም። ኤሌክትሪክ ከተቋረጠ አካባቢዎቹ ውሃ የማግኘት እድላቸው የጠበበ ይሆናል።

የከርሰ ምድር ውሃ ከተለያየ ቦታ ተሰብስቦ የሚሰራጭ በመሆኑ፤ በኢኮኖሚውም ቢሆን አዋጭ ካለመሆኑ ጋር ተያይዞ 24ቱም ጉድጓዶች ጀነሬተር እንዲኖራቸው አልተደረገም። የጀነሬተር አገልግሎት የሚያገኙ አራት የውሃ መግፊያዎች ቢኖሩም የጀነሬተሩ የመስራት አቅም ስምንት ሰዓት ብቻ ነው። የመግፋት አቅሙም ከ30 በመቶ በላይ አይደለም። የውሃ አቅርቦቱ በእነዚህ ተግዳሮቶች ውስጥ የሚያልፍ በመሆኑ ፈረቃውን ማስጠበቅ አልተቻለም።

**አዲስዘመን፡- የውሃ መሰረተ ልማት ከፍተኛ ገንዘብ የሚጠይቅ እንደሆነ ይታወቃል።ባለሥልጣኑ ያለው አቅም እንዴት ይገለጻል?**

**አቶ ፍቃዱ፡-** ባለሥልጣኑ ለሰጠው አገልግሎት ከተጠቃሚው የሚሰበሰበውን ገንዘብ የሚያውለው ለአነስተኛ ፕሮጀክቶች ሥራ ካልሆነ በስተቀር በአብዛኛው የሚያውለው ለጥገና እና ለሌሎች ወጭዎች ነው። የልማት ሥራ የሚሰራው ከተማ አስተዳደሩ ከሚሰበስበው ገቢ ውስጥ በሚመድበው ነው። ውሃና ሳንቴሽን መሰረተ ልማት ማስፋፊያ ክፍል ተቋቁሟል። ይሄ ክፍል ተልእኮውን የሚወጣው በየአመቱ ከከተማ አስተዳደሩ በሚመደብለት ገንዘብ ነው።

በተጨማሪም እንደ ዓለም ባንክ ያሉ በዘርፉ ላይ ድጋፍ ከሚያደርጉ ዓለምአቀፍ ተቋማት በሚገኝ ብድር በተመሳሳይ የልማት ሥራ ይከናወናል። የውሃ አቅርቦትን ለመጨመርና ክፍትትን ለመሙላት በጀት የሚገኘው በእነዚህ መንገዶች ነው።

**አዲስ ዘመን፡- አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ከባንቧ ውሃ ቀጥታ ከማግኘት ይልቅ በጀሪካን በግዥ የሚጠቀመው ነዋሪ እየበዛ ነው። ባለሥልጣኑ ይሄን እንዴት ያየዋል?**

**አቶ ፍቃዱ፡-** በከተማዋ አሁንም በፍላጎትና በአቅርቦት መካከል ክፍተት መኖሩ ግልጽ ነው። በዚህ ወቅት ከውሃ አቅርቦት ጋር ተያይዞ ያለው ችግር የኢትዮጵያ ብቻ አይደለም። ከአየር መዛባት እና ከኢኮኖሚ አቅም ጋር ይያያዛል። ከተማው እያደገ ሲሄድ፤ ያንን የሚመጥን ሥራ እየሰሩ መሄድ ያስፈልጋል። እኛም እየሰራን ያለነው በዚህ መንገድ ነው።

ውሃ በጀሪካን መግዛት የሚፈጠረው በሁለት መሠረታዊ ጉዳዮች ነው። አንዱ በሚያጋጥሙ በተለያዩ ምክንያቶች በየቀኑ ቀርቶ ውሃ በፈረቃ ለማድረስ እንኳን የተቀመጠውን አሰራር መተግበር ባለመቻሉ ነው። ሌላው ለልማቱ ሥራ የሚያስፈልጉ ግብአቶች በውጭ ምንዛሪ በግዥ የሚገቡ ከመሆናቸው ጋር ተያይዞ በሚፈጠር ችግር ነው። ያም ሆኖ ግን አሁን ያጋጠሙትን ችግሮች እንደተቋም የሚፈታና የምንሻገረው ነው።

ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በአዲስ አበባ ሰውም፣ ህንጻም፣ አትክልትም የሚጠጡት በተመሳሳይ የታከመ ውሃን ነው። ይሄ የውሃ ብክነትን አያስከትልም?**

**አቶ ፍቃዱ፡-** ትክክል ነው፤ ችግሩ አለ። ሆኖም ግን አሁን ላይ ለይቶ ለመጠቀም የሚያበረታታ ቁርጠኝነት እየታየ ነው። ከመጠጥ ውጭ ለሆኑ አገልግሎቶች የሚውል ውሃ አጣርቶ በማቅረብ ረገድ፤ አሁን ላይ የፍሳሽ ማጣሪያ ጣቢያዎች የተሻለ አቅም ፈጥረዋል። ተጣርቶ የሚወጣው ውሃም በቦኖ እንዲሰራጭ በማድረግ ለተጠቃሚዎች ተደራሽ እየሆነ ነው። በተለይ በከተማዋ ውስጥ እየተከናወኑ ላሉ የአረንጓዴ ልማቶች በስፋት እየዋለ ይገኛል። ውሃ መልሶ የማልማት ክፍል በማቋቋም ባለሙያዎች ተሚልተው በእቅድ እየተሰራ ነው።

የሚጠጣ ውሃ ሽፋን ወይም አቅርቦት የሚፈለገው ደረጃ ማድረስ ሳይቻል፤ የማይጠጣ ውሃን በኔትወርክ ደረጃ ለመሥራት ከፍተኛ የገንዘብ አቅም ይጠይቃል። አሁን ላይ በሁለተኛ የውሃ አማራጭ ላይ እየተሰራ ያለው በሚፈለገው የውሃ ደረጃ ላይ ያሉትን በመለየት ለእጥበት፣ ለአትክልትና ለተለያየ አገልግሎት እንዲውሉ እየተደረገ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በመዲናዋ የመኖሪያ ቤቶችን ጨምሮ ግዙፍ ግንባታ የሚያከናውኑ የውሃ አማራጮችን በራሳቸው እንዲያመቻቹ እየተደረገ ስለመሆኑ ይነገራል።ጉዳዩ ስለሚመራበት ሁኔታ ቢያብራሩልን?**

**አቶ ፍቃዱ፡-** የከተማዋን የውሃ አቅርቦትና ፍላጎት ክፍተት ለመሙላት ሁለተኛ የውሃ አማራጭ ከመጠቀም ጎን ለጎን ባለሥልጣኑ ላለፉት አምስት አመታት ሲሰራባቸው የቆየው ሌላው መንገድ ከፍተኛ የውሃ ተጠቃሚዎች፣ የመጠጥ ውሃን ለመጠጥ ብቻ ሳይሆን ለሌም የሚያውሉ አካላት ጉድጓድ በመቆፈር በራሳቸው ውሃ አመንጭተው እንዲጠቀሙ የማበረታታት ሥራ ሲሠራ ነበር። ከነዚህ አካላት ጋርም ቀድሞ በመመካከር እንዴት መደጋገፍ ይቻላል? በሚለው ላይ ወደ ትግበራ የገባው መክሮ ነው።

ቀደም ሲል በነበረው አሰራር ከርሰ ምድር ለመቆፈር ፍቃድ የሚሰጠው የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ነበር። በአሁኑ ጊዜ ግን ፍቃድ የሚሰጠው ባለሥልጣኑ ነው። ሶስተኛ ወገንም ሆነ ባለሥልጣኑ ለሚያለማው ውሃ ፍቃድ ከባለሥልጣኑ ማግኘት ይኖርበታል።የማስተዳደር ስልጣንም በአዋጅ ተሰጥቶታል። በዚሁ መሠረት ከ2011 ዓ.ም በኋላ በስፋት ሥራዎች ተከናውነዋል። የህብረተሰቡም ተሳትፎ እየጨመረ መጥቷል። ባለስልጣኑ ፍቃድ መስጠት ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ከ2012 ዓ.ም እስከ 2015 ዓ.ም ባሉት አመታት ለ388 ለተለያዩ ድርጅቶች ጉድጓድ የመቆፈር ፍቃድ ሰጥቷል። ፍቃድ ከወሰዱት መካከል ደግሞ 163 ደንበኞች የአጠቃቀም ፍቃድ ወስደዋል።

በፍቃድ አሰጣጥ ሂደትም፤ በአካባቢው ላይ በአምስት መቶ ሜትር ክልል ውስጥ ቀድሞ የተቆፈረ ጉድጓድ አለመኖሩና የሚቆፈረው ጉድጓድ የአካባቢውን ማህበረሰብ ጥቅም የማይጎዳና ችግር የማያስከትል መሆኑ ይታያል። እንዲሁም የህብረተሰብ ጥቅም የሚቀድም በመሆኑ እንደሆስፒታል ያሉ ለማህበረሰቡ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ቅድሚያ እንዲያገኙ የእነርሱን ፍላጎት ማረጋገጥ፤ ባለሥልጣኑም በአካባቢው ላይ ጉድጓድ ለመቆፈር የያዘው እቅድ አለመኖሩ ቀድሞ ይረጋገጣል።

**አዲስ ዘመን፡-የሰው የአኗኗር ዘይቤ መቀየሩ በውሃ አቅርቦቱ ላይ ጫና አሳሳደረም ?**

**አቶ ፍቃዱ፡-**የሰው የአኗኗር ዘይቤው በመቀየሩ የውሃ ፍላጎትም ጨምሯል። የውሃ ልማት ሥራ ፈታኝ ነው የሚባለው ለዚህም ነው። ባለፈው አመት በስድስት ወር ውስጥ በተሰበሰበ መረጃ በቀን እስከ 200 ሊትር ውሃ የሚጠቀም የህብረተሰብ ክፍል መኖሩ ተረጋግጧል።በተለይም ወደ ላይ ከፍታ ያላቸው ፎቆች መብዛታቸው ስርጭቱን አዳጋች አድርጎታል።ለባለስልጣኑ ፈተና የሆነው በአዋጅ በተሰጠው ስልጣን ሊያቀርብ የሚገደደው ከፍታ የመውጣት የግፊት መጠኑ ከአስር ሜትር ያልበለጠ መሆን እንዳለበት ነው። ባለ አንድ ወለል (ግራውንድ ፕላስ ዋን) ቤት የሚደርስ ማለት ነው። ከዚህ በላይ ላለው ፍላጎት የተጠቃሚው ኃላፊነት ነው። መሬት ላይ ወይንም ከጣሪያ በላይ የውሃ ማጠራቀሚያ በመስቀል ችግሩን ማቃለል ይኖርበታል።

አማራጭ በመውሰድ በኩል ችግሩ ጎልቶ የሚታየው በጋራ መኖሪያ ቤቶች ነው።ለባለስልጣኑ ከሚቀርቡ ቅሬታዎችም የጋራ መኖሪያ ቤቶች ከፍተኛውን ድርሻ ይይዛሉ።እኛ ግን አሁንም መልእክት እንዲተላለፍልን የምንፈልገው ባለሥልጣኑ በአዋጅ ከተሰጠው ስልጣን ውጭ መንቀሳቀስ አይችልም። አማራጩን ይጠቀሙ። አስፈላጊውን ምክር አገኝተው ወደ ተግባር በመግባት ችግራቸውን ያቃልሉ። አስፈላጊ ከሆነም በምክር እናግዛለን። ውሃ ለጋራ መኖሪያ ቤት የንጽህናም ጉዳይ በመሆኑ ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል።

**አዲስዘመን፡- ታሽጎ ለገበያ የሚቀርብ ውሃ መበራከት ባለሥልጣኑ በሚሰጠው የውሃ አገልግሎት ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተጽእኖ ይኖር ይሆን?**

**አቶ ፍቃዱ፡-** ባለሥልጣኑ በሚሰጠው አገልግሎት ላይ የሚኖረው ተጽእኖ የለም። አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ከምናመነጨው ውሃ ጋር አይገናኝም። መገኛቸው ከአዲስ አበባ ከተማ ውጭ ነው። አቅርቦቱ ክፍተት ሊሸፍን ይችላል። ነገር ግን የዋጋ ጉዳይ ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል ተጠቃሚ ስለማያደርግ ሊያማርር ይችላል። ቀደም ሲል በነበረው ታሪፍ ባለሥልጣኑ አንድ ሜትር ኩብ ውሃ በአንድ ብር ከ75 ሳንቲም እና በሁለት በር ከ40 ሳንቲም እያቀረበ አንድ ሊትር የታሸገ ውሃ እስከ 20 ብር የሚሸጥ ከሆነ የህብረተሰብን የውሃ አቅርቦት ጥያቄ መልሷል ለማለት አያስደፍርም።

መንግሥት የመጠጥ ውሃ አግልግሎትን የሚያቀርበው በድጎማ ነው። ውሃ መሰረታዊ ነገር ስለሆነ መቅረብም ያለበት በዚህ ደረጃ ነው። መዘንጋት የሌለበት ለህዝብ ጥቅም ሲባል በግለሰቦች የለማ ውሃ እንኳን ቢኖር ባለሥልጣኑ ወርሶ ለተጠቃሚው ማቅረብ እንደሚችል በአዋጅ ስልጣን ተሰጥቶናል። በመሆኑም ከውሃ አቅርቦት ጋር በተያያዘ በባለሥልጣኑ አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የገጠመ ፈተና የለም።

**አዲስዘመን፡- በሥራ ያጋጠሙ ተግዳሮቶች፣ ጠንካራ ጎኖች እንዲሁም ስክፍተቶቹ የተሰጠ መፍትሄ ላይ ሃሳብ ቢሰጡን?**

**አቶ ፍቃዱ፡-** የባለስልጣኑ ትልቁ ተግዳሮት በውሃ አቅርቦትና በፍላጎት መካከል ባለመጣጣሙ እርካታ ማምጣት አለመቻሉ ነው። ይህ መሰረታዊ ችግር ተደርጎ ይወሰዳል። ሌላው የውሃ መሰረተ ልማት ላይ የጥንቃቄ መጓደል ነው። ውሃ መሥመር ላይ ግንባታዎች ይከናወናሉ። ወደ መሰረተ ልማቱ መግቢያ ላይ አጥር በማጠር መግቢያ ማሳጣትና በዚህም ልማቱን የማስተጓጎል ሁኔታ ያጋጥማል። ውሃ ለማልማት የወሰን ማስከበር ችግርም አለ። የውሃ መስመሮች በተዘረጉባቸው ጋራዦችና ሌሎችም አገልግሎቶች ማከናወን አንገብጋቢ ላልሆኑ ነገሮች ውሃ በመጠቀም ማባከን፣ በቁጠባ አለመጠቀም አለ።

ለችግሮች ባለሥልጣኑ ያስቀመጠው መፍትሄ የከተማዋን ውሃ ፍላጎትና አቅርቦት ለማቅራረብ የአስር አመት ስትራተጅ እቅድ ነድፎ እየሠራ ይገኛል። ቀደም ሲል የጠቀስኩት ገንዘብ እስኪለቀቅ ከሚጠበቀው የገርቢ ግድብ ግንባታ በተጨማሪ 500ሺ ሜትር ኪዩብ በቀን የማምረት አቅም ያለው ሲቢሎ የተባለ ግድብ ፕሮጀክት የጥናት ሥራ ተጠናቅቆ የቀረው ገንዘብ የማፈላለግ ሥራ ነው። እንዲሁም በቀን 600 ሺ ኪዩቢክ ውሃ በቀን ማምረት የሚችል ዓለም ቱጂዶ ፕሮጀክትም የጥናት ሥራ በመጠናቀቅ ላይ ይገኛል። እነዚህ ሁሉ በአስር አመት እቅድ ውስጥ የተካተቱ ናቸው። ከከርሰ ምድርም በተመሳሳይ ውሃ የማውጣቱ ሥራ ይጠናከራል። በእቅዱ መሰረት ሥራዎች ከተከናወኑ ከተማዋ የተሻለ የውሃ አቅርቦት ይኖራታል።

**አዲስ ዘመን፡- ስነበረን ቆይታ እናመሰግናለን።**

**አቶ ፍቃዱ፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

ስፖርት እና መዝናኛ

# ፋሽን

## «ቀሲል» - የተፈጥሮ ውበት መጠበቂያ

**ወርቅነሽ ደምሰው**

በሀገራችን ተፈጥሯዊ የውበት መጠበቂያዎችን መጠቀም የተለመደ ነው። በተለይ ዘመናዊ መዋቢያዎች ከመምጣታቸው በፊት ከተፈጥሮ ንጥረ ነገሮች በባህላዊ መልኩ የሚዘጋጁ መዋቢያዎች በብዛት ጥቅም ላይ ይውሉ ነበር። አሁንም ቢሆን በአብዛኛው የገጠራቱ አካባቢዎች የተለያዩ የተፈጥሮ መዋቢያዎች በቤት ውስጥ እየተዘጋጁ ጥቅም ላይ ይውላሉ። ለእዚህም ወሎ አካባቢ በሴቶች ዘንድ በስፋት ጥቅም ላይ የሚውለውን የወይባ ጭስ በአብነት መጥቀስ ይቻላል።

ዘመናዊ የውበት ሳሎኖች በተበራከቱባቸው ከተሞችም ቢሆን በዘመናዊና በባህላዊ መልኩ የተዘጋጁ መዋቢያዎችን እናገኛለን። ይህም ተጠቃሚዎቹ የፈለጉትን አይነት መዋቢያ መርጠው እንዲጠቀሙ አማራጭ ይፈጥርላቸዋል። ምንም እንኳን በከተሞች አካባቢ በዘመናዊ መንገድ መዋብና ማጌጥ የተለመደ ቢሆንም፣ አሁን አሁን የተፈጥሮ መዋቢያዎች በብዙዎች ዘንድ በብዛት ተመራጭ እየሆኑ መምጣታቸውን ይስተዋላል።

በተለምዶ የፊት ቆዳንም ሆነ ሌሎች የሰውነት ክፍሎችን ውበት ለመጠበቅ የምንጠቀምባቸው የተፈጥሮ መዋቢያዎች በአብዛኛው ከተለያዩ እጸዋት ዝርያዎች የሚቀመሙ ናቸው። የእጸዋቱን ቅጠል፣ ፍሬ፣ ስር እና መሰል ነገሮች በማዋሀድ ለውበት መጠበቂያ እንዲውል ሲደረግ ይታያል።

ኬሚካል የተቀላቀለባቸው የፋብሪካ ምርቶችን መጠቀም የራሱ የሆነ ጥቅም ቢኖረውም የጎንዮሽ ጉዳት ሲያስከትልም ይስተዋላል። እንደሚታወቀው በኛ ሀገር በባህላዊ መንገድ የሚዘጋጁ ውበት መጠበቂያዎች የቆዩና በጥንት ጀምሮ በቤት ውስጥ እየተዘጋጁ እናቶቻችን ሲጠቀሙባቸው ቆይተዋል፤ አሁን እየተጠቀሙት ይገኛሉ። ፡ እነዚህ መዋቢያዎች ከተፈጥሮ ውህዶች የሚሰሩ ስለሆኑ በአካባቢያችን ላይ በቀላሉ ሊገኙ የሚችሉ ናቸው። የጎንዮሽ ጉዳት ይዘውብን ይመጣሉ የሚል ስጋትን የሚያስቀሩና አዘገጃጀታቸውም ሆነ አጠቃቀማቸው በጣም ቀላል እንደሆነ በብዙዎች ዘንድ ይነገራል።

የፊትን ፣ የቆዳን፣የጽጉርን፣ የእጅና የእግር ጥፍርን፣ የሰውነት ቆዳን እና ሌሎችን የሰውነት ክፍሎች ለማስዋብ የሚያገለግሉ ከተፈጥሮ ነገሮች የሚዘጋጁ ባህላዊ መዋቢያዎች በርካታ ናቸው። መዋቢያዎቹ በዱቄት፣ በፈሳሽ እና በጭስ እና በመሳሳሉ መልክ ተዘጋጅተው የሚቀርቡ ሲሆን፤ አብዛኞዎች በቀላሉ በቤት ውስጥ የሚዘጋጁ ናቸው። እንዲሁም ማንኛውም ሰው በሚፈልገው መልኩ አዘጋጅቶ በቀላሉ ሊጠቀምባቸው ይችላል። እንደ እንሶስላ ወይም እንሾሽላ፣ ወይባ ጢስ እና ቀሲል አይነቶቹ ከተፈጥሮ ነገሮች የሚገኙ መዋቢያ በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች በሚባል ደረጃ ይታወቃል።

በዛሬው የፋሽን ገፅ አምዳችን በስፋት ልንዳስሰው ያሰብነው የተፈጥሮ ውበት መጠበቂያ በምስራቁ የሀገራችን ክፍሎች በደንብ ጥቅም ላይ እየዋለ የሚገኘው "ቀሲል"ን ነው። መጠሪያው የተወሰደው ከሶማሊኛ ቋንቋ ነው። ይህ ዱቄት መሰል መዋቢያ በድሬዳዋና በጅግጅጋ አካባቢዎች በስፋት ይታወቃል። በእነዚህ አካባቢዎች የሚገኙት ሰዎችም ውበታቸውን ለመጠበቅ ይጠቀሙበታል። በተለይ የፊት ቆዳን ለማስዋብ ፍቱን እንደሆነ ይነገራል። በተለያዩ ምክንያቶች ጉዳት የደረሰበትን የፊት ቆዳ ይህንን ተፈጥሯዊ መዋቢያ በተደጋጋሚ በመጠቀም በሂደት ለውጥ በማምጣት ውበት ለመጠበቅ እንደሚያስችል ተጠቃሚዎች ይጠቁማሉ።

"ቀሲል" ቅጠሉ ሲሆን ለመዋቢያ የሚያገለግለው ቅጠል ደርቆና ተፈጭቶ ዱቄት ከሆነ በኋላ አገልግሎት ላይ ይውላል። የቀሲል ዱቄት ቀለሙ አረንጓዴ ነው፤ አጠቃቀሙ ዱቄቱ ከእርድ ጋር ተደባልቆ በውሃ ከተበጠበጠ በኋላ ውህዱን የፊት ቆዳን በመቀባት ውበትን መጠበቅ የሚያስችል ነው።

ወጣት ቤተልሔም የውብሸት ነዋሪነቷ በድሬዳዋ ከተማ ሲሆን ይህንን የተፈጥሮ መዋቢያ ታዘወትራለች። ቀሲልን ከእርድ እና ከውሃ ጋር ደባልቃ በመጠቀም የፊቷን እና የእጇቿን ውበት ትጠብቃለች። ይህንን መዋቢያ ቢያንስ በሳምንት ሁለት ጊዜ እንደምትጠቀም ወጣት ቤተልሔም ትናገራለች።

እሷ እንደምትለው፤ቀሲል ተፈጥሯዊ መዋቢያ ስለሆነ ብዙዎች ይጠቀሙታል። በተለይ ፊታቸው ላይ የተለያዩ ነጠብጣብ ነክ ነገሮች እና ማዲያት ያለባቸው ሰዎች በብዛት ይፈልጉታል ትላለች።

እሷ እንደምትለው፤ ቀሲል በገበያ ላይ በተመጣጣኝ ዋጋ የሚቀርብ በመሆኑ ማንኛውም ሰው በቀላሉ ገዝቶ ሊጠቀምበት ይቻላል። ተፈጥሯዊ በመሆኑም ምንም አይነት የጎንዮሽ ጉዳት በፊት ቆዳ ላይ አያስከትልም። ቀሲል ለፊት ቆዳ ውበት መጠበቂያ የሚያገለግል ተፈጥሯዊ ንጥረ ነገር ያለው በመሆኑ በተለይ ለሴቶች የፊት ቆዳ ተስማሚ ነው። በዚህ ምክንያት አብዛኛዎቹ ሴቶች እንደሚጠቀሙት ትናገራለች። አሁን ላይ ይህንን ተፈጥሯዊ መዋቢያ ሌላ አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች ገዝተው ሲጠቀሙበት ማየቷን ትናገራለች።

ቀሲል ሁሉም ሰው በቤቱ ውስጥ አዘጋጅቶ ሊጠቀመው የሚችልና አጠቃቀሙም ቀላል ነው የምትለው ቤተልሔም፤ አንድ ቀሲልን የምትጠቀም ሴት የቀሲሉን ዱቄት ከገዛች በኋላ እንደምትጠቀመው መጠን ብዛት የቀሲሉን ዱቄት ከእርድና ውሃ ጋር በማዋሀድ እንዳይቀጥንም በጣም ወፍራም እየመጠነች በመጨመር ፊቷ ለአንድ ጊዜ መቀባት እንዲያስችላት ውህድ አዘጋጅታ መጠቀም ትችላለች። ቀሲል ውበትን ከመጠበቅ ባሻገር ዘርፈ ብዙ ጥቅም እንዳለው ይታመናል።

እንደ ቤተልሔም ገለፃ፤ ከጥንት ጀምሮ እስካሁን ድረስ ጥቅም ላይ እየዋለ የሚገኘው ይህ ተፈጥሯዊ ውበት መጠበቂያ በሌሎች አካባቢዎች በጥቂቱ ቢኖርም በጅግጅጋና በድሬዳዋ አካባቢ ያሉት ነዋሪዎች በስፋት እየተጠቀሙበት ይገኛሉ። በፋብሪካ የተቀነባበሩት ውበት መጠበቂያዎች እንደ ቀሲል ብዙ ሰዎች እንዳይጠቀሟቸው የሚያደርገው ይዘው የሚያመጡት የጎንኛሽ ጉዳት መሆኑንም ታነሳለች።

ቤተልሔም እንደምትለው፤ በዘመናዊ መልኩ የሚመጡ የውበት መጠበቂያ "ሜካፖችን" የሚጠቀሙ ብዙ ሰዎች አሉ። መጠቀሙ ጥሩ ሆኖ ሳለ የሚያመጡት የጎንዮሽ ጉዳትም ታሳቢ መደረግ አለበት። እንዲሁም ከዋጋ አንጻር ከውጭ ሀገር በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ የሚገቡ በመሆኑ ከጊዜ ወደ ጊዜ ተጠቃሚውም ሲጨምር ዋጋቸው እየናረ መጥቷል። አሁን ላይ ባለው ሁኔታ የመዋቢያዎቹ ዋጋ የህብረተሰቡን አቅም ያገናዘበ ስላልሆነ ብዙ ሰዎች ውበታቸውን መጠበቅ እየፈለጉ የሚተውበት ሁኔታ ያጋጥማል።

"ይህንንና መሰል ሀገር በቀል ተፈጥሯዊ መዋቢያዎችን ማስፋፋት ቢቻል ከራስ አልፎ ለሌላው መትረፍ ይቻላል" የምትለው ቤተልሔም፤ በቀላሉ በቤታችን አዘጋጅተን መጠቀም ስንችል ለአላስፈላጊ ውጪ መዳረግ እንደማይገባም ትናገራለች። ባህላዊ የውበት መጠበቂያዎችንና እሴቶችን ጠብቆ ለትውልድ የማስተላለፍ ኃላፊነት የሁሉም እንደሆነም ትገልፃለች። በባህላዊ መንገድ የሚዘጋጁና በቀላሉ ማግኘት የምንችላቸው ተፈጥሮዊ መዋቢያዎችን መጠቀም መልመድ ጠቀሜታ እንዳለው ትገልጻለች። ከዚህ አለፍ ሲል ደግሞ ለሌሎችም እንዲተዋወቅ ማድረግን እንደሚጠይቅ ጠቅሳ፣ ከዚህ አኳያ ብዙ ሥራዎች መስራት እንዳለባቸው አመልክታለች፤ ፋሽን እየተባለ ከውጭ ለሚመጣው ብቻ ትልቅ ዋጋ ከምንሰጥ የራሳችንን ማበረታታት ይገባል ስትል ምክረ ሃሳቧን ትለግሳለች።

# ትዝብት/ ማረፊያ

## ወላጆችም ይማሩ!

**ዋስልኝ አየለ**

ከዓመታት በፊት ለበዓል ወደ ቤተሰብ በሄድኩበት አጋጣሚ አንድ መምህር ጓደኛዬን አግኝቼው ያጫወተኝ ነገር በትምህርት አጋጣሚዎች ሁሉ ትዝ ይለኛል። ይህ ጓደኛዬ አብረን የተማርን ሲሆን እሱ እዚያ የተማርንበት ትምህርት ቤት ውስጥ መምህር ሆነ። በተገናኘን ቁጥር ያለፈ ትዝታችንን እያነሳን እንጫወታለን። ከዓመታት በፊትም ተገናኝተን ተጫወትን።

በጨዋታችን ውስጥም ያው ‹‹ሥራ እንዴት ነው?›› የሚለው በሁለታችንም በኩል ተነሳ። በተገናኘን ቁጥር የሚነግረኝ ነገር የተማሪዎችን ጎበዝ አለመሆን ነበር። እኔም የቅርብ ጓደኛዬ ስለሆነ ‹‹መምህሩ ጎበዝ ሲሆን ነው ተማሪ ጎበዝ የሚሆን›› እያልኩ በቀልድም በቁም ነገርም እነግረዋለሁ። እሱም ‹‹ስላላየኸው ነው የምትፈርድ! ምንም ማንበብና መጻፍ የማይችልን ተማሪ ከየት ጀምሮ ነው ጎበዝ ማድረግ የሚቻል›› እያለ ይሞግተኛል (እሱ የሚያስተምረው ሁለተኛ ደረጃ ነው)። ይሄም ከታች ክፍል ያሉ መምህራን ችግር ነው እየተባባልን እንከራከራለን።

በዚያ ዓመት የነገረኝ ነገር ግን ከዚህም ከበድ ያለ ሆነ። ‹‹ተማሪዎችን ‹ምን መሆን ትፈልጋላችሁ?› ብትላቸው፤ እንደ ድሮው ‹ዶክተር፣ ኢንጂነር...› የሚሉ እንዳይመስልህ! ምኞታቸው፤ ሴቶች ወደ አረብ ሀገር፣ ወንዶችም ወደ ወርቅ ቁፋሮ ነው የሚሉህ›› አለኝ። ምኞታቸው ብር የሚያገኙበትን አጋጣሚ ማመቻቸት ነው። ትምህርት የማይማሩ ጓደኞቻቸው ሄደው የመጡበት አካባቢ መሄድ ነው ፍላጎታቸው። ወላጆችም ገንዘብ ካመጡልን በማለት ብዙም አይቆጧቸውም፤ እንዲያውም ይባስ ብሎ የሚፈቅዱላቸውና ሂዱ የሚሏቸውም አሉ። ቁጥራቸው በዛ ያለው ከ5ኛ ክፍል በታች ያሉት ናቸው። እነሱም ዕድሜያቸው ገና ለመሄድ ስላልደረሰ ነው።

ይሄ የመሄድ ፍላጎት ገና በልባቸው ሲጠነሰስ ለትምህርቱ ትኩረት አይሰጡም። መሄድ ሳይችሉ ቢቀሩ እንኳን ፈተና አያልፉም። እንኳን ሀገር አቀፍ ፈተናዎች ላይ የክፍል ውስጥ ፈተና እንኳን የሚያመጡት ውጤት ዝቅተኛ ነው።

ከዚህም በላይ አሳዛኙ ደግሞ የተማሪዎች ብቻ ሳይሆን የመምህራኑም ተስፋ መቁረጥ ነው። ‹‹ምክንያቱ ምን ይሆን›› ያልኩት ጓደኛዬ እንደሚለው የብዙ መምህራን ቅሬታ ከደመወዝና ጥቅማጥቅም ጋር፣ ከሥራ መሰላቸት ጋር የመጣ ነው። የሥራ መሰላቸቱንም ያመጣው ከኑሮ ውድነት ጋር የሚከፈለን ክፍያ አይመጣጠንም በሚል ቅሬታ ነው።

ይሄ ነገር ትውልድ ገደላ ነው። መምህራን መንግሥት ላይ ያላቸውን ቅሬታ የሚገልጹት ተማሪ ላይ ከሆነ ይሄ የእውቀት አባትነት ሳይሆን ጨለማን ማውረስ ነው። እርግጥ ነው የሚከፈለው ክፍያ በቂ ነው ማለት አይደለም። በቂ አለመሆኑ ግን የተማሪዎችና የወላጆች ችግር አይደለም፤ የመንግሥት ችግር ነው። ያንን ከመንግሥት ጋር ነው መነጋገር። እልሃቸውን ተማሪ ላይ አይደለም መወጣት ያለባቸው። የጠየቁት ጥያቄ ካልተመለሰ ወይም በውይይት መፍትሔ ላይ ካልደረሱ ሥራውን መልቀቅና የተሻለ ካለ መፈለግ ነው!

በነገራችን ላይ ይሄ ችግር የሚታየው መምህራን ላይ ብቻ አይደለም። በብዙ የመንግሥትም ሆነ የግል ተቀጣሪ ሰራተኞች ላይ የሚታይ ነው። የግል ትምህርት ቤት ላይ ቢዝረከረክ በነገታው እንደሚባረር ስለሚያውቀው ማንም አይዝረከረክም። የመንግሥት ተቋማት ላይ ግን ይሄ ነገር ጎልቶ ይታያል። ብዙ ጊዜ የታዘብኩትን ነገር ልንገራችሁ።

የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ሾፌር ይቀጥራሉ። ሹፌሮችም ሠራተኞችን ወደ ሥራ ቦታ ይወስዳሉ። ይህ ሲሆን ታዲያ ሾፌሮች በለቅሶና በጭቅጭቅ ነው። ከመስሪያ ቤት ሲወጡ አለቃቸው ያዘዛቸውን ‹‹እሺ›› ብለው ይወጣሉ። ከዚያ በኋላ ከሠራተኛው ጋር ጭቅጭቅ ይፈጥራሉ። ‹‹እዚህ ቦታ አልሄድም፣ በዚህም አልሄድም፣ እዚህ አልጠብቅህም›› ይላሉ። ይባስ ብሎ በፉከራ ‹‹ማን አባቱ ነው የሚያዝዘኝ፣ እስኪ ማን እንዲህ አድርግ እንደሚለኝ አያለሁ!›› እያሉ ፉከራ!

የቅሬታቸውን ምክንያት ሲናገሩም፤ ‹‹በዚህ ደመወዝ አልሰራም! አንተ ይህን ያህል እየተከፈለህ እኔ ልፈጋልህ ነው!›› እና ታዲያ ሥራውን ለቆ የተሻለ ካለ መፈለግ ነዋ!

ወደ መምህራኑ ስንመለስ የእነርሱ ደግሞ ከዚህም ይከፋል። የእነርሱ ማኩረፍ እንደሌላው ማኩረፍ አይደለም። ትውልድ ላይ ነው እየሰሩ ያሉት።

የተማሪዎች ተስፋ መቁረጥ ግን የመምህራን ችግር ብቻም አይደለም። ይሄ የወላጆችም ችግር ነው። አለፍ ሲልም የትምህርት ዋጋ ማጣት ነው። ከእነርሱ በፊት የተማሩ ሲያማርሩ ከሰሙ ከታች ያሉት ተስፋ ይቆርጣሉ። ተምሮ ሥራ የለም፤ በደመወዝ መኖር ከባድ ነው፣ ሥርዓተ ትምህርቱ ሀገር በቀል እውቀት ላይ ያተኮረ አይደለም... የሚሉ ቅሬታዎች ተደጋግመው የሚሰሙ ናቸው። ታዲያ ይሄን እየሰሙ ይሆን?

የትምህርት ነገር ገና ብዙ ያልተስተካከለ ነገር አለው። በቅርብ ዓመታት በወጣው የትምህርት ፍኖተ ካርታ ላይ ከአንደኛ ደረጃ ጀምሮ ዲግሪ ያለው ይሆናል ተብሏል። ይሄ ጥሩ ነገር ነው። የመምህራን ብቃትና ቁራጥ ውሳኔም አንዱ አጠያያቂ ነገር ስለነበር። ከ10ኛ እና ከ12ኛ ክፍል ውጤት ያልመጣለት ተማሪ ነበር እኮ መምህር የሚሆነው! ከዩኒቨርሲቲ የተመረቀውም ቢሆን ብዙም የተሻለ አይደለም። ባዮሎጂ፣ ኬሚስትሪ፣ ፊዚክስ ትምህርት ክፍል የሚመደቡት ከ12ኛ ክፍል ዝቅተኛ ውጤት ያመጡት ናቸው። እነዚህ ወሳኝ እና ለሁሉም የትምህርት ክፍል መሰረት የሆኑት የትምህርት አይነቶች ከዚህ በፊት በነበረው አሰራር ‹‹ኮምፒቴሽናል ሳይንስ›› በሚለው ውስጥ ናቸው። ይሄ ዘርፍ ማለፊያ ነጥቡን ብቻ ያመጡ ተማሪዎች ሳይመርጡት የሚመደቡበት ነው። እንደ ህክምና፣ ምህንድስና፣ ጤና፣ መሬት አስተዳደር፣ የመሳሰሉ የትምህርት ክፍሎችን መርጠው የሞሉ ተማሪዎች ያንን ካላገኙ የሚመደቡት ‹‹ኮምፒቴሽናል›› እና ‹‹አዘር ሳይንስ›› የሚባለው ውስጥ ነው። መምህር የሚወጣው ደግሞ ከዚህ ዘርፍ ውስጥ ነው። አሁን ግን በመጀመሪያው ዓመት ጠቅላላ የሆነውን ነገር ተምረው ከዚያ በኋላ ነው የሚመርጡት።

የትምህርት ክፍሎችን አወቃቀር ለአሰራሩ እንተወውና ወደ ተማሪዎች የትምህርር ፍላጎት እንመለስ። ይህን ነገር ብዙ ሰው በአዲስ አበባ ዓውድ ካየው ልክ ላይሆን ይችላል፤ ምክንያቱም ትልልቅ ከተሞች ውስጥ ያሉ ተማሪዎች የተሻለ (ቢያንስ የማንበብና የመጻፍ) ችሎታ ይኖራቸዋል። የትምህርት ሚኒስትሩ ከአንድ ዓመት በፊት እንደገለጹት፤ ምንም መጻፍና ማንበብ የማይችሉ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ተገኝተዋል። ስሌቱንም በመቶኛ ሲያስቀምጡት ነበር፤ ያ መደገም የለበትም።

ትምህርት ሚኒስቴር ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ከአንደኛ ደረጃ እስከ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ብዙ ማሻሻያዎችን አድርጓል። ይህ ትልቅ ለውጥ ነው፤ ዳሩ ግን የልጆቹና የወላጆች አመለካከት ላይ ደግሞ መሰራት አለበት። ዛሬም ቅስቀሳ የሚፈልግ ወላጅ ያለበት አካባቢ አለ። እነዚያ ልብ መባል አለባቸው። በከተሞቹ ዓውድ ብቻ መታየት የለበትም። አንዳንድ ወላጆችና ልጆች ወደ ትምህርት ቤት በጊዜ የማይሄዱት ከሥርዓተ ትምህርቱ ጋር በተያያዘ ጉዳይ አይደለም፤ በአመለካከት ነው። የሥርዓተ ትምህርቱ መሻሻል ብቻውን የነበረውን የተዛባ አመለካከት አይቀይረውምና ዛሬም ግንዛቤ ሊሰጣቸው የሚገባ አሉ። ልጆቻቸውን ወደ ትምህርት ቤት የማያስገቡ ወላጆችንም ማንቃት አስፈላጊ ነው። ‹‹በዚህ ዘመን ልጁን የማያስገባ አለ እንዴ?›› ማለት የተሳሳተ ግምት ነው። ለዚህ የተሳሳተ ግምት የሚዳረገው ደግሞ በከተማው ዓውድ ብቻ የሚረዳ ሰው ነው። በዚህ ላይ አሁንም ዘመቻ ያስፈልጋልና ልጆች ወደ ትምህርት ቤት እንዲሄዱ ቅስቀሳ ሊደረግ ይገባል!

# አዲሱን ዓመት በአዲስ ልብ

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጽ)**

አዲስ አመትን በአዲስ ልብ ካልተቀበልነው አሮጌ ነው። አዲስ አመት አዲስ የሚሆነው እኛ በአስተሳሰብ ስንልቅና አዲስ ስንሆን ብቻ ነው። የሰው ልጅ ታሪክ አለው..ታሪክ ደግሞ በጊዜና በዘመን ውስጥ ያልፋል። የእያንዳንዳችን ታሪክ ከውልደት የሚጀምር በሞት የሚጠናቀቅ የዘመን ሀቅ ነው። ይህ ተፈጥሮአዊ እውነት ደግሞ የሰውን ልጅ ማረፊያ አድርጎ በተቀመጠለት የሥርዓት አውድ ውስጥ እየመጣ የሚሄድ ነው።

ጊዜ ሀጂውን እየሸኘ..መጪውን እየተቀበለ በማይዛነፍ ፍጹም እውነት ውስጥ ይጓዛል..የሰውን ልጅ ጉዳይ አድርጎ። ጊዜ ጌታ ነው..ጊዜ ፈራጅ ነው። ጊዜ መጽናናት መሻርም ሁሉንም ነገር ነው። በተፈጥሮ እውነት የጸና..በሚዛናዊነት ምህዋር ውስጥ ሳይንገዳገድ የቆመ መለኮታዊ ጽኑ ቃል ነው።

የጊዜ ጌትነት ግን በራሱ የሚሆን ሳይሆን በሰው ልጅ የማሰብ አቅም የሚወሰን የአእምሮ ነጸብራቅ ነው። የእያንዳንዳችን ትናንት የእያንዳንዳችን ዛሬና ነገ፣ የእያንዳንዳችን ድሮና ዘንድሮ፣ አምናና ካቻምና በዚህ በጊዜና በሰው ልጅ የጋርዮሽ መስተጋብር የተቃኘ ነው።

የሰው ልጅ በጊዜ ውስጥ ባለታሪክ ነው። ጊዜ በሰው ልጅ ውስጥ ጉልበታም ነው። የጊዜና የሰው ልጅ ቁርኝት ታሪክን እየደገመ፣ ተፈጥሮን እያጣቀሰ የሚያዘግም ነው። ጊዜ የታሪክ መፈጠሪያ፣ የህልምና ምኞት ካዝና ነው። የምንፈልጋቸው ነገሮች በጊዜ ውስጥ አልፈው የእኛ የሚሆኑ ናቸው።

ካለጊዜ ሰው፣ ካለሰው ጊዜ ምንም ናቸው። ጊዜና የሰው ልጅ እጅና ጓንት፣ መዳፍና አይበሉባ፣ መረብና አሳ ናቸው። ሁለት አካል አንድ ገጸ ሰብ፣ ሁለት ገላ አንድ አይነት መልክ። በተፈጥሮ እውቀትና ጥበብ ተሰናስለው የተደሩ የዳበሩም ናቸው።

ለዚህም ነው አዲስ አመት በመጣ ቁጥር አዲስ አስተሳሰብና አዲስ ነፍስና ስጋ ፍለጋ የምንዋትተው። ለዚህ ነው አዲስ አመት በመጣ ቁጥር ከአምናው የተለየን ለመሆን በአዲስ እቅድና በአዲስ ምኞት የምንሳበው። ለዚህ ነው እድሜአችን የሚያሳስበን፣ ሞታችን የሚያስጨንቀን።

ትልቁ የዘመን መለወጥ ፋይዳው በአስተሳሰቡ ለተቀየረና ተሀድሶን መሰረት ላደረገ አእምሮ ነው። ለለውጥ ካልተጠቀምንበት ጊዜ መጥቶ ከመሄድ ባለፈ ትርጉም የለውም። ትርጉም ያለው ሆኖ እንዲያልፍ የምናደርገው እኛ ነን።

አዲስ አመት እንደ ትርጉሙ አዲስ ነው። በውስጡ አንዳች ሀይልና ብርታት አለው። ለሰው ልጅ ሁሉ የሚሆን የመታደስ፣ የመበርታት መንፈስን በውስጡ ይዟል። ብዙዎቻችን ይሄን ሀይል እንፈልገዋለን። በዚህ ሀይል ውስጥ መኖር እንፈልጋለን። ለዚህም አመት ጠብቀን የምናቅድ፣ አመት ጠብቀን የምንጀምር፣ አመት ሲመጣ የምንበረታ ባጠቃላይ ለምንም ነገር አዲስ አመት የምንል ብዙዎች ነን።

የአዲስነት ስሜት የሚያድርብን አዲስ አመት ሲመጣና ሲቃረብ ነው። የመስራት የመለወጥ ፍላጎታችን የሚነሳሳው መስከረም ሊጠባ ጥቂት ሲቀረው ነው። ህልሞቻችን የሚታወሱን የአበቦቹን ሽታ ተከትለን ነው። ከአሮጌነት የምንወጣው፣ ከድሮነት የምንሸሸው ጳጉሜን ተሻግረን አበባየ ሆይ ሲባል የሚመስለን እልፍ ነን።

ህይወታችን፣ መኖራችን ትርጉም ያሚያገኝ የሚመስለን በዚህ ጊዜ ነው። ለአዲስ ህይወት የምንዘጋጀው ይሄን አዲስ ዘመን ታከን ነው። ሁሉ ነገራችንን ለአዲስ አመት አሳልፈን የሰጠን ነን።

ይሄ ስህተት ነው የሰው ልጅ የጊዜ ባሪያ መሆን የለበትም። ዛሬን ለለውጥና ለስኬት መጠቀም ይኖርበታል። የምንፈልገውን ማንኛውንም ነገር ከዛሬ በመጀመር፣ ከአሁን በማቀድ ማሳካት እንችላለን። ብዙዎቻችን ዛሬን አናውቀውም። የአሁንን ሀይል አልተረዳነውም።

የቆምንባት ቅጽበት የሀይል የለውጥ መጀመሪያ እንደሆነች ገና አልደረስንበትም። አዲስ አመት የምንም ነገር መጀመሪያ እንደሆነ አምነን የተቀበልን ነን። በአዲስ አመት ሰሞን ከሞት የምንነቃ፣ ካንቀላፋንበት የምንባንን ብዙ ነን።

> **አዲስ አመት**
> **አዲስ የሚሆነው በእኛ አዲስ ልብ ነው፡፡ ልቦቻችንን አሳድፈን፣ መንፈሳችንን አስነውረን፣ ፍቅርና ይቅርታን ሳንማር፣ በመነጋገር ሳንግባባ፣ በእርቅ አንድ ሳንሆን ብንቀበለው ያው ነው እንደ ድሮው.. እኛም ከእርግማን አንወጣም**

በዚህ አስተሳሰብ ውስጥ ለውጥ የለም። በዚህ እምነት ውስጥ ስኬት የለም። ስኬት መነሻውም መድረሻውም አዲስ አመት ሳይሆን አዲስ አስተሳሰብ ነው። አዲስ አስተሳሰብ ደግሞ ዛሬን ከመጠቀም አሁንን ከመኖር የሚጀምር ነው። አዲስ አመት ሲያልፍ ምኞታችን አብሮ የሚያልፍ ከሆነ፣ አዲስ አመት ሲመጣ ምኞታችን ከሞተበት የሚነቃ ከሆነ የአዲስ አመትን ትርጉም አልተረዳነውም ማለት ነው።

ጊዜና ለውጥን አስታከው የተጻፉ ብዙ የስኬት መጽሀፎች አሉ። አንዳቸውም ለውጥ ከአዲስ ዘመን እንደሚጀምር አልጻፉም። የሁሉም የጋራ ሀሳብ ለውጥ ያለው ከዛሬና ከአሁን የሚል ነው።

በአስተሳሰቡ ላልተቀየረ ማህበረሰብ አዲስ አመት ምኑ ነው? ከመጠበቅና ተስፋ ከማድረግ ላልወጣ ሰውነት አዲስ አመት ዋጋው ስንት ነው? ፍቅርን ለማያውቅ ይቅርታን ላልተማረ ልብ ጊዜ ዘመን ምኑ ነው? ለማይሰሩ እጆች፣ ለማያስቡ ጭንቅላቶች መጠበቅ ፋይዳው ምንድነው?።

በብሄር፣ በጎሳ ለሚባላ ሀገርና ህዝብ የዘመን መቀየር ፋይዳው ምንድነው? ከወንድሞቹ ጋር ሆድና ጀርባ ሆኖ ለሚኖር፣ ተነጋግሮ መግባባት፣ ተወያይቶ መስማማት ላቃተው ፖለቲካና ፖለቲከኛ፣ ትውልድና ዜጋ መሻገር ምንድነው? እኒህ ጥያቄዎች አሁን ላለነው እኛ መሰረታዊ ናቸው። የእነዚህን ጥያቄዎች መልስ ስናውቅና ስንረዳ ብቻ ነው የአዲስ አመትን ዋጋ ልንረዳው የምንችለው።

ያለፈውን አመት እንዲህ እንደአሁኑ ለመነቃቃት ተጠቅመንው ነበር። አምናን እኮ በእልልታና በፌሽታ ተቀብለነው ነበር። ካቻምናን እኮ የደስታና የሰላም ዘመን ብለንው ነበር። ያለፈውን አመት ብዙ ልንሰራበት ብዙ ልናተርፍበት አውርተን ነበር። 2015 እኮ እንደ ሀገር፣ እንደግለሰብ ብዙ ያቀድንበት ብዙ ያሰብንበት ዘመን ነበር ፤ግን እንደሀሳባችን አልተጠቀምንበትም። እንደምኞታችን አላዋልንውም። ምክንያቱም ከዘመን ጋር የተቀየረ አእምሮ ስላልነበረን ነው ፡

በተቃራኒው አመቱ መጥፎና እድለ ቢስ እንደነበር አወራን። ምንም ያላተረፍኩበት አመት ነው ስንል ነቀፍነው። ዘመን የሚዘወረው በሰው ልጅ አስተሳሰብ ነው። ያለፉት አመታቶች ጥሩ ያልነበሩት ዘመኑ ጥሩ ስላልነበር ሳይሆን እኛ ጥሩ ስላልነበርን ነው። እኛ ስላልተቀየርን ዘመኑም አልተቀየረም።

የሰው ልጅ ልቡና አእምሮው፣ ሀሳቡና ምኞቱ ካልተቀየረ አዲስ አመት ምንም ነው። ሀሳባችንን ሳናድስ፣ ከድሮነት ሳንወጣ ሰኔና ሀምሌ ገመገም ላይ ቆመን 2015 ለኔ ጥሩ ጊዜ አልነበረም፣ ለሀገራችን መልካም አልነበረም ብንል ልክ አይደለንም።

ዘመን ለሰው ልጅ ሎሌ እንጂ ሰው ለዘመን ሎሌ አይደለም። ሁሉን ነገር ለአዲስ አመት ትተን መቀመጣችን የዘመን ጥገኞች መሆናችንን ከማሳየቱ ባለፈ እያንዳንዱን ቀን ዋጋ ለመስጠት የምናደርገው የበረታ እንቅስቃሴ እንደሌለም የሚያሳይ ነው። ዘመን በእኛ ስር ነው። አዲስ አመት አዲስ የሚሆነው በእኛ አዲስ ልብ ነው። ልቦቻችንን አሳድፈን፣ መንፈሳችንን አስነውረን፣ ፍቅርና ይቅርታን ሳንማር፣ በመነጋገር ሳንግባባ፣ በእርቅ አንድ ሳንሆን ብንቀበለው ያው ነው እንደ ድሮው..እኛም ከእርግማን አንወጣም።

ተስፋ ያደረግነው አዲሱ አመት ያሰብነውን እንደሚሰጠን ዋስትናችን ምንድነው? የሚመጣው አዲስ አመት የምንመኘውን እርቅ፣ የምንፈልገውን አንድነት፣ የራቀንን ሰላም እንደሚሰጠን መተማመኛችን ምንድነው? ምንም መተማመኛ የለንም። ልንተማመንበት የሚገባ አንድ ነገር ቢኖር ራሳችን ነን። ራሳችንን ለፍቅር፣ ለይቅርታ፣ ለመነጋገር ዝግጁ ካደረግን እንዳሰብንው አዲስ አመት አዲስ ይሆናል። ይሄ ባልሆነበት ሁኔታ አዲስ አመትን አዲስ ይሆናል ብሎ መጠበቅ ሞኝነት ነው ።

ታሪኮቻችን ውብ እና ጋፍ የሚሆኑት በእኛ ነው። ጊዜ እኛ ተኝተን የሚያነቃ ሀይል የለውም። ለምንፈልገው ሰላም፣ ለምንፈልገው አንድነት፣ ለምንፈልገው እድገት ዘመን አስተዋጽኦ የለውም። ለዚህ ምስክር የሚሆኑን ያለፉ በአዲስ ምኞት ተቀብለናቸው አዲስነትን ያልሰጡን ዘመኖች ናቸው።

ተስፋዎቻችን ሀሳቦቻችን በኩል የሚያብቡ እንጂ በመስከረም መጥባት በኩል የሚታዩ አይደሉም። እንደዚህ አይነት መለማመዶች ለማንም አይጠቅሙም። ዘመን ያው እንደትላንቱ ነው። የተፈጥሮን እውነት ጠብቆ መጥቶ የሚሄድ ነው። አትምጣ ብንለውም፣ ና ብንለውም በእኛ ፍቃድ ስር አይደለም። መጥቶ መሄድ ተፈጥሮአዊ ግብሩ ነው።

ከዚህ እውነት በመነሳት አዲስ አመት ሲመጣም ሆነ ሲሄድ የተለየ ተፈጥሮ እንደሌለው መተማመን ላይ መድረስ አለብን ። አዲስም ሆነ አሮጌ የሚሆነው በሰዎች ተጽዕኖ ነው። ቀን ሳንጠብቅ፣ ጊዜ ሳናሰላ፣ አዲስ አመት ሳንል የምንፈልገውን ማንኛውንም ነገር አሁን ላይ መፍጠር እንችላለን። ሰላም ከሆነ የምንሻው፣ አንድነት ከሆነ ፍላጎቶቻችን ሰላምና አንድነት በሚያመጡ ሀሳቦች ላይ በማተኮር የምንፈልገውን ማግኘት እንችላለን።

ባልተለወጠ እምነት የተለወጠች ሀገር አትኖርም። ለውጥ ሁልጊዜም መነሻው አእምሮ ነው። በአእምሯችን ስንለወጥ ብቻ ነው ባለውም በሚመጣውም ዘመን ላይ ጀግና የምንሆነው። ከጊዜ ባርነት መውጣት ይኖርብናል። ለምንም ነገር ነገን መጠበቃችን፣ ለምንም ነገር አዲስ አመትን መሻታችን ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ነው የሚያመዝነው።

ሰላም ሊሰጡን የሚችሉ፣ ህልምና ራዕዮቻችንን ልናሳካባቸው የሚችሉ ብዙ ቀናት፣ ብዙ ጊዜዎች አብረውን አሉ። ራሳችንን ማንቃት ከቻልን ወደትላንት ሳንሄድ፣ ወደነገም ሳናዘግም መለወጥ እንችላለን። ችግሩ ከአዲስ አመት አስተሳሰብ አልወጣንም። ችግሩ ከዛሬ ይልቅ ነገን ተስፋ የምናደርግ መሆናችን ነው። ከቻልን ጊዜ የእኛ ባሪያ እንዲሆን እንቆጣጠረው። ከቻልን እያንዳንዱን ቀናችንን የምንም ነገር አዲስ አመታችን አድርገን እንቀበለው።

በጊዜ ባርነት ውስጥ ልዕልና የለም። በመጠበቅ ውስጥ ንግስናና ክብር ምንም ናቸው። ሰው ከትጋት ሲጎድል፣ ከጥረት ሲላላ ለምንም ነገር ጊዜን መጠበቅ ይጀምራል። ጊዜን የመጠበቃችን ምክንያት ስንፍናና አጉል የኑሮ ዘየቤ መልመዳችን ነው። በእውቀትና በእቅድ መኖር ብንጀምር እያንዳንዷ ቀን አዲስ አመታችን ትሆን ነበር ወይም ደግሞ ከአዲስ አመት በበለጠ ምን ያክል ለለውጥና ለስኬት አውፈላጊ እንደሆነች እንረዳ ነበር።

በትጋት ስንሞላ ለምንም ነገር ጊዜ እኛን መጠበቅ ይጀምራል። በትጋት ስንሞላ ምንም ነገር ከአሁን እንጀምራለን። ጊዜን መጠበቅና በጊዜ መጠበቅ ሁለት የተለያዩ እውነቶች ናቸው። ልክ ለምንም ነገር አዲስ አመትን እንደሚጠብቁት እና ለምንም ነገር ዛሬ የተሻለ ቀን ነው ብለው እንደሚያምኑት ሁለት ጉራማይሌ ነፍሶች አይነት።

ትጉ ነፍሶች የሚፈልጉትን ዘመን ዛሬ ላይ ይፈጥሩታል። ታካች ነፍሶች ደግሞ በመንቀፍ፣ በመሰልቸት፣ በስንፍና፣ በአይሆንልኝም፣ በማመንታት፣ በመወላወል፣ ቆይ ነገ በሚል እሳቤ በመጠበቅ ውስጥ ይቆማሉ። ብዙ ዛሬዎችን፣ ብዙ አሁኖችን፣ ብዙ ነገዎችን ዘለን አዲስ አመትን መጠበቃችን ስንፍናና ስልቹነት ምን ያክል ስር እንደሰደደብን አመላካች ነው።

ብልህ ሰው በብሩህ ሀሳቡ በኩል ዛሬን አዲስ አመት ማድረግ ይችላል። ጠንካራ ሰው ወደ ነገ ሳይሄድ፣ ወደ አምና ሳይሳብ አሁንን ለለውጥና ለስኬት መጠቀም ይቻለዋል።ለተጋ ልብ፣ ለበረታ አእምሮ ሁሌም ስኬት፣ ሁሌም አዲስ አመት አለ። አዲስ አመት ለእኛ ብሎ የሚያደርገው ምንም ነገር የለም። መጥቶ እንዲሄድ የተፈጥሮ ግዳጁን እየተወጣ ነው።

እኛ ነን ከተፈጥሮ የራቅነው። እኛ ነን ማስተዋል የጎደለን..በጊዜ ሀቅ ውስጥ ቆመን እንኳን መማር አልቻልንም። ለመማር ዝግጁ ብንሆን ጊዜ የሚያስተምረን ብዙ ነበረው። አምናን በጉጉት ጠብቀንው የምንፈልገውን ሰላምና አንድነት ካልሰጠን፣ 2015 ለነበሩብን ችግሮች መፍትሄ አድርገንው ቃሉን ከበላ ችግሩ ከጊዜው ሳይሆን ከእኛ እንደሆነ ልንረዳ ይገባል። አዲሱን 2016 በአምና ልብ ሳይሆን በታደሰና በተቀየረ ልብ ልንቀበለው ይገባል። ያኔ ያለጥርጥር የምንፈልገውን እናገኛለን..እንደምኞታችንም ዘመኑ አዲስ መሆን ይጀምራል።

የሚሰማ ጆሮ የሚያስተውል ልብ ቢኖረን ኖሮ የጊዜን ሹክሹክታ እናደምጠው ነበር። ጊዜ ህላዊ ኖሮት መናገር ቢችል ኖሮ ‹..እባካችሁ አትጠብቁኝ እኔ ለሰው ልጅ የሚሆን ምንም የለኝም፣ ለበረቱ እየመጣሁ የምሄድ፣ ለጠንካሮች ሚዛኔን የደፋሁ ነኝ› የሚለን ይመስለኛል። በዚህ አያበቃም ፡-

‹ከኔ ይልቅ ዛሬና ነገ የላቀ ዋጋ አላቸው። አስራ ሁለት ወራትን አልፋችሁ፣ ሀምሳ ሁለት ሳምንታትን ትታችሁ፣ ሶስት መቶ ስልሳ አምስት ቀናትን ሽራችሁ የምትጠብቁኝ ምናችሁ ሞኝ ነው? ሲል የሚያላግጥብን ይመስለኛል። መች በዚህ ያበቃና ‹ልቦቻችሁን ሳታድሱ፣ አመለካከታችሁን ሳትቀይሩ ጥሩ ነው መጥፎ ነው እያላችሁ አትሙኝ። እኔ ጥሩና መጥፎ የመሆን ስልጣን የለኝም። መጥቼ እንድሄድ የታዘዝኩ የተፈጥሮ መንገደኛ ነኝ እናም አትጠብቁኝ በአሁናችሁ ላይ በርትታችሁና ተልቃችሁ ቁሙ› ይለን ነበር።


ምኞታችን መልካም ጊዜ ከሆነ እጆቻችንን በስራ፣ ልቦቻችሁን በትጋት እናጥመድ። ምኞታችን ሰላም፣ ፍቅር፣ አንድነት፣ ወንድማማችነት ከሆነ ደግሞ ለነዚህ የሚሆን የተግባቦት ሰውነት እንፍጠር ። ካልሰራንበት፣ ካልበረታንበት አዲሱ አመትም እንደ አምናና ካቻምና ርባና ቢስ ሆኖ ነው የሚያልፈው።

አዲስ አመት የዛሬ አብራክ ነው። ብዙ ዛሬዎች ተቆጥረው ነው  አዲስ አመት የሰጡን። ለምንድነው ዛሬአችንን አዲስ አመት አድርገን የማንቀበለው? ለምንድነው አዲስ አመት ሲመጣ የምናገኘውን ሀይልና ብርታት በቆምንባት ዛሬ ላይ የማንፈጥረው?

አዲስ አመት የቀናት ጥርቅም ነው። አዲስ አመት የሳምንታት የወራት ሂደት ነው። ለመለወጥ ካልተጋን የሚሰጠን አንዳች ነገር የለውም። እኛ እስካልተለወጥን ድረስ የአዲስ አመት መምጣት ምንም ነው..ቤስቲ ቤስታ የለውም።

ጊዜ በተለይም አዲስ ዘመን በእያንዳንዳችን ህይወት ላይ ዋጋ የሚኖረው የአሁንን ወይም ደግሞ የዛሬን ዋጋ ስናውቅ ብቻ ነው። አምና አዲስ ያልነው ዘንድሮ አሮጌ ብለን ሸኝተንዋል። ብዙም  አላተረፍንበትም። ስለዚህ ከዘመን ቁራኛነት ወጥተን ዛሬን አዲስ አመት እናድርግ። በተለወጠ ልብ በተለወጠ ሀሳብ የተለወጠ ሀገርና ህዝብ እንፍጠር።

# ዓለም አቀፍ



## ሩሲያ 'የጥቁር ባህር ስምምነትን' ለማደስ የሚደረገው ጥረት የማይሳካ ነው አለች

በጋዜጣው ሪፖርተር

የሩሲያ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሰርጌ ላቭሮቭ ተመድ 'የጥቁር ባህር የእህል ስምምነትን' ለማደስ የሚያደርገው ጥረት የማይሳካ መሆኑን ተናገሩ።

በማደግ ላይ ያሉ ሀገራትን ድጋፍ የሚሹት አሜሪካ እና አውሮፓ በተቀረው ዓለም ላይ ንቀት እያሳዩ ነው ያሉት ላቭሮቭ ሩሲያ ተመድ ስምምነቱን ለማደስ የሚያደርገውን ጥረት ባትቃወምም በቅርቡ ያቀረበው ምክረሃሳብ ግን ከእውነት የራቀ ነው ብለዋል።

ላቭሮቭ ይህን ያሉት የዩክሬኑ ፕሬዚዳንት በአካል በተገኙበት እና ምዕራባውያን አጋሮቻቸው ለኪቭ ድጋፍ በሻቱበት የኒው ዮርኩ የተመድ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ ነው። ላቭሮቭ ከጉባዔው ጎንለጎን ከ30 ሀገራት በላይ ከመጡ ዲፕሎማቶች ጋር መወያየታቸውን ገልጸዋል።

ተመድ ሩሲያ በፈረንጆቹ 2022 በዩክሬን ልዩ ያለችውን ወታደራዊ ዘመቻ ከጀመረች በኋላ አንዳቸው ሌላቸውን ለማሸነፍ በሚያደርጉት ጥረት የምግብ እጥረት ቀውስ እና አዲስ የዲፕሎማቲክ ፍጥጫ ተፈጥሯል የሚል ወቀሳ አቅርቧል።

ላቭሮቭ 193 አባል ሀገራት ባሉት የተመድ ጠቅላላ ጉባዔ ላይ በአብዛኛው የዓለም ማኅበረሰብ እና ለማሸነፍ የቅኝ ግዛት ዘዴን በሚጠቀሙ ጥቂቶች መካከል ትግል እየተካሄደ ነው ብለዋል።

በፈረንጆቹ ሐምሌ 2022፣ በቱርክ እና በተመድ አማካኝነት የተደረሰው እና ዩክሬን እህሏን በጥቁር ባህር በኩል ወደ ውጭ እንድትልክ ያስቻላት «የጥቁር ባህር የእህል ስምምነት» ሩሲያ ከስምምነቱ በመውጣቷ ምክንያት ፈርሷል።

ሩሲያ ከስምምነቱ የወጣችው በስምምነቱ መሠረት የምትፈልገው ተፈጻሚ አለመሆኑን በመግለጽ ነበር። ላቭሮቭ ለተመድ ዋና ጸሐፊ በጻፉት ደብዳቤ ተመድ ያቀረበው ምክረሃሳብ ሊተገበር የማይችል እና የማይሳካ መሆኑን መግለጻቸውን ሮይተርስ ዘግቧል።

## ኡጋንዳ ሶማሊላንድ ከሶማሊያ እንድትዋሃድ አደራድራለሁ አለች

በጋዜጣው ሪፖርተር

ኡጋንዳ ሶማሊያ እና ተገንጥላ ራሷን እያስተዳደረች ያለችው ሶማሊላንድ ውህደት እንዲፈጥሩ ለማድረግ እንደምታደራድር አስታውቃለች። ሶማሊላንድ ከሶማሊያ ከተገነጠለች ሦስት አስርት አመታትን አስቆጥራለች።

የኡጋንዳው ፕሬዚዳንት ዮሪ ሙሰቨኒ የማደራደሩን ሚና ለመወጣት የተስማሙት ባለፈው አርብ የሶማሊላንድ ልዩ መልዕክተኛ ጃማ ሙሳ ጃማ በኡጋንዳ ጉብኝት ማድረጋቸውን ተከትሎ መሆኑን የፕሬዚዳንት ጽ/ቤት ባወጣው መግለጫ ገልጿል።


«ፕሬዚዳንት ሙሰቨኒ በሶማሊላንድ እና ሶማሊያ መካከል ውህደት ለማመቻቸት ተስማምተዋል» ብሏል መግለጫው። ሶማሊላንድ ከሶማሊያ የተገነጠለችው በፈረንጆቹ በ1991 ቢሆንም የነፃ ሀገርነት ዓለምአቀፍ እውቅና አላገኘችም።

ሙሰቨኒ እንደስትራቴጂ ሲታይ ስህተት ስለሆነ መገንጠልን እንደማይደግፉ ገልጸዋል። ይህ ውህደት የአፍሪካ ቀንዷን ሶማሊያን የአልሸባብ ጥቃትን ጨምሮ በሌሎች ቡድኖች የሚሰነዘሩ ጥቃቶችን ለመቋቋም አቅም ይፈጥርላታል።



ሶማሊላንድ ከሶማሊያ የተገነጠለችው በፈረንጆቹ በ1991 ቢሆንም የነፃ ሀገርነት ዓለምአቀፍ እውቅና አላገኘችም

# ስፖርት



## የሴቶች የማራቶን ክብረወሰን ለመጀመሪያ ጊዜ በኢትዮጵያ እጅ ገባ

**ቦጋለ አበበ**

ኢትዮጵያዊቷ አትሌት ትዕግስት አሰፋ የማራቶንን የዓለም ክብረወሰን ትናንት በርሊን ላይ ሰበረች። ባለፈው አመት በዚሁ በርሊን ማራቶን የቦታውን ክብረወሰን በማሻሻል አሸናፊ የነበረችው ትዕግስት ዘንድሮ ለሁለተኛ ተከታታይ ድል ወደ በርሊን ስትመለስ የዓለምን ክብረወሰን ትሰብራለች ብሎ የጠበቀ አልነበረም። ያምሆኖ አስደናቂዋ አትሌት ያልታሰበውን አሳኪታ ክብረወሰኑን በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በኢትዮጵያ እጅ አስገብታለች።

አስደናቂዋ ኢትዮጵያዊት አትሌት ከባዱን የማራቶን ክብረወሰን 2:11:53 በሆነ አዲስ ሰዓት ለማመን በሚከብድ ብቃት አነክታዋለች። ይህም 2019 ላይ ኬንያዊቷ አትሌት ብሪጊድ ኮስጌ በቺካጎ ማራቶን ካስመዘገበችው የቀድሞው 2:14:04 ከሁለት ደቂቃ በላይ የተሻለ ሆኗል።

አትሌት ትዕግሥት ወደ ማራቶን ውድድር የገባችው ብዙም ትኩረት ሳይሰጣት ነው። ከዚህ ውድድር በፊት በማራቶን የሩጫ ዘርፍ የተወዳደረችው ሁለት ጊዜ ብቻ ነበር። ከባለፈው ዓመት የበርሊኑ ውድድር ቀድሞ የተሳተፈችው በሳውዲ አረቢያ በተዘጋጀው የሪያድ ማራቶን ላይ ሲሆን 2:34:00 በሆነ ሰዓት ነበር ያጠናቀቀችው።

ትናንት በበርሊን በተካሄደውና ሁለተኛዋ በሆነው የበርሊን ማራቶን ውድድር የራሷን ሰዓት በሦስት ደቂቃ ገደማ አሻሽላለች። ለረዥም ጊዜያት የ800 ሜትር ሯጭ የነበረችው ትዕግሥት፣ በቅርቡ ነው ወደ ጎዳና ሩጫ ፊቷን ያዞረችው። በ2016 ኦሊምፒክ ኢትዮጵያን ወክላ በ800 ሜትር ተሳትፋለች። ሆኖም ከግማሽ ፍጻሜው ማለፍ ባለመቻሏ ከውድድሩ ውጪ ሆና ነበር። ትዕግሥት ከ800 ሜትር በተጨማሪ በ400 ሜትርም ስትወዳደር ቆይታለች።

አትሌቷ ቀደም ሲልም የግማሽ ማራቶን ውድድሮችን ለማሸነፍ በቅታለች። ትዕግስት የዛሬ አመት ስታሸንፍ የገባችበት 2:15:37 ሰዓት በወቅቱ የኢትዮጵያ የሴቶች ማራቶን ክብረወሰን ሆኖ ነበር። አሁን ደግሞ በልምምድ ጓደኛዋና በዓለም ቻምፒዮኗ አማኔ በሪሶ 2:14:58 እጅ ተይዟል። ትዕግስት አሰፋ አንድ ወቅት በጉዳት ምክንያት አትሌቲክስ በቃሽ ተብላ ነበር፣ እንኳን ለመሮጥ መራመድ ይቸግርሻል ተብላ የነበረችው አትሌት ግን ተስፋ ሳትቆርጥ የዓለም ክብረ ወሰን ባለቤት ሆናለች።

በዓለም አትሌቲክስ ውድድር ውስጥ ከፍተኛ የሚባለው የፕላቲኒየም ደረጃ ያለው የበርሊን ማራቶን የተጀመረው እንደ አውሮፓውያኑ በ1974 ነው። በጀርመን መዲና የሚካሄደው ውድድር ፈጣን ሰዓት ከሚመዘገብባቸው የማራቶን ውድድሮች መካከልም አንዱ ነው። ኢትዮጵያውያን አትሌቶች በዚህ ውድድር በተለያዩ ጊዜያት ያሸነፉ ሲሆን ኃይሌ ገብረሥላሴ እና ቀነኒሳ በቀለ ቀዳሚዎቹ ናቸው።

በሴቶች በኩል ጌጤ ዋሚ ውድድሩን ለማሸነፍ የቻለች የመጀመሪያዋ ኢትዮጵያዊት ናት። ጌጤ እንደ አውሮፓውያኑ በ2006 እና በ2007 ውድድሩን በተከታታይ ማሸነፍ ችላለች።

በበርሊን ማራቶን 12 ጊዜ የዓለም ክብረወሰን ተሻሽሏል ዘጠኙ በወንድ ሦስቱ በሴቶች። ኃይሌ ገብረሥላሴ እና ኢሉድ ኪፕቾጌ ሁለት ሁለት ጊዜ የዓለም ክብረ ወሰንን ያሻሻሉት እዚህ በርሊን ማራቶን ነው።

17 ጊዜ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች በርሊንላይ አሸንፈዋል። ኃይሌ ገብረሥላሴ(4ተከታታይ ጊዜ)፣ ቀነኒሳ በቀለ(2ጊዜ) እና ጉዬ አዶላ በወንዶች ያሸነፉ ናቸው። ኬንያዊው የርቀቱ ፈርጥ ኪፕቾጌ ትናንት ይህን ውድድር ለአምስተኛ ጊዜ በማሸነፍ የመጀመሪያ የሆነበትን ታሪክ ሠርቷል። በማራቶን ውድድር ለመጀመሪያ ጊዜ የተሳተፈው ማርክ ኮሪር ኪፕቾጌን ተከትሎ የገባ ሲሆን፥ ኢትዮጵያዊው አትሌት ታደሰ ታከለ 3ኛ ደረጃን ይዞ አጠናቋል።

ጌጤ ዋሚ(2ጊዜ)፣ አበሩ ከበደ(3ጊዜ)፣ አፀደ ሀብታሙ፣ አሼቴ በከሪ፣ ትርፌ ፀጋዬ፣ ጎትይቶም ገብረሥላሴ እና ትዕግስት አሰፋ ሴት ኢትዮጵያውያን የበርሊን ማራቶን ከዚህ ቀደም አሸናፊዎች ናቸው።

